2. ተገቢ የወሲብ መገለጫዎች

I. ቀዳሚ መረጃ

የተማሪው ዐላማዎች

1. በወንድና በሴት መካከል ተገቢ የሆነ የወሲብ ግንኙነት መገለጫ ይሆን ዘንድ እግዚአ ብሔር ጋብቻን ፈቅዶ እውን ያደረገ መሆኑን መገንዘብ፤
2. እግዚአብሔር በጋብቻ ውስጥ ወሲብ ውብ፣ አስደሳች፣ የዕድሜ ዘመን ግንኙነትም ከፍተኛው መገለጫ አድርጎ ያቀደው መሆኑን ማስተዋል፤
3. ለተገቢው ወሲባዊ መገለጫ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች መግለጽ፤
4. ወሲባዊ ግንኙነት በተገቢው መንገድ መግለጽ የሚያስገኘው ጥቅም፤
5. ከጋብቻ በፊት ወሲብ ላለመፈጸም ቃል መግባት፤
6. ከተገቢ ወሲባዊ መገለጫዎች ጋር ለተያያዙት ቃላት ፍቺ መስጠት መቻል።

ትምህርቱን ከሕይወት ጋር ለማዛመድ የቀረቡ ሐሳቦች

1. ወጣቶች የጾታ ልዩነትና የወሲብ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን በሚገነዘቡበት ወቅት፣ እግዚአብሔር የወሲብን ስጦታ የፈጠረ መሆኑንና በመጽሐፍ ቅዱስ መስፈርት መሠረትም ተገቢው የወሲብ መገለጫ ምን እንደ ሆነ ማወቅ ያስፈልጋቸዋል።
2. እግዚአብሔር አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት ወይም አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ ትሆን ዘንድ ላቀደው ዕቅድ ተማሪዎች ራሳቸውን ማስገዛት አለባቸው።
3. የአንዲት ሴት ባል ወይም የአንድ ወንድ ሚስት መሆን ለምናገባው ሰው ራሳችንን በግብረ ገብ ረገድ ንጹሕ አድርጎ መጠበቅ ማለት ነው።
4. በተቃራኒ ጾታ መካከል ያለው መሳሳብ የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ፍጥረት ክፍል ነው፤ ይህም እግዚአብሔር መልካም ነው ያለው ፍጥረት ነው፤ ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር የተሰጠው የወሲብ ፍላጎት በኀጢአት የተበከለ መሆኑን መገንዘብ አለብን።
5. ከጋብቻ በፊትና በጋብቻ ውስጥ ከትዳር ጓደኛ ውጭ ሩካቤ ሥጋ ከመፈጸም ለመታቀብ፣ ለአያሌ ፈተናዎችና ግፊቶች ጀርባን በመስጠት እንዴት ተደላድሎ መቆም እንደሚቻል ትምርህትን ይጠይቃል።
6. አካልህ የወደፊት የትዳር ጓደኛህ ነው፤ ስለዚህ ሳይበከል በንጽሕና ጠብቀው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች

ዘፍጥረት 2÷24፤ 24÷67፤ ማቴዎስ 19÷4-6፤ ማሕልየ መሓልይ 2÷7፤ 3÷5፤ 8÷4:6-7፤ 1ቆሮንቶስ 7÷1-8

አዲሱ መደበኛ ትርጉም	የ1980 ዓ.ም. ኅትመት ትርጉም
ዘፍጥረት 2÷24 24 ስለዚህ ሰው ከአባቱና ከእናቱ ተለይቶ ከሚስቱ ጋር ይጣመራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።	ዘፍጥረት 2÷24 24 ወንድ አባቱንና እናቱ ትቶ ከሚስቱ ጋር የሚተ ባበረው ስለዚህ ነው፤ ሁለቱም አንድ ይሆናሉ።

አዲሱ መደበኛ ትርጉም	የ1980 ዓ.ም. ጎትመት ትርጉም
ዘፍጥረት 24÷67 67 ይስሐቅም ርብቃን ወደ እናቱ ወደ ሣራ ድንኳን ይዟት ገባ፤ አገባትም፤ ሚስት ሆነችው፤ እርሱም ወደዳት። ይስሐቅም ከእናቱ ሞት ተጽናና።	**ዘፍጥረት 24÷67** 67 ከዚህ በኋላ ይስሐቅ እናቱ ሣራ ትኖርበት ወደነበረው ድንኳን ርብቃን ይዞአት ገባ፤ ሚስትም ሆነችው፤ ይስሐቅ ርብቃን ወደዳት፤ በእናቱ ሞት ምክንያት ከደረሰበትም ሐዘን በዚህ ሁኔታ ነጽናና።
ማሕልየ መሓልይ 2÷7፤ 3÷5፤ 7÷4:6-7፤ 8÷4:6-7 2÷7 እናንት የኢየሩሳሌም ቈነጃጅት፣ ራሱ እስኪፈልግ ድረስ፣ ፍቅርን እንዳታስነሡት ወይም እንዳትቀሰቅሱት በሚዳቋና በሜዳ ዋልያ አማጥናችኋለሁ።	**ማሕልየ መሓልይ (ሰሎሞን) 2÷7፤ 3÷5፤ 7÷4:6-7፤ 8÷4:6-7** 2÷7 እናንተ የኢየሩሳሌም ቈነጃጅት ሆይ! ፍቅር ራሱ ፈቅዶ እስኪነሣ ድረስ ቀስቅሳችሁ እንዳታስነሡት በፈጣን አጋዝንና በምድረ በዳ ዋልያ ስም ዐደራ አላችኋለሁ።
3÷5 እናንት የኢየሩሳሌም ቈነጃጅት፣ ራሱ እስኪፈልግ ድረስ ፍቅርን እንዳታስነሡት ወይም እንዳትቀሰቅሱት፣ በሚዳቋና በሜዳ ዋልያ አማጥናችኋለሁ። 8÷4 እናንት የኢየሩሳሌም ቈነጃጅት፣ ራሱ እስኪፈልግ ድረስ ፍቅርን እንዳታስነሡት ወይም እንዳትቀሰቅሱት፣ አማጥናችኋለሁ። 8÷6 በልብህ እንዳለ፣ በክንድህም እንደምትይዘው ማኅተም አስቀምጠኝ፤ ፍቅር እንደ ሞት የበረታች፣ ቅናቷም እንደ መቃብር ጨካኝ ናትና፤ እንደሚንበገበግ እሳት፣ እንደ ኀይለኛም ነበልባል ትነዳለች። 8÷7 የውሃ ብዛት ፍቅርን ሊያጠፋ አይችልም፤ ፈሳሾችም አያሰጥሟትም፤ ሰው የቤቱን ሀብት ሁሉ ስለ ፍቅር ቢሰጥ ፈጽሞ ይናቃል።	3÷5 እናንተ የኢየሩሳሌም ቈነጃጅት ሆይ! ፍቅር ራሱ ወዶ እስኪነሣ ድረስ ቀስቅሳችሁ እንዳታስነሡት በፈጣን አጋዝንና በምድረ በዳ ዋልያ ስም ዐደራ አላችኋለሁ። 8÷4 እናንተ የኢየሩሳሌም ቈነጃጅት ሆይ! ፍቅር ራሱ ወዶ እስኪነሣ ድረስ ቀስቅሳችሁ እንዳታስነሡት ዐደራ አላችኋለሁ። 8÷6 በዘላለማዊ ፍቅር በልብህ ውስጥ አትመኝ፤ በክንድህም እንደ ማኅተም እኔን ብቻ ያዘኝ፤ ፍቅር እንደ ሞት የበረታች ናት፤ ቅንአትም እንደ መቃብር የከፋች ናት፤ በምትነድበትም ጊዜ እንደ እሳት ወላፈን ትገርፋለች። 8÷7 የውሃ ብዛት የፍቅርን እሳት ሊያጠፋ አይችልም፤ ጕርፍም ጠራርጎ ሊወስዳት አይችልም፤ ሰው ባለው ሀብት ሁሉ ፍቅርን ለመግዛት ቢሞክር፣ ፍቅር በገንዘብ ስለማትገኝ ሰዎች ይንቁታል።
1ቆሮንቶስ 7÷1-8 1 ስለ ጻፋችሁልኝ ጕዳይ፣ ሰው ወደ ሴት ባይደርስ መልካም ነው። 2 ነገር ግን ከዝሙት ለመጠበቅ፣ እያንዳንዱ ሰው የራሱ ሚስት ትኑረው፤ እያንዳንዷም ሴት የራሷ ባል ይኑራት። 3 ባል ለሚስቱ የሚገባትን ሁሉ ያድርግላት፤ ሚስትም እንዲሁ ለባሏ የሚገባውን ሁሉ ታድርግለት።	**1ቆሮንቶስ 7÷1-8** 1 ስለ ጻፋችሁልኝ ጥያቄ ሰው ከሴት ጋር በግብረ ሥጋ ባይገናኝ ወይም ሚስት ባያገባ መልካም ነው። 2 ነገር ግን በዝሙት ኃጢአት ላለመውደቅ፤ እያንዳንዱ ወንድ የራሱ ሚስት ትኑረው፤ እያንዳንዷም ሴት የራሷ ባል ይኑራት። 3 ባል ለሚስቱ ማድረግ የሚገባውን የጋብቻ መብትዋን አይከልክላት፤ እንዲሁም ሚስት ለባልዋ ማድረግ የሚገባትን የጋብቻ መብቱን አትከልክለው።

አዲሱ መደበኛ ትርጉም	የ1980 ዓ.ም. ጎተመት ትርጉም
4 ሚስት አካሏ የራስዋ ብቻ አይደለም፤ የባሏም ነው፤ እንዲሁም ባል አካሉ የራሱ ብቻ አይደለም፤ የሚስቱም ነው።	4 ሚስት በሰውነቷ ላይ ሥልጣን የላትም፤ በእርስዋ ሰውነት ላይ ሥልጣን ያለው ባልዋ ነው። እንዲሁም ባል በሰውነቱ ላይ ሥልጣን የለውም፤ በእርሱ ሰውነት ላይ ሥልጣን ያላት ሚስቱ ነች።
5 በጸሎት ለመትጋት ተስማምታችሁ ለተወሰነ ጊዜ ካልሆነ በስተቀር፤ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ፤ ራሳችሁን ባለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈትናችሁ እንደ ገና አብራችሁ ሁኑ።	5 በጸሎት ለመትጋት ሁለታችሁም ተስማምታችሁ ለተወሰነ ጊዜ ካልሆነ በቀር፤ በመለያየት አንዱ የሌላውን የጋብቻ መብት አይከልክል። ራሳችሁን መቈጣጠር አቅቶአችሁ ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ እንደ ገና አብራችሁ ሁኑ።
6 ይህን የምለው ግን እንደ ትእዛዝ ሳይሆን እንደ ምክር ነው።	6 ይህን ግን የምላችሁ እንደ ምክር ነው እንጂ እንደ ትእዛዝ አይደለም።
7 ሰው ሁሉ እንደ እኔ ቢሆን ምኞቴ ነው። ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው ከእግዚአብሔር የተቀበለው የራሱ የሆነ ስጦታ አለው፤ አንዱ አንድ ዐይነት ስጦታ ሲኖረው፤ ሌላው ደግሞ ሌላ ዐይነት ስጦታ አለው።	7 ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሚስት ሳያገባ ቢኖር በወደድሁ ነበር፤ ነገር ግን ለእያንዳንዱ እግዚአብሔር የተለየ ስጦታ ሰጥቶታል፤ አንዱ አንድ ዐይነት ስጦታ፤ ሌላውም ሌላ ዐይነት ስጦታ አለው።

II. ዳራዊ መረጃ

አስተዋፅኦ

I. ጋብቻ ተገቢ የወሲብ መገለጫ መሆኑ፤

ሀ. ወሲብ በጋብቻ ውስጥ ብቻ የሚገለጸው በተለያዩ ምክንያቶች ነው።

1. የእግዚአብሔርን የጋብቻ ዕቅድ ለመፈጸም (ዘፍ 2፥24፤ ማቴ 19፥4-6)
   - ሀ) ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው
   - ለ) ጋብቻን ፈቅዶ ለሰው ዘር እውን አደረገ
   - ሐ) ጋብቻ በወንድና በሴት መካከል የዕድሜ ልክ ጥምረት እንዲሆን ፈለገ
2. አንዱ ለሌላው ከልብ ፍቅሩን ለማካፈል (ዘፍ 24፥67፤ ማሕልየ ማሓልይ 2፥7፤ 3፥5)
3. የጋለ ፍቅር መገለጫ እንዲሆን (ማሕልየ መሓልይ 2፥7፤3፥5)
4. ኢግብረገባዊ ከሆነ የወሲብ ኀጢአት ለመራቅ (1ቆሮ 7፥1፡2)
5. በአፍቃሪው ሰው በኩል የእግዚአብሔርን ቸርነት ለማድነቅ፤ በጋብቻ አንድ በመሆንና በወሲባዊ ግንኙነት ለሰሚሰጠው በረከት ለእርሱ ምስጋና ለማቅረብ (ማሕልየ መሓልይ 8፥4፡6-7)
6. ጥንዶች አንድ ይሆኑ ዘንድ ማስተሳሰሪያ ለመሆን (1ቆሮ 7፥15)

ለ. በጋብቻ ውስጥ ወሲባዊ ግንኙነትን ለመግለጽ አስፈላጊ ሁኔታዎች

1. ብስለት - ጋብቻ እስከሚፈጸም ድረስ ፍቅርን አታነሣሣ ወይም አትቀስቅስ (ማሕልየ መሓልይ 2፥7፤ 3፥5፤ 8፥4)።
2. ቃል ኪዳን፡- ከአባትና ከእናቱ «ተለይቶ ከሚስቱ ጋር ይጣመራል» (ዘፍ 2፥24)።
3. የግል መሆን - «እያንዳንዱ ሰው የራሱ ሚስት ትኑረው፤

እያንዳንዷም ሴት የራሷ ባል ይኑራት» (1ቆሮ 7÷2)።

4. ዘላቂነት - «እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለየው» (ማቴ 19÷6)።
5. ለብቻ መሆን - «ይስሐቅም ርብቃን ወደ እናቱ ወደ ሣራ ድንኳን ይዟት ገባ (ዘፍ 24÷67)።
6. ግልጽነት - «አዳምና ሚስቱ፣ ሁለቱም ዕራቍታቸውን ነበሩ፤ ይሁን እንጂ አይተፋፈሩም ነበር (ዘፍ 2÷25)።
7. ራስን መግዛት - ፍቅር ቅዱስና ክቡር በሆነ መንገድ መገለጽ አለበት (1ተሰ 4÷4)።
8. ፍቅር - «እንዴት ውብ ነሽ! እንዴትስ ደስ የምትይ ነሽ! ፍቅሬ ሆይ፤ የምታስደስቺ ነሽ (ማሕልየ ማሓልይ 7÷6፤ 1ተሰ 4÷4)።
9. ተዘውታሪነት (1ቆሮ 7÷5)
10. ለጤናማ ወሲባዊ መገለጫ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ሁኔታዎች
    ሀ. አድናቆት (ማሕልየ መሓልይ 7÷1-9)
    ለ. መስማማት «እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ» (1ቆሮ 7÷5)
    ሐ. የግል ማድረግ «እያንዳንዱ ሰው የራሱ ሚስት ትኑረው፤ እያንዳንዷም ሴት የራሷ ባል ይኑራት» (1ቆሮ 7÷22)
    መ. ጎላፊነት - ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይጣመራል» (ማቴ 19÷5)
    ሠ. መተማመን «ሚስት አካሏ የራስዋ ብቻ አይደለም፤ የባሏም ነው፤ እንዲሁም ባል አካሉ የራሱ ብቻ አይደለም፤ የሚስቱም ነው (1ቆሮ 7÷4)
ሐ. ወሲባዊ ግንኙነትን በጋብቻ ውስጥ መግለጹ የሚያስገኛቸው ጥቅሞች
    1. ወዲያው የሚገኙ ጥቅሞች
        ሀ. ሥጋዊ ርካታ የሚገኘው የጋብቻ ግዴታን በመፈጸም ነው (1ቆሮ 7÷3)
        ለ. በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጸም በደል እንዲቀር ያስችላል (1ቆሮ 7÷1-2)
    2. ዘላቂ ጥቅሞች - ፍቅርና ጎብረት (ሁሉም ምንባቦች)
    3. የረጅም ጊዜ ጥቅሞች - ዘር ማፍራት (ዘፍ 4÷1)።

II. ላያገቡ መቅረት አማራጭ ጸታዊ መግለጫ መሆኑ (1ቆሮ 7÷1፡7-8)።
    ሀ. ጳውሎስ ይበጃል አለ፤ሰው ወደ ሴት ባይደርስ መልካም ነው (7÷1)።
    ለ. ጳውሎስ ላያገባ ኖሮአል፡- ሰዎች ሁሉ እንደ እርሱ ቢሆኑ ተመኝቶአል (7÷7)።
    ሐ. ጳውሎስ ይህንኑ አብራርቶአል «ያላገቡና ባሎቻቸው የሞቱባቸው ላያገቡ መቆየታቸው መልካም ነው (7÷8)።

ይዘታዊ እጥርታ

እግዚአብሔር ወንድንና ሴትን ፈጥሮ በመካከላቸው ጋብቻ እንዲሆን ሲፈቅድ ለግንኙነታቸው የሚረዳ ቀላል የሆነ ግን ጥልቅ ምስጢር ያለውን የሚከተለውን ቀመር መሠረተ፤ «ስለዚህ ሰው ከአባቱና ከእናቱ ተለይቶ ከሚስቱ ጋር ይጣመራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ» (ዘፍ 2÷24)። እዚህ ላይ እግዚአብሔር የሰው ወሲባዊ ግንኙነት ከእንስሳት ወሲባዊ ግንኙነት ወይም ዘርን ለማፍራት ሲባል ከሚፈጸመው ሥጋዊ ተግባር በላይ እንዲሆን አድርጎ የሠራው መሆኑን እናያለን። እግዚአብሔር ለሰው ዘር ባቀደው ወሲባዊ ግንኙነት ውስጥ ከሚታዩት ልዩ ባሕርያት አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው፤

1. ብስለት እንዲኖር ያስፈልጋል፤ እግዚአብሔር ለሰዎች ያዘጋጀው የጋብቻ ዕቅድ ከሚጠይቃቸው ነገሮች አንዱ ወንዱ (በተዘዋዋሪም ሴቷ) ወላጆቹን ትቶ ለመውጣትና የራሱን ቤተ ሰብ ለመመሥረት የበሰለ ሰው ሆኖ እንዲገኝ ነው። በማሕልየ መሓልይ ላይ ጥበበኛው፣ አንድ ሰው ጊዜው ሳይደርስ ፍቅርን እንዳይቀሰቅስ ያስጠነቅቃል (2÷7፤ 3÷5፤ 8÷4)፤ ምክንያቱም ጥልቅ የፍቅር ስሜት ከሞት ይልቅ ብርቱ ነው፤ እንደ እሳት ይቀጣጠላል፤ ከሀብትም ይልቅ እጅግ የከበረ ነው (8÷6-7)። እንዲህ ያለው ፍቅር በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ገና ከጧቱ ከተቀሰቀሰ አጥፊ ይሆናል።

2. ቃል ኪዳን እንዲኖር ያስፈልጋል፤ በእግዚአብሔር የጋብቻ ዕቅድ ውስጥ አስፈላጊ የሆነው ሁለተኛው ነገር ወንዱ፣ «ተለይቶ» ከሚስቱ ጋር «አንድ ሥጋ» እንዲሆን ነው፤ እዚህ ላይ የዕብራይስጡ ቃል «መጣበቅ» ማለት ሊሆን ይችላል። «አንድ ሥጋ ይሆኑ ዘንድ ከመፈቀዱ በፊት ወንዱና ሴቷ በዘላቂነት ለመዋደድና ታማኝ ለመሆን ራሳቸውን ኪዳን ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋቸዋል።

3. ለአንድ ሰው ብቻ መሆን፤ 1ቆሮንቶስ 7÷2 እንዲህ ይላል፤ «እያንዳንዱ ሰው የራሱ ሚስት ትኑረው፤ እያንዳንዷም ሴት የራሷ ባል ይኑራት።» ወሲብ መፈጸም ያለበት ከሌላ ሰው ጋር ሳይሆን ከትዳር ጓደኛ ጋር ብቻ ነው፤ አንድ ወንድ አንዲት ሴት፣ አንዲት ሴትም አንድ ወንድ ብቻ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። ከብዙ ሴቶች ጋር መዘሞት ቅምጦችን ማበጀት ወይም ከአንድ በላይ ጋብቻ መፈጸም፣ ይህን ለአንድ ሰው ብቻ የመሆኑን ሥርዓት ያጠፋዋል።

4. ዘላቂነት እንዲኖር ያስፈልጋል፤ ፍች ይህን የዘላቂነት መርሕ ያጠፋል። ሙሴ ፍችን የፈቀደው በዚያን ጊዜ ከነበሩት ሰዎች የልብ ጥንካሬ የተነሣ እንደ ሆነ ጌታ ኢየሱስ ሲናገር፣ ... እንጂ ከመጀመሪያው እንዲህ አልነበረም» ብሏል (ማቴ 19÷8)። ኢየሱስ እንዲህ በማለትም አስጠንቅቆአል፤ «ስለዚህ እግዚአብሔር ያጣመረ ውን ሰው አይለየው» (ማቴ 19÷6)።

5. ሰብቻ መሆን ያስፈልጋል፤ ይስሐቅ ርብቃን ወደ ቤቱ በማምጣት ተገቢውን የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ስለ መፈፀሙ ሲናገር፣ «ይስሐቅም ርብቃን ወደ እናቱ ወደ ሣራ ድንኳን ይዟት ገባ፤ አገባትም» ይላል (ዘፍ 24÷67)። ከብዙዎቹ እንስሳት በተለየ መልኩ በሰዎች መካከል የሚፈጸመው ወሲብ የግል ጉዳይ ነው።

6. ግልጽነት እንዲኖር ያስፈልጋል፤ ዘፍጥረት 2÷25 እንዲህ ይላል፤ «አዳምና ሚስቱ፣ ሁለቱም ዕራቍታቸውን ነበሩ፤ ይሁን እንጂ አይተፋፈሩም ነበር።» ዕራቍትነት አንድን ሰው ለሌላው ሰው ማንነቱን እንዳለ ገልጦ ያሳያል። ወንድና ሴት ወሲባዊ ግንኙነት በማድረግ ራሳቸውን በሚገልጹበት ጊዜ፣ ይህ ሁኔታ ጥቅሙ መልካም ስሜት ለማግኘት ብቻ ሳይሆን፣ ከፍተኛውን ግልጽነትና ግንኙነት እውን ለማድረግ ያስችላል።

7. ራስን መግዛት ያስፈልጋል፤ ጥበበኛው ሰው በማሕልየ መሓልይ እንዲህ በማለት ሦስት ጊዜ ያስጠነቅቃል፤ «ራሱ እስኪፈልግ ድረስ፣ ፍቅርን እንዳታስነሡት ወይም እንዳትቀሰቅሱት (2÷7፤ 3÷5፤ 8÷4)። ወሲባዊ ፍቅር እስከ ጋብቻ ድረስ ማቆየት አስፈላጊ ነው። ፍቅርን ጊዜው ሳይደርስ ወይም ከጋብቻ ውጭ ማነሣሣት ርካሽ ያደርገዋል፤ በጋብቻ ውስጥ የሚገኘውን ደስታ ያስቀራል፤ የእግዚአብሔርንም ትእዛዞች ይጥሳል። በጋብቻ ውስጥ እንኳ ወሲባዊ ግንኙነት መፈጸም ያለበት፣ «በቅድስናና በክብር» ነው (1ተሰ 4÷4)።

8. ፍቅር እንዲኖር ያስፈልጋል፤ ወሲብን መፈጸም የመጨረሻው የፍቅር መገለጫ እንደ ሆነ ተደርጎ ይታያል፤ ለወሲብ የዘመኑ ተመሳሳይ አገላለጽም፣ «ፍቅር መሥራት» ይባላል (መጽሐፈ ምሳ 5÷15-19፤ ማሕልየ መሓልይ 2÷5-6፤ 5÷8፤ 8÷6-7 ይመልከቱ)።

9. ተዘውታሪ እንዲሆን ያስፈልጋል ሐዋርያው ጳውሎስ ባልና ሚስት እርስ በርስ መከላከል እንደሌለባቸው ሲናገር እንዲህ ብሏል፤ «በጸሎት ለመትጋት ተስማምታችሁ ለተወሰነ ጊዜ ካልሆነ በስተቀር፣ እርስ በርሳችሁ

አትከላከሉ፤ ... እንደ ገና አብራችሁ ሁኑ» (1ቆሮንቶስ 7÷5)። በሰዎች መሀከል የሚፈጸመው ወሲብ እንደ እንስሳት ዘር ለማፍራት ብቻ የታቀደ ሳይሆን ፍቅርንና ደስታን ለመግለጽም ነው። ይህም ተዘውትሮ መፈጸም አለበት።

የግል የወሲብን ፍላጎት በጋብቻ ግንኙነት ውስጥ በመግለጽ የሚገኙት ጥቅሞች ምን ምን ናቸው? ወዲያው የሚገኘው ጥቅም ወሲባዊ ግንኙነት በሚፈፀምበት ጊዜ የሚሰጠው ደስታና የውስጥ ርካታ ነው። የረጅም ጊዜ ጥቅሙ ደግሞ፤ በወሲብ የራስን አካል ለሌላው ማካፈሉ ፍቅርን ለማዳበር ክትዳር ጓደኛ ጋር አወንታዊ የሆነ ግንኙነት ለማጠንከር መርዳቱ ነው። ሌላው የወሲብ ጥቅም ልጆች የሚወለዱበት መንገድ መሆኑ ነው። እግዚአብሔር ዕርግዝናና ልጅ መውለድ ጅማሬው በግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲሆን አቅዶአል። ዘር ማፍራቱ ቀጣይነት እንዲኖረው፤ እግዚአብሔር አፈጻጸሙን ደስ በሚያሰኝ መንገድ እንዲሆን ማድረጉ እጅግ የሚያስደንቅ ነው።

ስለዚህ ጋብቻ አንድ ሰው የወሲብ ስሜቱን የሚገልጽበት ዋነኛ ስፍራ ነው። በክርስቲያን የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ውስጥ ቀጥሎ ያለው የተለመደው ጥያቄ ቢጠየቅ አያስገርምም፤ «በቅዱስ ጋብቻ ውስጥ የእግዚአብሔርን ቅዱስ ሥርዓት በማክበር በአንድ ላይ ለመኖር፤ ይህን ሰው (ወይም ይህችን ሴት) የቃል ኪዳን ባልሽ ታደርጊዋለሽን (ወይም የቃል ኪዳን ሚስትህ ታደርጋታለህን)? ሁለታችሁም በሕይወት እስከኖራችሁበት የዕድሜ ዘመን ድረስ ትወጂዋለሽን (ትወዳታለህን)? ታጽናኝዋለሽን (ታጽናናታለህን)? ታከብሪዋለሽን (ታከብራታለህን)? በሕመምና በጤና ጊዜ ትንከባከቢዋለሽን (ትንከባከባታለህን)? ሌሎቹን ሁሉ በመተው አንዳችሁ ለሌላችሁ ራሳችሁ የተጠበቀ እንዲሆን ታደርጋላችሁን? «አዎን አደርጋለሁ» ብሎ መመለስ በወሲባዊ ግንኙነት ያላንዳች ጎፍረት ለመደሰትና የራስንም ፍቅር ለመግለጽ በሚቻልበት ሁኔታ ራስን ውል ውስጥ ማስገባት ማለት ነው።

ቁልፍ ቃላት

- ድንግልና፤ ሳያገቡ በመቆየት ከግብረ ሥጋ ግንኙነት መታቀብ።
- ውል/ኪዳን፤ ራስን ለሌላው አሳልፎ ለመስጠት ዘላቂና የማይሻር ቃል ኪዳን ማድረግ።
- የባልና ሚስት ግንኙነት፤ በጋብቻ ውስጥ የሚፈፀም ወሲባዊ ግንኙነት ነው።
- መስማማት፤ ውል ማድረግ።
- የግል መሆን፤ በአንድ ሰው መወሰን።
- የጠበቀ ወዳጅነት፤ ሁለት ሰዎች በጣም በመቀራረብና በመዋደድ የሚፈጥሩት ሐሜት የሚያስገኝ ግንኙነት ነው። የጠበቀ ወዳጅነት የመጨረሻው ከፍተኛ መገለጫው ወሲብ መፈጸም ነው።
- ጋብቻ፤ የወንድና የሴት ዘላቂ የሆነ ጥምረት ነው፤ ይህም ጥብቅ ግንኙነት በፍቅርና በታማኝነት በአንድ ላይ እንዲኖሩ የሚያበቃ ነው።
- ብስለት፤ ከጉልምስና ደረጃ ላይ መድረስ ማለት ነው። ይህም አንድ ሰው በአካል ጥንካሬው፤ በሥነ ልቦናውና በውስጣዊ ስሜቱ ሙሉ በሙሉ ማደጉን ያመለክታል።
- ግልጽነት፤ ድብቅ ነገር ሳይኖር ሁሉንም ቊልጭ አድርጎ መግለጥ።
- ዘላቂነት፤ ሳይለወጥ ለብዙ ዘመን የሚቆይ ወይም የሚኖር።
- ለብቻ መሆን፤ ከሌሎቹ ሁሉ ተገልሎና ርቆ መቀመጥ፤ በቅርብ ሌሎች ሰዎች እንደሌሉ ያመለክታል።
- ዘር ማፍራት፤ ሌላ ፍጡር ወደ ዓለም የሚመጣበት የመፀነስ፤ የዕርግዝናና ልጅ የመውለድ ሂደት ነው።
- ጎላፊነት፤ አስተማማኝነትን፤ ታማኝነትንና ተጠያቂነትን ያካትታል። አስተዋይነት

የተሞላበትን ውሳኔ የሚወስን ጎላፊነት የሚሰማው ሰው ነው።

- ራስን መግዛት፤ እንግዳ ደራሽ ስሜትን፣ ፍላጎትንና ጥልቅ ስሜትን የመቈጣጠር ችሎታ ነው።
- መታመን፤ በሌላ ሰው ባሕርይ ችሎታና እውነተኛነት እምነት ማድረግና ሙሉ ሐሳብን መጣል።

III. የትምህርት ዝግጅት መርጃ መሣሪያዎች

ትምህርቱን ለማስተዋወቅ የቀረቡ ሐሳቦች

1. አንድ ተማሪ ማሕልየ መሓልይ 7÷1-9 በአዲሱ መደበኛ ትርጒም እንዲያነብ አድርግ። በክፍል ውስጥ የማፈር ሁኔታ መፈጠሩ፣ ሊሆን የሚችል ነገር ነው። ተማሪው ሁሉንም እንዲያነብ ልትፈቅድ ትችላለህ ወይም በምንባቡ መካከል ላይ እንዲያቆም ታደርገዋለህ። መሸጋገሪያ ሐሳብ፡- *እንዲህ ያለውን ምንባብ ድምፅህን ከፍ አድርገህ በማንበብህ ጎፍረት ይሰማሃልን? ለምን ጎፍረት ይሰማናል፤ ምክንያቱም ይህ ምንባብ በወንድና በሴት መካከል ያለውን በጣም የጠበቀ ግንኙነት ይገልጻል። ስለዚህ ጕዳይ ስንናገር በመጠኑም ቢሆን ጎፍረት የሚሰማን ቢሆንም እንኳ፣ በማሕልየ መሓልይ ያሉት የትዳር ጓደኛሞች ያደርጉት እንደነበረው ሁሉ፣ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ተገቢ ሁኔታ ፍቅራችንን በአግባቡ መግለጹ፣ እግዚአብሔር ከሰጠን አስደናቂ ስጦታዎች ውስጥ አንዱ ነው። ዛሬ የምንነጋገርበት ጕዳይም ይህ ነው።*
2. የቴፕ ማጫወቻውንና ዓለማዊ ሙዚቃ ያለበት የቴፕ ክር ወደ ክፍሉ ይዘህ ግባ። አንድ የፍቅር ዘፈን ለክፍሉ እንዲሰማ አድርግ። ተማሪዎች በዘፈኑ ውስጥ የሚገኙትን የግጥም ቃላት ይረዷቸው ዘንድ የዘፈኑን ግጥሞች በጥቁር ሰሌዳው ላይ መጻፍህን ርግጠኛ ሁን አስተማሪው ይህንን ክፍል ከማስተማሩ በፊት ሙሉ ሐሳቡን ለመረዳት ከገጽ 27-31 ቢያነብ መልካም ነው። መሸጋገሪያ ሐሳብ፡- *እንዲህ ያለውን ሙዚቃ በየቀኑ እንሰማለን ማለት ይቻላል። ሁሉም ሰው ፍቅርንና የጠበቀ ወዳጅነትን ለማግኘት ይፈልጋል። ዛሬ ስለ ፍቅርና ስለ ተገቢው የፍቅር መግለጫ እግዚአብሔር ምን እንደሚያስብ እንወያያለን።* ትምህርቱን ለመቀጠል፣ የትምህርት አቀራረብ ዘዴን ቊጥር 2 ተመልከት።
3. ነባራዊ ሁኔታ፡- «በረከትና ሂሩት በአንድ ትምህርት ቤት ሁለቱም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ነበሩ። በረከት በጣም የታወቀ ተማሪ ነበር፤ እርሱን የማታውቅ ወይም የማትወድ ልጃገረድ አልነበረችም ማለት ይቻላል። እርሱም ልጃገረዶችን ይወድ ነበር። ይሁን እንጂ ሂሩት በበረከት ልብ ውስጥ የተለየ ስፍራ ነበራት። ሁልጊዜ ጊዜውን ከእርሷ ጋር ለማሳለፍ ይፈልግ ነበር። አንድ ነገር በበረከት ልብ ውስጥ ተቀጣጥሎ ወደ ሂሩት ተሻገረ። ሂሩት ይህን ታውቃለች፤ እርሷም በተመሳሳይ ሁኔታ በበረከት ተማርካ ነበር።» መሸጋገሪያ ሐሳብ፡- ጥያቄ ጠይቅ፡- *በበረከት ቦታ ብትሆኑ ኖሮ እንደዚህ ያለው ስሜት ሲሰማችሁ ምን ታደርጉ ነበር? በሂሩት ቦታ ብትሆኑ ኖሮስ ምን ታደርጉ ነበር? የማታደርጉት ነገር ምንድን ነው? በምን ምክንያት? ዛሬ ክርስቲያኖች የወሲብ ፍላጎታቸውን በአግባቡ እንዴት መግለጽ እንዳለባቸው በትኵረት እናያለን።*

ትምህርቱን ለማቅረብ የሚጠቅሙ አማራጭ ዘዴዎች

1. ትንታኔያዊ ዘዴ፤ በትምህርቱ ላይ እንዲቀርብ የተመለከተውን እያንዳንዱን ክፍል አንብብ፤ ስለ ምንባቡም አጭር ማብራሪያ ስጥ። በተለይ በማሕልየ መሓልይ 2፥7፤ 3፥5 እና 8፥4 አጽንዖት አድርግ። አስተዋፅኦውንና ዕጥርታውንም ልብ በል። ሌላ ተማሪ እያንዳንዱን ጥቅስ እንዲያነብ አድርግ። እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ አንድን ነገር ደጋግሞ ሲገልጽ፤ አጽንዖት እያደረገበት መሆኑን በትኩረት አመልክት። በ8፥6-7 ላይ እንደ ቀረበው ፈጥኖ ፍቅርን ከመቀስቀስ መታቀብ ለምን አስፈላጊ እንድ ሆነ ምክንያቶቹን ልብ በል። ፍቅር እንደ ሞት ብርቱ ነው፤ እንደሚንበገበግም እሳት ነው፤ በዓለም ውስጥ ደግሞ እጅግ ክቡር ነገር ወጣቶች ከጋብቻ በፊት ከወሲብ መታቀብ እንዳለባቸው ለማስጠንቀቅ ይህን ክፍል በሚገባ ተጠቀምበት።

2. ሙዚቃዊ ዘዴ፤ የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፦ ቴፕ እንዲሁም ዓለማዊ ዘፈን ያለባቸው የቴፕ ክሮች። የተምህርት አቀራረብ ዘዴ ቍጥር 2 ተመልከት። የፍቅር ሙዚቃውን ካዳመጡ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለተማሪዎች አቅርብላቸው፦

   - የዚህ የፍቅር ዘፈን ዋና መልእክት ምንድን ነው?
   - የታወቁ የፍቅር ዘፈኖች፤ አንዳንድ የጋራ መልእክቶች ምን ምን ናቸው?
   - እነዚህ መልእክቶች እውነት ናቸውን? መልሱ አዎን ከሆነ በምን ምክንያት? ያልሆነው በምን ምክንያት ነው?
   - እነዚህ ዘፈኖች ታዋቂ ሊሆኑ የቻሉት በምን ምክንያት ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

   (መምህር፦ ብዙ የፍቅር ዘፈኖች ሰዎች ፍቅር ለማግኘትና የጠበቀ ወዳጅነት ለማበጀት ያላቸውን ፍላጎት የሚንጸባረቁ መሆናቸውን ይረዱ ዘንድ ተማሪዎችን አግዛቸው፤ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች እስከ ጋብቻ ድረስ ወሲብን ከመፈጸም ለመታቀብ ፈቃደኞች አይደሉም። ከዚህም የተነሣ ግንኙነታቸው በቀላሉ ይቋረጣል ይህም በአጭሩ ስለ ቀረ ፍቅር በሚያዜሙ ዘፈኖች ላይ ተንጸባርቆ ይገኛል። የሰው ወሲባዊ ግንኙነት በተመለከተ የእግዚአብሔር ዕቅድ ምን መሆን እንዳለበት፤ ለክፍሉ ለማሳየት፤ በዕጥርታው ውስጥ ያለውን ሐሳብ አቅርብ)።

3. ጥያቄያዊና መልሳዊ ዘዴ፤ ጠይቅ፦

   - በዘፍጥረት 2፥24 ላይ «ሰው ... ከሚስቱ ጋር ይጣመራል» ሲል ምን ማለት ነው?
   - ሰው ከሚስቱ ጋር ከመጣመሩ በፊት (ከአባቱና ከእናቱ ተለይቶ) አስቀድሞ የሚጠየቀው ነገር ምንድን ነው?
   - የማሕልየ ማሓልይ ዋና ሐሳብ ምንድን ነው?
   - በ2፥7፤ በ3፥5 እና በ8፥4 ላይ የማሕልየ መሓልይ ጸሓፊ የሚያስጠነቅቀው ስለ ምን ጉዳይ ነው?
   - በማሕልየ መሓልይ 8፥6-7 መሠረት አንድ ሰው ስለ ፍቅር ከሚጠነቀቅባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዳንዶቹ ምን ምን ናቸው?
   - ጳውሎስ በ1ቆሮንቶስ 7፥2 መሠረት ሰዎች መጋባት አለባቸው ያለበት አንድ ምክንያት ምንድን ነው?
   - በ1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 7 መሠረት ሳያገቡ ስለ መኖር የጳውሎስ አስተያየት ምንድን ነው?
   - ባል ስለ ሚስቱ አካል ባለው አስተሳሰብና ሚስትም ስለ ባሏ አካል ባላት አመለካከት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

- ባል ሚስቱ ከእርሱ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ለመፈጸም ቢከለክል፣ ሚስትም ባሏ ከእርሷ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት እንዳይፈጽም ብታደርግ ይህን ሁኔታ ተከትለው ከሚመጡት ውጤቶች አንዱ ምንድን ነው?
- ለው ጸታ ያለው በመሆኑ ከሚያገኛቸው ጥቅሞች አንዳንዶቹ ምን ምን ናቸው?
- አንዳንድ ሰዎች ከጋብቻ በፊትና ከጋብቻ ውጭ ወሲብ ለመፈጸም የሚፈልጉት በምን ምክንያት ነው?
- ወጣቶች ከጋብቻ በፊት ያለውን የወሲብ ፍላጎት እንዴት ማሸነፍ ይችላሉ?

4. *ታሪካዊ ዘዴ፣* «የላቪንግ ሱቬታንና የሪስፖንሲብል ሪቻርድ» ታሪክን ወይም «የሴቨን ካው ዋይፍ» ታሪክን አንብበህ ከታሪኩ መጨረሻ ላይ ያሉትን ጥያቄዎች በመጠቀም ውይይቱን ምራ።

ናሙና የክፍል ሥራዎች

1. ክፍሉን ለሁለት ቡድን ክፈለው፤ ዘፍጥረት 2÷24፤ 24÷67 እና ማሕልየ መሓልይን 2÷7፤ 3÷5፤ 8÷4፡6-7 ለአንድ ቡድን ስጥ። 1ቆሮ 7÷1-7 ደግሞ ለሌላ ቡድን ስጥ። እያንዳንዱ ቡድን የሚከተሉትን እንዲያከናውን *መመሪያ* ስጥ፡-
   - በምንባቡ ውስጥ የተገለጹትን ተገቢ ወሲባዊ *መገለጫዎች* እንዲዘረዝር፤
   - በምንባቡ ውስጥ ላሉት ተገቢ ወሲባዊ *መገለጫዎች* የሚገኙ ጥቅሞች ምን ምን እንደ ሆኑ እንዲዘረዝር፤
   - አንድ ሰው የወሲብ ፍላጎቱ የሚገልጥበት ብቸኛ ተገቢ ስፍራ ጋብቻ የሆነበት ምክንያት እንዲያቀርብ፤
2. ይህን ሐረግ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ጻፍ፡- *«ራሱ አስኪፈልግ ድረስ፣ ፍቅርን እንዳታስነሡት ወይም እንዳትቀሰቅሱት»* የሚለውን እንዲያስቡና ከዚህ በታች ያሉትን *መልመጃዎች* በቃል እንዲሠሩ *መመሪያ* ስጣቸው፡-
   - ዐረፍተ ነገሩን በራሳችሁ አባባል ግለጹ፤
   - ዐረፍተ ነገሩን *ሙሉ* አድርጉ። *«ራሱ አስኪፈልግ ድረስ ፍቅርን እንዳታስነሡት ወይም እንዳትቀሰቅሱት፤ ምክንያቱም ...*
   - ተገቢው ጊዜ አስኪደርስ ድረስ ፍቅርን ያለማስነሣቱ ጥቅሙ ምን እንደ ሆነ ዘርዝር፤
   - የፍቅርን መቀስቀሻ መንገዶችን ግለጹ።
3. የጋብቻን ፎቶግራፍ ከፍ አድርገህ በመያዝ የጋብቻ ዓላማ ምን እንደ ሆነ የክፍሉን ሐሳብ ጠይቅ። በዚህ ትምህርት ላይ የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ሁሉ ክፍሉ እንዲያነብ በማድረግ «የጋብቻ» ትርጒም ምን እንደ ሆነ ተማሪዎቹ እንዲጽፉ አዘዝ። ከዚያም ፈቃደኛ የሆኑ ተማሪዎች የጻፉትን ለክፍሉ እንዲያነቡ አድርግ።
4. ተማሪዎች ያስቡበት ዘንድ የሚከተለውን ጥያቄ ጠይቅ፤ **«ከመጋባታችሁ በፊት ወሲብ ስለ መፈጸም ያላችሁ ውሳኔ ምንድን ነው?»** ለተማሪዎቹ እንዲህ ብለህ ንገራቸው፤ «ከጋብቻ በፊት ወሲብ ስለ መፈጸም ወይም ስለመፈጸም ምርጫ ማድረግ ይኖርብሃል፤ ምርጫ የምታደርገው ሰው አንተ ነህ።» ከዚያም የወሰኑትን ውሳኔ ለወደፊት ባላቸው ወይም ሚስታቸው እንዲጽፉ አድርግ። የደብዳቤው *የመጀመሪያ መሥመር* እንዲህ ማለት አለበት፡-

   «ከዛሬ ጀምሮ ... (ቀን) ... ወስኛለሁ።»

   (ለመምህሩ ማስታወሻ፡- ተማሪዎቹ በደብተራቸው ላይ ከሚጽፉ ይልቅ፤ የሚጽፉበትን ወረቀት እንዲሰጣቸው፤ የጻፉትንም ደብዳቤ ለራሳቸው እንዲያስቀሩ ማድረግ፤ ደብዳቤያቸውንም የማታነብ መሆንህን ለተማሪዎቹ መንገር አስፈላጊ ነው።)

Loving Lovetta and Responsible Richard (by Nuwoe - James Kiamu)

(ይህ ታሪክ ተማሪዎች አንድን ሰው መልካም ባል ወይም አንዲትን ሴት መልካም ሚስት የሚያደርጓት በጎ ነገሮች ምን እንደ ሆኑ ያስቡ ዘንድ ይረዳቸዋል። ትክክለኛው ጊዜ እስኪደርስ ድረስ ጋብቻ ሳይፈጽሙ መቆየት አስፈላጊ መሆኑን እንዲገነዘቡም ማድረግ)።

«መዓዛ፣ በጭንቅላቴ ልወድቅ የደረሰኩ ይመስለኛልና እባክሽ እርጅኝ» በማለት ስንዱ ለዩኒቨርስቲ የክፍል ጓደኛዋ በጆሮዋ ሹክ አለቻት።

«አንቺ ልጅ ምን ነካሽ» በማለት መዓዛ ጠየቀች። ስንዱ ደስ ብሏት ወደ ጓደኛዋ ተመለከተች። ዐይኖቿ እንደ ውቅያኖስ ፈጠጡ።

«ዛሬ ጧት ረታ የነገረኝን ማመን አልቻልኩም» በማለት ስንዱ ለመግለጽ ሞከረች። «ወደ እኔ አተኩሮ ተመለከተ፤ እጄን ጠበቅ አድርጎ በመያዝም፣ 'አፈቅርሻለሁ!'» አለ።

«መዓዛ፣ መች ይህ ብቻ ረታ እኔን የሚያፈቅር መሆኑን ብቻ ሳይሆን፣ የዩኒቨርስቲ ትምህርታችንን ስንጨርስ ልንጋባ እንደሚፈልግም ነገረኝ።

መዓዛም፣ «እንግዲህ ስንዱ እኔ ስለ ረታ ብዙ የማውቀው ነገር የለም» በማለት ገለጸች። እርሷም «ይሁን እንጂ» በማለት ቀጠለች፤ «ከሁኔታው እንደሚታይ ጥሩ ወጣት ልጅ ይመስለኛል፤ ጨዋ፣ ትሑትና በሌሎች ተማሪዎች የተከበረ ልጅ ነው። ለእግዚአብሔር ክልብ የሆነ ፍቅር ያለው ይመስላል። ጎላፊነት የሚሰማው ጉብል ስለሚመስል ጥሩ ምርጫ ነው እላለሁ።»

«በጣም ትክክል ነሽ በማለት ስንዱ ተስማማች። «ልጃገረዶችን የሚያባልግና የሚያ ዋርድ ሰው አይደለም። በተወያየንባቸው ጉዳዮች የእኔን ሐሳብ የሚያከብርና፣ እኔ የተሰየሁ ሰው አድርጐ የሚያስብ መሆኑን ተረድቻለሁ፤ እኔም እወደዋለሁ፤ በተቻለ መጠን በቅርብ ጊዜ ውስጥ ላገባው እፈልጋለሁ።»

«ወዳጄ ሆይ፤ ረጋ በይ» በማለት መዓዛ ጓደኛዋን አሳሰበቻት። በመቀጠልም፣ «እናቴ ዘወትር እንደምትነግረኝ ወንዶች ምንጊዜም ወንዶች ናቸው። ዛሬ አንችን በጋለ ስሜት ሊወዱሽ ይችላሉ፤ ይሁን እንጂ በዚያ በጋለ ፍቅራቸው መቆየት አለመቆየታቸውን ለመገንዘብ እስከ ነገ መታገሡ የተሻለ አማራጭ ነው። ረታ እወድሻለሁ እንደሚለው የሚወድሽ ከሆነ፣ የአንችን ማንነት ያከብራል፤ ደስ የማይልሽን ነገር እንድትፈጽሚ አይጠይቅሽም። እንደሚታ ወቀው ረታ ጎላፊነት የሚሰማው ልጅ ነው። ሌላው ቢቀር ለራሱ ጥሩ ሚስት የሚፈልግ ሰው ነው፤ እናም ራሱን ለዚያ ጠብቆአል ብዬ በእውነት አምናለሁ። በርግጥ ልታገቢው የምትፈልጊው ዐይነት ሰው ነው።»

«ለእኔ ትክክለኛው ሰው እርሱ መሆኑን በማሰብሽ ደስ ብሎኛል፤ ጥሩ ባልና አባት እንደሚሆን ዐውቃለሁ» በማለት ስንዱ መለሰች።

ልጃገረዶቹ «ደኅና ሁኝ፤ ደኅና ሁኝ» ተባብለው ከተሰነባበቱ በኋላ በየፊናቸው ሄዱ። ስንዱ በመጀመሪያው የፍቅር መነቃቂያ ደረጃ ላይ ተቀጣጠሰች።

በእነዚህ ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፦

- ስንዱ ረታን እንድትወደው ያደረጋት ነገር ምንድን ነው?
- ሴቶች በመልካም ባል ላይ እንዲታዩ የሚፈልጓቸው በጎ ነገሮች ምን ይመስ ሏቸዋል?
- ረታ በስንዱ ማንነት ተማርኮ ነበር ብላችሁ የምታስቡት በምን ምክንያት ነው?
- አድን ቀን መልካም ባል ወይም መልካም ሚስት የሚያደርጓችሁን በጎ ነገሮች አሁን እንዴት ማዳበር ትችላላችሁ?
- መዓዛ ለስንዱ የመከረቻት ምክር ምን ነበር? አስተዋይ ልጅ ትመስላችኋለችን? በምን ምክንያት? አስተዋይ ካልሆነችስ ለምን?

- አንድን ሰው፤ «አገባዋለሁ» ወይም «አላገባውም» ብላችሁ ከመወሰናችሁ በፊት ሰፊ ጊዜ ወስዶ ማየቱ ጥቅሙ ምንድን ነው? [ከጸሓፊው በተገኘ ፈቃድ አገልግሎት ላይ የዋለ]።

The Seven Cow Wife
(from Manual for Teachers of Christian Religious Knowledge in Senior Seccondary
Schools SS1, p. 260

(ይህ ታሪክ በባልና በሚሰት መሀከል ያለ ፍቅር የቱን ያህል ዋጋ እንዳለው ያሳያል።)

አንድ ቀን አንድ መንገደኛ በአንድ መንደር ውስጥ ሊያልፍ እጅግ ቆንጆ ሴት አየ፤ በሕይወቱ ዘመን እንደ እርሷ ያለች ቆንጆ ሴት ከቶ አይቶ አያውቅም። ሴትዮዋ በመንገድ ስታልፍ ፍዝዝ ብሎ ቆሞ ተመለከታት፤ በመጨረሻም አንድ ሽማግሌ ሰው አገኘና፤ «ስለዚህች ቆንጆ ሴት ይንገሩኝ! ማን ናት! ከየት ነው የመጣችው? በማለት ይጠይቃቸዋል።

ሽማግሌው ሰው እንዲህ በማለት ገለጹ፤ «በእኛ ጎብረተ ሰብ የጋብቻ ሥርዓት አንድ ላም ወይም ላሞች በማጫ መልክ ይሰጣሉ። መለስተኛ ውበት ላላት ልጃገረድ ብዙ ጊዜ ለማጫ የሚሰጠው ሁለት ላሞችን ነው። እጅግ በጣም ቆንጆ የሆኑ ልጃገረዶች ያሉት አባት ሴት ልጁን ሲሰጥ ዐልፎ ዐልፎ ሦስት ላሞች ይሰጡታል።» ከዚያም ሽማግሌው የሚከተለውን ታሪክ ለመንገደኛው መናገር ጀመሩ።

የዛሬ ዐሥር ዓመት ገደማ አንድ ወጣት በአንዲት ልጃገረድ ፍቅር ተጠምዶ ሊያገባት ፈለገ። ልጅቷ ያን ያህል የሚማርክ ቁንጅና አልነበራትም፤ ይሁን እንጂ በጣም ወደዳት።

ይህ ወጣት ስለ ጋብቻው ስምምነት ላይ ለመድረስ ወደ አባቷ ሄዶ፤ «ምን ያህል ላሞች ይፈልጋሉ?» በማለት ጠየቀ።

«ባህሉን ታውቃለህ» አሉ የልጅቱ አባት። «ልጄ ቆንጆ አለመሆኗን ስለማውቅ፤ ከአንድ ላም በላይ አልጠይቅም።»

ወጣቱም፤ «እንደሚመስለኝ በጣም ቆንጆ ልጅ ናት!» በማለት አድንቆ ተናገረ። «እርሷን ለማግኘት ሰባት ላሞች አሰጥዎታለሁ።»

አባትየው አፋቸውን ከፈቱ፤ ይህን ልዩ ወጣት ሰውም በትኩረት ተመለከቱት። ዕብድ ትመስለኛለህ፤ እውነቴን እኮ ነው፤ የጠየቅሁህ አንዲት ላም ብቻ ነው፤ አንተ ግን ሰባት ላሞች አሰጥሃለሁ ትላለህ!»

እውነቴን ነው» አለ ወጣቱ፤ ሴት ልጅዎ በጣም እወዳታለሁ፤ ለማጫ ደግሞ ሰባት ላሞች ልሰጥዎት እፈልጋሁ።»

አባትየው በጣም እየሣቁ፤ «አንተ ወጣት ይህን ያህል ውበት ለሌላት ልጄ ሰባት ላሞች ልትሰጠኝ ከፈለግህ፤ እቀበልሃለሁ» አሉ።

ስለዚህ የጋብቻው ድግስ ተጀመረ። የወጣቱ ባልንጀሮች ስለ ከፈለው ማጫ ሲሰሙ እየተፈራረቁ እንዲህ በማለት አፌዙበት፤ «ዕብድ ነህ፤ ለዚያች ርባና ለሌላት ልጃገረድ ሰባት ላሞች እንዴት ትሰጣለህ? በጣም ቆንጆ አይደለችም!»

ወሬው በመንደሩ ሁሉ ተዳረሰ፤ ወጣቱ በሄደበት ሁሉ ዘመዶቹ ጣታቸውን ወደ እርሱ እየቀሰሩ፤ «ሰባት ላሞች የሰጠው ቂል ይኸውላችሁ መጣ!» እያሉ ይሥቁበታል። ትናንሽ ልጆች እንኳ ሳይቀሩ ከጀርባው ሆነው ያፌዙበት ነበር።

ይሁን እንጂ ወጣቱ ባደረገው ነገር ከቶ ሐዘን አልተሰማውም፤ ወይም በሰጠው ማጫ አልተጸጸተም። የጋብቻው ሥርዓት የሚፈጸም በት ጊዜ ደረሰ፤ ላሞቹም ለአባትየው ተሰጡ፤ ሙሽራዋም ለሙሽራው ተሰጠች። ሙሽሪት በማፈር ፊቷ ቢቀላም በባሏ ዐይኖች ላይ ለእርሷ ያለውን ፍቅር ስታነብም የፊቷ ፍካት እየጨመረ ሄደ።

አንድ ቀን ሙሽሪት ባሏን «ሰባት ላሞችን ለእኔ ስትል ለምን ከፈልክ?» በማለት ጠየቀችው። «በመንደራችን ታሪክ ውስጥ ማንም እነዚህን ያህል ብዙ ላሞች ለማጫ የከፈለ ሰው

የለም፤ ለዚያውም ደግሞ እኔ ቄንጆ አይደለሁም።»

ባሏ ሣቅ ብሎ፣ «ለእኔ ከሰባት ላሞች ዋጋ ትበልጭብኛለሽ» አለ።

ስለዚህ ሙሽሪት ባሏ የተናገረውን ቃልና ተግባሩን ማሰላሰል ጀመረች። ስለ ፍቅሩ እያሰበች በሄደች ቊጥር፣ ይበልጥ እየወደደችው ሄደች፤ እርሷም በፍቅሩ እየደመቀች መጣች። በመንደሩ ሁሉ የታወቁ እጅግ ደስተኛ ፍቅረኛሞች ሆኑ።

ሙሽሪትም ባሏ የሚወደውን ምግብ ለማዘጋጀት በትጋት ትሠራ ነበር፤ እርሱም ርኅራኄና ፍቅር በተሞላ ቃል ያነጋግራት ነበር። እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ሲሥቁና ሲጫወቱ ጉረቤቶቻቸው ይሰሟቸው ነበር።

ብዙም ሳይቆይ የመንደሩ ሰዎች ሙሽሪት እያደር ውበትዋ እየጨመረ መሄዱን አስተዋሉ። ሰባት ላሞች የተሰጠላት ሚስት ናት፤ በጣም ተወደደች። የዚያ ፍቅር ግንዛቤም የተደበቀውን ውበት ይፋ አወጣው። ባሏ፣ «አንች ለእኔ ከምንም ነገር ትበልጭብኛለሽ» በማለት በየጧቱ ይነግራት ነበር። ያገኘችው ደስታና ፍቅርም በየቀኑ ይበልጥ ቄንጆ እንድትሆን አደረጋት።

«ያየኻት ያች ሴት እርሷ ናት» በማለት ሽማግሌው ለመንገደኛው ተናገሩ። «እርሷ ሰባት ላሞች የተከፈለላት ሚስት ናት፤ እስከ አሁን ድረስ እንደ እርሷ ያለ ቆንጆ ሴት ታይቶ አይታወቅም»

በእነዚህ ጥያቄዎች ተወያዩ፡-

- በዚህ ታሪክ ውስጥ የሴቷን ዋጋ የወሰነ ማን ነው?
- ሴቲቱ በአባቷ ዐይን ስትታይ፣ በመንደሯ ሰዎች ዐይን ስትታይ፣ በአገባት ሰው ዐይን ስትታይ፣ ሰባት ላሞች የሚሰጥላት ነበረችን?
- የሰውየው ፍቅር በሙሽሪት ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ አሳደረ?
- ሰውየው ለሚስቱ እንዲት ላም ብቻ ቢከፍል ኖሮ ታሪኩ ምን ያህል የተሰየ ይሆን ነበር?

(መምህር፡- ፍቅርና የጠበቀ ግንኙነት በጣም ውድ መሆናቸውንና በርካሽ ዋጋ የማይገኙ መሆናቸውን ይገነዘቡ ዘንድ ተማሪዎችን አግዛቸው። ሰውየው ለሙሽራዪቱ ከፍተኛ ዋጋ ከፈለ፤ ከዚህ በላይ ደግሞ በተቻለው መጠን ሚስቱን ወደዳት፤ ተንከባከባትም፤ እርሷም ለገለጸላት ፍቅር አጸፋውን መለሰች፤ ጋብቻቸውን ስኬታማ ያደረገውም ይኸው ነው። አንድ ወንድ ወይም አንዲትን ሴት ለመውደድ ራስህን ለዚያ ሰው ብቻ መጠበቅ ደስታንና የልብ መሻትን ለማግኘት የእግዚአብሔር ዕቅድ ነው።)

ተማሪዎች ሊሠሩት የሚገባ ሥራ

1. ከማሕልይ መሓልይ ቢያንስ ሁለት ምዕራፍ አንብቡና ፍቅረኛሞች እርስ በርስ ያላቸውን ፍቅር የገለጹበትን መንገድ ጻፉ።
2. በወላጆቹ ጋብቻ ውስጥ እያንዳንዱ ተማሪ በማግኘት ላይ ያለውን ደስታ መዘርዘር አለበት።
3. ባለ ሦስት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ፤ በመጀመሪያው አንቀጽ ላይ አንድ ባል ወይም ሚስት ሊኖረው (ሊኖራት) ይገባል የምትሉትን መልካም ነገር ግለጹ፤ በሁለተኛው አንቀጽ ላይ የትዳር ጓደኛችሁ ከእናንተ ዘንድ የሚጠብቀውን (የምትጠብቀውን) መልካም ነገርን ግለጹ፤ በሦስተኛው አንቀጽ ላይ ደግሞ መልካም ባል ወይም መልካም ሚስት ለመሆን ራሳችሁን የምታዘጋጁበትን መንገድ ግለጹ።

4. ከፍቅር አንጻር የእግዚአብሔር ዕቅድ ምን እንደ ሆነና እስከ ጋብቻ ድረስ ወሲብ ከመፈጸም መታቀብ ምን ጥቅም እንዳለው በመግለጽ፣ የፍቅር ግጥም፣ ቅኔ ወይም አጭር ልብ ወለድ ታሪክ ጻፉ፤ ግጥሙን በትወና አሳዩ፤ ወይም ግጥሙን አለዚያም አጭር ልብ ወለዱን ለክፍሉ አንብቡ።

5. በማኅበረ ሰባችሁ ውስጥ ደስተኛ የቤተ ሰብ ሕይወት አላቸው የምትሏቸውን አስቡ። በትዳር ውስጥ ሲኖሩ የደስታቸው ምንጭ ምን እንደ ሆነ ሰውየውን (ሴትዮዋን) ጠይቁ። የጠየቃችሁት ሰው ለደስታው ዋና ምክንያት ነው ብሎ የነገራችሁና በሰውየው ወይም ከሴትዮዋ ላይ አድናቆት ያሳደረባችሁን ነገር ጻፉ።

6. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታሪካቸው ከተገለጸው ሰዎች መካከል ለእግዚአብሔር ሕግ ታማኝ ነበር ስለምትሉት ሰው አስቡ፤ ይህ ሰው ታማኝ ሆኖ በመገኘቱ እግዚአብሔር እንዴት እንደ ባረከው አሳዩ፤ ሕይወታችሁ ከዚያ ለይታችሁ ካመለከታችሁት ሰው ሁኔታ ጋር እንዴት ይነጻጸራል?

7. ከምታውቁት የፍቅር ግጥም አንዱን በመቅዳት በግጥሙ ውስጥ ካለው ሐሳብ ጋር የምትስማሙ ወይም የማትስማሙ መሆናችሁን በመግለጽ አንድ አንቀጽ ጻፉ።

ተማሪዎች የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች - ለእነዚህም የተሰጡ መልሶች

1. በዘፍጥረት 2÷24 ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ባልና ሚስት «አንድ ሥጋ ይሆናሉ» ሲል ምን ማለቱ ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ ጋብቻ ምን እንደ ሆነ ሲናገር አንድ ወንድና አንዲት ሴት እርስ በርስ የሚጣመሩ መሆናቸውን ይገልጻል። ሁለቱን አካላት አንድ የሚያደርግ ማሰሪያ ያስፈልጋል። ማስተሳሰሪያው ብርቱ ሲሆን ኅብረቱም ጠንካራ ይሆናል፤ ብሎም ጋብቻው ስኬታማ ይሆናል። በሌላ በኩል ግን ማስተሳሰሪያው ልል ሲሆን፣ ኅብረቱ ደካማ ይሆናል፤ ከዚህም የተነሣ ጋብቻው ያን ያህል ስኬታማ አይሆንም። የዚህን የኅብረትና የመተሳሰር ጉዳይ በሚገባ መረዳት አስፈላጊ ነው። ኅብረት ከመደመር ጋር አንድ አይደለም። አፍሪካዊው የጋብቻ ዕንስ ሐሳብ ብዙ ጊዜ በመጨመር መርሕ ላይ የተመሠረተ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት ሙሽራው ወደ ቤተ ሰቡ ለተጨመረችው ሙሽራ ጥሎሽ ስለሚከፍል ነው። ይህ መርሕ በግልጽ እንደሚታየው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ጋብቻን የሚመለከተው አንድ ከመሆን (ኅብረት ከማድረግ) መርሕ አንፃር እንጂ ከመጨመር መርሕ አንጻር አይደለም። ከዚህም በላይ አንድ ሲደመር አንድ የሚያስገኘው ውጤት ሁለት ብቻ ነው። ኅብረት ማድረግ ግን አንድ ጠርሙስ ኮካ ኮላን ወደ አንድ ጠርሙስ ፋንታ በመጨመር ኮካ ፋንታ ብለን ልንጠራው የምንችለውን አዲስ መጠጥ ማግኘት ማለት ነው። ከዚህ በኋላ ሁለቱን ለስላሳ መጠጦች ወደ መጀመሪያው መልካቸው ለመመለስ ልንለያቸው አንችልም፤ ምክንያቱም አንድ ሆነዋል። አንድ ከአንድ ጋር ሲደባለቅ ውጤቱ ሁለት ሳይሆን አንድ ነው። በክርስቲያን ጋብቻ ውስጥ ያለው እውነት ይህ ነው። እግዚአብሔር ባቀደላቸው መሠረት የሚጓዙ ቤተ ሰቦች ለማግኘት ከፈለግን ዛሬ ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሕ የጋብቻ መርሕ አድርገን መቀበል ይኖርብናል። *(from Nigerian Covenant Study Guide).*

2. አንድ ወንድ ዘወትር ወሲብ ካልፈጸመ ደካማ ወይም ታማሚ ይሆናል የሚለው አነጋገር እውነት ነውን? ወንዶች ወሲብ ካልፈጸሙ በስሜት ወይም በአካል ረገድ በሚገባ አያድጉም የሚባለው እውነት ነውን?

እንደዚህ ያለው አነጋገር ከቶ እውነት አይደለም። ይህ በብዙ ወጣቶች ዘንድ በጣም ጉጂ የሆነ ሐሳብ ነው። እውነቱ የዚህ ተቃራኒ

የሆነው ነው። ከጋብቻ በፊት ወሲብን ከመፈፀም የታቀቡ ወጣት ወንዶችና ወጣት ሴቶች፣ ከሴሰኞች ባልንጀሮቻቸው ይልቅ በዩኒቨርስቲ ትምህርታቸው ፈጣን መሻሻልና ዕድገት የሚሳዩ ናቸው፤ ብዙ ወጣት ወንዶች በዚህ ጉዳይ ላይ መሠረተ ቢስ በሆነ ፍርሃት የተያዙ ናቸው። ይህ ከወሲብ ጋር የተያያዘ ራስ ወዳድ የሆነ ሐሳብ ነው። ለጤናችን መጥፎ ቢሆን ኖሮ፣ እግዚአብሔር ከጋብቻ ውጭ ከወሲብ እንድን ታቀብ ይነግረን ነበርን? ከጋብቻ በኋላ እንኳ አንድ ሰው ለተወሰነ ጊዜ ከቤተ ሰቡ የሚለይበት ሁኔታ ካጋጠመው ወሲብ ካልፈጸምኩ በቀር እታመማለሁ ብሎ አሁንም ሥጋት ላይ የሚወድቅበት ምክንያት የለም። ባልየውና ሚስቲቱ እንደ ገና በሚገናኙበት ጊዜ ደስታቸው የላቀ ይሆናል።

3. አንድ ሰው የመጀመሪያ ሚስቱ ልጅ ካልወለደች፣ ሌላ ሚስት ማግባቱ ትክክል ነውን?

ከጋብቻ ታላላቅ በረከቶች ውስጥ አንዱ ልጆችን መውለድ፣ እንዲሁም እግዚአብሔርን እንዲፈሩና እንዲያውቁ አድርጎ ማሳደግ ነው። ይሁን እንጂ ይህ ልዩ ጥቅም አንጂ መብት አይደለም። ብዙ የአፍሪካ ባህሎች ልጆችን ማግኘት የባል መብት ነው ይላሉ፣ ከዚህም የተነሣ በእነዚህ ባህሎች የሚገኙ ብዙ ሰዎች ልጆችን አለማግኘት ለፍች ወይም የጋብቻን ግንኙነት በሚፈልጉት መንገድ ለማስኬድ ተገቢ ምክንያት አድርገው ይጠቀሙበታል። ይህ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። ልጆች ከእግዚአብሔር የተሰጡ ስጦታዎች ናቸው (መዝሙር 127÷3)። ስጦታዎች የሚሰጡትም በሰጪው በጎ ፈቃድ ነው። የተቀባዩ መብቶች አይደሉም።

በተጨማሪም እግዚአብሔር ሔዋንን የፈጠራት ከሁሉም በፊት የአዳም አጋር እንድትሆን እንጂ ለእርሱ ልጅ እንድትወልድለት አይደለም። እግዚአብሔር ጋብቻ ምን እንደ ሆነ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፤ «ሰው ከአባቱና ከእናቱ ተለይቶ ከሚስቱ ጋር ይጣመራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ» (ዘፍ 2÷24)። ሚስቲቱ ልጅ መውለድ አለባት ከሚል አንግር የጋብቻን ምንነት አልገለፀም። (Adapted from the *Nigerian Covenant: Study Guide*)

4. ማሕልየ መሓልይ ራሱ እስኪፈልግ ድረስ፣ ፍቅርን እንዳናስነሣው ወይም እንዳንቀሰቅሰው ያስጠነቅቀናል፤ ፍቅር የሚቀሰቀስበት ትክክለኛ ጊዜ መቼ እንደ ሆነ እንዴት ማወቅ እንችላለን?

እግዚአብሔር በአንተ ላይ ፍቅርን መቼ እንደ ቀሰቀሰ ማወቁ እስቸጋሪ ነው፤ ምክንያቱም በትክክል ሲታይ፣ ፍትወት ወይም ከራስ ወዳድነት የመነጨ ፍላጎት፣ ፍቅር ሊመስልህ ይችላል። እግዚአብሔር ለአንተ (ለአንች) ሴትን ወይም ወንድን እንዲመርጥ ማድረግ አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር እንዲመርጥ ፈቃድን ለእርሱ ማስረከብ ማለት አዳም እንደ ተኛው መተኛት ማለት ነው። በሌላ አነጋገር የትዳር ጓደኛን ምርጫ በተመለከተ እግዚአብሔር ከእንቅልፉ እስኪቀሰቅሰው ድረስ (ማሕልየ መሓልይ 8÷4)፣ አንድ ሰው ውጫዊ ለሆነው ሁኔታ ጀርባውን ሰጥቶ በትዕግሥት መቆየት አለበት። እግዚአብሔር ይመርጥ ዘንድ ሁሉን ነገር ለእርሱ ለመተው፣ ከልብ መጸለይን ማወቅና የእግዚአብሔርን ምሪት በመረዳት ማደግን ይጠይቃል። (Adapted from the *Nigerian Covenant: Study Guide*)

5. ወሲብ ይህን ያህል ጥሩ ከሆነ፣ እኛ በፊለግን ቊጥር በዚያ አንድንደሰት እግዚአብሔር ለምን አልፈለገም?

የጎጢአት እውነታ፣ ጥሩ የሆነው ነገር ብዙ ጊዜ ትክክል ባልሆነ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውል መደረጉ ነው። እግዚአብሔር የሰጠንን የወሲብ ስጦታ እንዴት መጠቀም እንዳለብን ግልጽ መመሪያን ሰጥቶአል። እግዚአብሔር ለእኛ መልካም የሆነውን ነገር በመከልከል፣ ከባሕሪው ውጭ ክፉ ሊሆንብን አይፈልግም። ይልቁንስ እኛ ከጋብቻ በፊት የምንፈጽመው ወሲብ ጉዳትን፣ ዕላማ ማጣትንና ርካታ ቢስ መሆንን እንደሚያስከትልብን በቸርነቱ ያውቃል።

ከዚህ ሁኔታ ሊጠብቀን ይፈልጋል። እግዚአብሔር መልካም ስጦታዎችን ይሰጣል፤ በስጦታዎቹ ለመደሰት ግን በትክክለኛው ጊዜ እንጠቀምባቸው ዘንድ መቆየት አለብን።

6. የተጫጩ ጥንዶች ከጋብቻ በፊት ወሲብ ቢፈጽሙ ስሕተት ነውን?

ጤነኛ በሆነ ግንኙነት፣ አካላዊ መፈቃቀድ የሚያድገው አንዱ ለሌላው ራሱን የመስጠቱ ሁኔታ እያደገ ሲሄድ ነው። እድገቱ የራሱ የሆነ ከፍተኛ ኀይል አለው። የወሲብ ፍላጎቱ እያደገ መጥቶ ለመቁጣጠር አስቸጋሪ ከመሆኑ በፊት፣ ፍትወትን ገትቶ ማስቀረት ጥበብ ነው። ነገር ግን አያሌ ጥንዶች ለመጋባት ካቀዱን ዘንድ ከጋብቻ በፊት ወሲብ መፈጸሙ የተፈቀደ ነው የሚል አቋም በመያዝ፣ ንጽሕናቸውን እስከ ማጕደፍ ድረስ ይሄዳሉ። የሚያሳዝን ነው፤ ከጋብቻ በፊት ወሲብ ለመፈጸም ምክንያት ከመፍጠር ይልቅ በጋብቻ ውስጥ ለሚፈጸመው ሩካቤ ሥጋ እግዚአብሔር ያቀደውን ዕቅድ መከተሉ የተሻለ ነው።

7. ጳውሎስ ሳያገቡ መኖር ይሻላል ያለው ለምንድን ነው?

ጳውሎስ እንዲህ ያለበት ምክንያት የሚከተለው ነው፤ ያላገባ ወንድ ወይም ያላገባች ሴት፣ «ስለ ጌታ ነገር ያስባል» ወይም ታስባለች። የትዳር ጓደኛን ወይም ቤተ ሰብን የመንከባከብ ጣልቃ ገብነት ሳይኖርም ጌታን በማገልገል ረገድ ትኵረት ለማድረግ ጊዜና ዕቅም ይኖረዋል (1ቆሮ 7፥32-35)። ጳውሎስ ራሱ የመረጠው ይህንኑ መንገድ ነው። ማግባት ስሕተት እንዳልሆነ ግን በግልጽ አመልክቶአል። እንዲያውም ኢግብረገባዊነትን ገድቦ የሚያስቀር መሣሪያ ነው በማለት ጋብቻ ይኑር ብሎአል (1ቆሮ 1፥7)።

8. አንድ ሰው ያገባ ዘንድ የስንት ዓመት ሰው መሆን አለበት?

አንድ ሰው ዘላቂና ጎላፊነት ያለበትን ምርጫ ያደርግ ዘንድ ብስለት ከሚታይበት የዕድሜ ደረጃ ላይ መድረሱ አስፈላጊ ነው።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

1. የጋብቻ ፎቶግራፍ
2. ሬድዮና ቴፕ
3. ዝነኛ የፍቅር ሙዚቃ የተቀረጹበት የቴፕ ክር

IV. ለሁሉን አቀፍ ትምህርት የቀረቡ እይታዎች

ትንታኔ

Genesis 2:24
Kyle Yates, *Wycliff Bible Commentary, 1962*, Moody Press, p.6

«ስለዚህ ሰው ... ከሚስቱ ጋር ይጣመራል (ደባክ - *dabaq*) ፈጣሪ አምላካችን አንድ ለአንድ ለሆነው ጋብቻ አስፈላጊውን መሠረት ጥሎአል። ታላቁ የዕብራይስጥ ተርጓሚ ራሺ እነዚህ ቃላት በመንፈስ ቅዱስ የተሰየ አጽንዖት የተደረገባቸው ናቸው ብሎአል። ስለ ባልና ሚስት መጣመር የመጨረሻ የሆነው ማብራሪያ የተሰጠው በጌታ ኢየሱስ ነው፤ ይህም እንዲህ ይላል፤ «ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይጣመራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፤ ከእንግዲህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ያጣመረውን ማንም አይለየው (ማር 10፥7-9)። እግዚአብሔር የጋብቻ ትስስር እስከ ዘለቄታው እንዳይፈታ አድርጎ ዐቀደው። ይጣበቃል (ደባክ - dabaq) ማለት ራሱን ከገዛ ሚስቱ ጋር አጣበቀ ማለት ነው። መጣበቅ ያለበት ይበልጥ ብርቱ የሆነው

ስውየው ነው። ባልየው በዚህ ጥቅስ ላይ የተገለጸውን ብርቱ ፍቅር ሲገልጽ፣ ሚስቱ በዚሁ ፍቅር ትታሰራለች። ፍቅር ብርቱና ዘላቂ ነው። ስለዚህ «እግዚአብሔር ያጣመረውን ማንም አይለየው።» ይህ የቆየ ሐሳብ ነው፤ ይሁን እንጂ ዛሬም ሆነ ነገ ልባችንን የሚያሳርፍ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

ከምእት ዓመታት በፊት በሙሴ በትክክል የተገለጸው ግንኙነት የዘላለም እውነትና መለኮታዊ ትእዛዝ ሆኖ አሁንም መጽናቱ እንዴት የሚያስደንቅ ነው! የጋብቻ ቅዱስነት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ዐቢይ ስፍራ የያዘ ነው፤ መሠረታዊ እንደ መሆኑም በመንፈስ ቅዱስ ለዘላለሙ አጽንዖት ተሰጥቶታል። እግዚአብሔር በአምሳሉ የፈጠራቸው ሰዎች እርሱን ደስ የሚያሰኝ ቤት ለመሥራት የተመረጡ ዕቃዎች ይሆኑ ዘንድ ፈቃዱ ሆነ። በአዲስ ኪዳን ላይ መንፈስ ቅዱስ የሚከተሉትን ዐቢይ ጉዳዮች ገልጦ ያሳያል፦ በፍጥረት ሥርዐት ላይ ተመሥርቶ በመለኮት ትእዛዝ የተጀመረውን የወንድና የሴት ግንኙነትን፣ የቤተ ሰብ ጎላፊነትን በባል ላይ እንዲሆን መደረጉን፣ የጋብቻ ቃል ኪዳን ለዘላለም የተቀደሰ መሆኑን፣ ባልንና ሚስትን የሚያስተሳስራቸው የፍቅር ዐይነት እንዲሁም ክርስቶስ ሕይወቱን የሰጠላት ሙሽራ ምሳሌ የሆኑት ወገኖች ተለይተው የሚታወቁበት ንጽሕናን። *[Used by Permission of Moody Press)*

ማሕልየ መሓልይ
David Hubbard ***Mastering the Old Testament: Ecclesiastes, Song of Solomon,*** **1991 Word Publishing, pp. 267-269**

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጋብቻ ይናገራል። በመጀመሪያ ወደዚህ ምድር ለመምጣት ቀዳሚ የሆኑትን ሴትና ወንድ አንድነት ያሳያል። ይህ አንድነት «አነሆ፤ ይህች ዐጥንት ከዐጥንቴ፣ ሥጋም ከሥጋዬ ናት» በሚል የደስታ ጩኸት የታጀበ ነበር (ዘፍ 2÷23)። ጽኑ በሆነ ትእዛዝ የተመሠረተ አንድነት ነበር፤ «ስለዚህ ሰው ከአባቱና ከእናቱ ተለይቶ ከሚስቱ ጋር ይጣመራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ» (ዘፍ 2÷24)። ማራኪና ንጽሕናም መለያው የሆነ አንድነት ነበር፤ «ሁለቱም ዕራቍታቸውን ነበሩ፤ ይሁን እንጂ አይተፋፈሩም ነበር» (ዘፍ 2÷25)።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጋብቻ መናገሩን በመቀጠል እግዚአብሔር የታሪክን አካሄድ ቤዛ በሆነ እጅ እየመራ፣ እርሱ ያቀደው ሁሉ ፍጻሜ ላይ መድረሱን በመጨረሻ ከጋብቻ ጋር በተያያዘ መንገድ እንዲህ በማለት ይገልጻል፤ «የበጉ ሰርግ ስለ ደረሰ፣ የእርሱም ሙሽራ ራሷን ስላዘጋጀች፣ ደስ ይበለን፤ ሐሤት እናድርግ፤ ክብርም እንስጠው። የሚያንጸባርቅና ንጹሕ፣ ከተልባ እግር የተሠራ ቀጭን ልብስ እንድትለብስ ተሰጣት። ከተልባ እግር የተሠራው ቀጭን ልብስ የቅዱሳን የጽድቅ ሥራ ነው» መልአኩም፣ «'ወደ በጉ ሰርግ እራት የተጠሩ ብፁዓን ናቸው' ብለህ ጻፍ» አለኝ (ራእ 19÷7-9)።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጋብቻ ይናገራል፤ ከመጀመሪያ አንሥቶ እስከ መጨረሻ ባለው አካሄዱ ሁሉ ማእከላዊ የሆኑትን ጉዳዮች አጉልቶ የሚያሳየው ከጋብቻ ጋር በተያያዘ ዘይቤአዊ አነጋገር አማካይነት ነው። ከሆሴዕ ጥልቅና ሥቃይ ከበዛበት ተመክሮ እንደምንረዳው፣ እግዚአብሔር በጋብቻ ቃል ኪዳን ከእስራኤል ጋር እንደ ተሳሰረ ሁሉ፣ እርሷም ከእርሱ ጋር በጋብቻ ቃል ኪዳን

ተሳስራለች። ኢሳይያስ (62÷4)፣ ተፈርዶ ባቸው የተተዉ እና የተፈቱ የተባሉት ይሁዳና ኢየሩሳሌም ድነታቸውን በት እምርት ለማመልከትም ደስታዬ በእናንተ ነው ተብለው እንደገና የሚጠሩበትንና ጋብቻ የሚፈፅሙበትን ቀን አሻግሮ ይመለከታል። ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር እያለ ባልንጀሮቹ በበዓሉ እንዲደሰቱ እያበረታታቸው (ማቴ 9÷14-15፤ 25÷1-13፤ ዮሐ 3÷29) እርሱም ሙሽራ ሆኖ በመሀከላቸው ተገኝቶ እንደ ነበር የሚያመለክቱ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች በብዛት ይገኛሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ በለጋች መካከል የሚደረገው ጋብቻ፣ ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለውን ጋብቻ አጉልቶ የሚያሳይ መሆኑን አስተውሏል (ኤፌ 5÷21-33)።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጋብቻ ይናገራል፤ በማ እከላዊ ስፍራውም ላይ መንፈስ ቅዱስ የጋብቻ መዝሙሮችን ስብስብ አስቀምጦአል። እነዚህም መዝሙሮች የአምልኮ ሥርዐቶች ወይም ትእዛዛት፣ የመዝሙረኛ ማኅሌት፣ የነቢይ ንግር፣ የባለ ራእይ ራእይ የላቸውም። በስሜት ተፈልቅቀው የወጡ፣ በፍላጎት ብሩህ የሆኑ፣ ሥጋዊ ፍቅርን በመናፈቅ የፈነዱ፣ ንጹሕና ግልፅ የሆኑ የፍቅር መዝሙሮች ናቸው። በዚህም ከሌላው የብሉይ ኪዳን ክፍል የተለዩ ናቸው። ከዘፍጥረት 4 እና 10 ጀምሮ እስከ ሚልክያስ መጨረሻ ድረስ ወሲብ የሚፈፀመው ልጅ ለመውለድ ነው። ዐላማው ዘር ማፍራት ነው፤ ግቡም እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ፍጻሜ ላይ በማድረስ የአብርሃም ዘር እንዲቀጥል ማድረግ ነው። ይስሐቅ እስኪፀነስ ድረስ ወሮች ዐልፈው ወሮች እየተተኩ ሲሄዱ፣ ከሣራ ጋር የምንስቅበትና የምናለቅስበት ሁኔታ ይገጥመናል። መካኗ ሐና የምትወልደውን ልጅ ለጌታ አገልግሎት አሳልፋ ለመስጠት ቃል በመግባት ልጅ ትወልድ ዘንድ በሴሎ ማምለኪያ ላይ በማነብነብ ጸሎት ስታቀርብ እኛም በመስማማት «አሜን» እንላለን። ከእነዚህ ታሪኮች የባልና ሚስት ግንኙነት ምን መምሰል እንዳለበት የሚያሳዩ ፍንጮች አናገኝም። ስለ ፍቅር ስሜት በተለይም በወሲባዊ ግንኙነት አማካይነት እውን ስለሚሆነው ደስታ ጥያቄ አናነሣም።

ነገር ግን ማሕልየ መሓልይ ከዚህ የተለየ ነው። እዚህ ላይ ወሲብ ለደስታ፣ ለአንድነት፣ ለግንኙነትና ለሙገሳ ነው። ግጥሞቹ ዕርግዝናንና ወላጅነትን ተስፋ የማድረግ ሁኔታን አይገልፁም። ትኩረቱ ያረፈው የዘር ሐረጉ እንዲቀጥል ዘር በማስቀረት ላይ ላይሆን ፣ ባልና ሚስት የገቡት ቃል ኪዳን ፍጻሜ ላይ ይደርስ ዘንድ በጥልቅ የፍቅር ስሜት ላይ ነው። ካርል ባርት የማሕልየ መሓልይን ቃና የገለጸው፣ «ጎፍረት የሌለበት የፍቅር ስሜት» በማለት ነበር። እርሱም የመጀመሪያዎቹ ወንድና ሴት ዕራቍታቸውንና ሳይተፋፈሩ ፊት ለፊት ቆመው (ዘፍ 2÷25)፣ አንዱ ሌላውን በማድነቅ የቀረበ ቅኔያዊ ገለጻ አድርጎ ተመለከተው።

በዔደን የነበረው ያ ግንኙነት ክቡር ነበር። እነዚያ የመጀመሪያዎቹ ጥንዶች የሰው ዘር መሆን ያለበትን ሁኔታ በመያዝ ያልተበከሉ ሆነው ከእግዚአብሔር እጅ መጡ። ሴሎችን ፍጥረቶች በበላይ ሆኖ የመቈጣጠርን ኀላፊነት ከፈጣሪ ጋር ተጋሩ። ሰውየው እንደራሴነቱን በትእምርት ለመግለፅ ለእንስሳቱ ስም አወጣላቸው። ወንድና ሴት ሆነው በአምላክ አምሳል የተፈጠሩት እነዚህ

ባልና ሚስት በዚያ እንዲኖሩ በተደረገበት የአትክልት ስፍራ ገነሮች ሆነው በደስታ ኖሩ። ከፈጣሪያቸው ጋርና እርስ በርሳቸው የነበራቸው ግንኙነት፣ የሰው ዘር ሕይወት ምን መሆን እንዳለበት በእርአያነት የሚያመለክት ነበር። ይህም በአሪት ዘፍጥረት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች ላይ ይገኛል። ከዚያም በምዕ 3 ላይ ተንኰለኛ ውን እባብ፣ ዐመፀኛ በመሆን ፍሬ መብላታቸውን፣ በደለኛ መሆናቸው ተሰምታ ቸው ከእግዚአብሔር መሸሸጋቸውን፣ እርስ በርስ መወነጃጀላቸውንና ዕራቍትነታቸውን በቅጠል እስኪሸፍኑ ድረስ በኀፍረት መያዛቸውን እንመለከታለን። ከዚያ ወቅት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የሰው ዘር ቤተ ሰብ ጸታዊ ስሜቱን፣ አመለካከቱንና ድርጊቱን ተቈጣጥሮ ለመኖር እየታገለ ነው። ሙሉነት ላይሆን ስብራት ዕጣ ፈንታችን ሆነ። የስብራቱ መልክ ስፍር ቊጥር የለውም፤ ወሲብን በከፋ መልኩ የሚርቀው ግብዝነት፣ ወይም በበጎ መልኩ የሚያስተናግደው ከልክ በላይ የሆነ ሥነ ሥርዐት አክባሪነት፣ ጤነኛ ያልሆነ የወሲብ ግንኙነት፣ ወይም ሌሎችን አሠቃይቶ በመርካት የራስን ጥቅም መጠበቅ ሊሆን፣ ወሲባዊ ግንኙነትንም ድል የሚገኝበት ግጥሚያ ወይም በድል የሚገኝ መራት አድርጎ መቊጠር ነው።

ስለ ጸታና ስለ ጋብቻ ብርቱ ጥንቃቄ የሚያደርገው መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሔዋንና አዳም እግዚአብሔር የሰጣቸውን ኀላፊነት ከተላለፉ በኋላ ሁኔታው እንዴት አስከፊ እየሆነ እንደመጣ፣ በሂደትም የጸታነታ ቸውን ትርጉም እንዴት እንደ አበላሹት በአያሌው አስፍሮ ይገኛል። በአንድ በኩል ሊታይም ወንድና ሴት መሆናቸው ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ያንጸባርቃል። ወንድና ሴት ሆነው በእርሱ አምሳል ተፈጠሩ (ዘፍ 1÷27)። እርስ በርስ ጥብቅ ትስስር ለማድረግ የነበራቸው ችሎታ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን አንድነትና ግንኙነት ነፀብራቅ ነበር። ባለመታዘዝ ከአምላካቸው ጋር የነበራቸውን ለማያዊ አንድነት ባፈረሱ ጊዜ ግራ ተጋቡ፣ እርስ በርስ በነበራቸው ምድራዊ ግንኙነት ረገድም የተምታታ ሕይወት ውስጥ ገቡ። ይህን ግራ መጋባትም ለትውልዳቸው ሁሉ አስተላለፉ።

በሰዶምና በገሞራ (ዘፍ 18÷16-19:29) ወይም በጊብዓ (መሳ 19) የተከሠቱት አሳዛኝ ሁኔታዎች፣ ልቅ ወሲባዊ ድርጊት የቱን ያህል ሰውን አዘቅጥ ውስጥ ሊከት እንደሚችል ያረጋግጣሉ። በዐሥርቱ ትእዛዛት ውስጥ ማእከላዊ ስፍራን በመያዝ ምንዝር መፈጸም እንደሌለበት የሚያመለክተው ትእዛዝ፣ ጋብቻ የቱን ያህል ቅዱስ እንደ ሆነና እኛም ታማኝነታችንን ለማጕደል የቱን ያህል ዝንባሌ እንዳለን ያሳስባል። በመጀመሪ ያውኑ በመለኮት ባርኮት የተመሠረተው ክቡር ግንኙነት እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ዘላለማዊ ፍቅር እንዲያ ንጸባርቅ የታለመለት ቀዳሚ ዕቅድ በፍትወትና በብልግና አንድ ጊዜ ከተበላሸ በኋላ ገደብ ወደሌለው የውርደት አዘቅት ለመውረድ የተጋለጠ ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጋብቻ ይናገራል፤ የሚናገረውም ከታሪኩ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ ስለሚገኘው፣ ንጹሕና አስደሳች ስለ ሆነው ጋብቻ ብቻ ሳይሆን፣ በጉዞ ላይ ትድግና ስለሚያስፈልገውም ጋብቻ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማሕልየ መሓልይን ያህል ከብክለት ነፃ የሆነ የጋብቻ ፍቅር ምን ማለት እንደ ሆነ የሚገልጽ ሌላ

ክፍል የለም። የርእሱ ስያሜ መጽሐፉን ከአስቀያሚውና ከፍተወታዊው ዐልፎ ተርፎም ውብ ከሆነው ከፍቅር ታሪክ በላይ ከፍ ያደርገዋል፤ ከተቀሩት የብሉይ ኪዳን ግጥሞችም ልዩ ያደርገዋል። *[Used by Permission of Thomas Nelson, Inc.]*

ማሕልየ መሓልይ 8፥4፡6-7
Danny McCain

መግቢያ፤ ማሕልየ መሓልይ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ለመረዳትና ለመተርጐም በጣም አስቸጋሪ ከሆኑት መጻሕፍት ውስጥ አንዱ ነው። አስቸጋሪነቱም ማን ጻፈው? ከሚለው ጥያቄ አንስቶ ትክክለኛው የአተረጓጐም ስልት የትኛው ነው እስከሚለው ድረስ ያለውን በማካተት ከመጽሐፉ አያሌ ገጽታዎች ጋር ይያያዛል። የእኔ የግሌ መረዳት በሰሎሞን የተጻፈ አለዚያም ስለ ሰሎሞን የተጻፈ መጽሐፍ ነው የሚል ነው። ረጅም የፍቅር ግጥም ወይም የፍቅር ግጥሞች ስብስብ አሊያም ተውኔት ሆኖ ተጽፎ ይሆናል። ምናልባት በሰሎሞን አያሌ የጋብቻ በዐሎች ላይ እንዲዜም ወይም በመድረክ ላይ እንዲቀርብ ሆኖ ሳይዘጋጅ አልቀረም።

ይህም እርስ በርስ በጣም የሚዋደዱ ሁለት ሰዎች በመሀከላቸው ያለውን የጋለ ፍቅር ቀጥተኛ መገለጫ ይመስለኛል። ስለዚህ መጽሐፉ እግዚአብሔር ይሆን ዘንድ ባቀደው መሠረት የተገለጸውን የሰዎች እውነተኛ ፍቅር ማሞገሻ ይመስለኛል። ግሊሰን አርከር እንዲህ ይላሉ፤ «ቃል በቃል የሆነው ትወራ፣ ይህ ግጥም ሥነ መለኮታዊ ቃና ያለውን መንፈሳዊ መልእክት ለማሳየት ሳይሆን፣ ምጡቅ ደረጃ ላይ የደረሰውን የሰውን የፍቅር ስሜት ለማሳየት ሲባል በቅኔ መልክ የቀረበ ዓለማዊ የፍቅር መወድስ አድርጐ ይመለከተዋል» የሚል ነው። የመጽሐፉ ዐላማ በዚያ ዘመን በስፋት ይተገበር ከነበረው ከአንድ በላይ ጋብቻ ይልቅ፣ አንድ ለአንድ ጋብቻ የቱን ያህል ውብና የጠለቀ ግንኙነት ያለበት ለመሆኑ መለከታዊ ማስረጃ ለመስጠት ሳይሆን አይቀርም። መጽሐፉን በቁሙ ከሚተረጕሙት ሰዎች አንጻር ቢያንስ ቢያንስ ሁለት ዐበይት አመለካከቶች አሉ።

ባለ ሦስትዮሽ ሰው እይታ፤ አንዳንድ ተርጓሚዎች በዚህ ታሪክ ውስጥ ሦስት ሰዎች የተሳተፉ መሆናቸውን ያስተውላሉ። በመጀመሪያ ሰሎሞን ወደ ዕልፍኙ ለማስገባት የሚያዘ ጋጃት ቄንጆዬቱ ወጣት ልጃገረድ አለች። ሁለተኛ በአገሪቱ ገጠር አካባቢ ሲጓዝ ሳለ ይህችን ውብ ልጃገረድ አስተውሎ በመመልከት በፍቅሯ የወደቀው ንጉሥ ሰሎሞን አለ። ታሪኩ ስለ እርሱ ሲሆን፤ ይህችን ወጣት ሴት ከሚስቶቹ አንዷ ለማድረግና እርሷኑ በፍቅሩ ለማሸነፍ የሚያደርገውን ጥረት የሚያሳይ ነው። ይሁን እንጂ በታሪኩ ሥዕል ውስጥ ሦስተኛ ሰው አለ። እርሱም ወጣቷ ሴት በጣም የምትወደው ልዩ የሆነው እረኛ ነው። ሰሎሞን ሊሰጣት ከሚችለው ማራኪ ከሆነውና ምኞት ካለው ነገር ይልቅ ይህን ሰው ትወደዋለች። በምንባቡ ውስጥ ግልጽ ሆኖ እንደሚታየው መሻቷና ናፍቆቷ ባለጸጋ ለሆነውና ሀብቱን እንዳሻው ለሚረጨው ንጉሥ ሳይሆን፣ እውነተኛ ለሆነው ፍቅረኛዋ ነው። ይህኛው አተረጓጐም ከቁሳዊ ሀብት ይልቅ በእውነተኛ ፍቅር ለመርካት በመምረጥ፤ እውነተኛ ፍቅር የቱን ያህል ውብ እንደ ሆነ አጽንዖት ያደርጋል።

ባለ ሁለትዮሽ ሰው እይታ፣ ከዚህ እይታ አንፃር መጽሐፉ በሰሎሞንና በዚህች ወጣት ሴት መካከል የነበረውን ንጹሕ ፍቅር የሚገልፅ ነው። ሰሎሞን ሌሎች ብዙ ሚስቶች የነበሩት ቢሆንም እንኳ ይህች ወጣት ሴት እውነተኛ ፍቅር ምን ማለት እንደ ሆነ አስተማረችው። ይህ እንግዲህ ነባሩ አመለካከት ነው።

ትንታኔ፤ በማሕልየ መሓልይ መጽሐፍ ላይ በተደጋጋሚ የሚታይ ፍሬ ሐሳብ አለ። መጽሐፍ ቅዱስ በእጅጉ ዕምቅ የሆነ መጽሐፍ ስለ ሆነ፤ አንድ ነገር በተደጋጋሚ ሲያጋጥምህ፣ ልዩ ትኩረት ማድረግ ይኖርብሃል። በ2፥7 ላይ ጸሓፊው እንዲህ ይገልጻል፤ «እናንት የኢየሩሳሌም ቈነጃጅት ራሱ እስኪፈልግ ድረስ ፍቅርን እንዳታስ ነሡት ወይም እንዳትቀሰቅሱት በሚዳቋና በሜዳ ዋልያ አማጥናችኋለሁ።» ይህ ጥቅስ በ3፥5 ላይ ቃል በቃል ተደግሞ ይገኛል። ይኸው ጥቅስ አጠር ባለ መልክ በ8፥4 ላይ ተደግሞ እንዲህ ይላል፤ «እናንት የኢየሩሳሌም ቈነጃጅት፤ ራሱ እስኪፈልግ ድረስ፣ ፍቅርን እንዳታስነሡት ወይም እንዳትቀሰቅሱት አማጠናችኋለሁ።»

ጸሐፊው ይህንኑ ማስጠንቀቂያ ሦስት ጊዜ በሦስት ልዩ ልዩ ዐውዶች ውስጥ ሰጥቷል። በዚህ ሐሳብ ላይ አጽንዖት ያደረገው ለምንድን ነው? ምክንያቱም መጽሐፉ ክልብ የሆነ የጋለ ፍቅር ማሞገሻ በመሆኑ ነው። እግዚአብሔር ከሰጣቸው ልዩ ስጦታዎች መሀከል ይህ አንዱ ነው። ይሁን እንጂ እንደ ማንኛቸውም የእግዚአብሔር ስጦታዎች ሁሉ ልዩ በሆነ መልክ ሊያዝና ሊያድግ ይገባል። ይህን ስጦታ እጅግ በፈጠነ መልኩ የሚቀበሉትና ወዲያው ተግባራዊ የሚያደርጉት ከሆነ፣ አጥፊ ሊሆን ይችላል።

በ8፥6-7 ላይ ጸሐፊው ይህ የጋለ ፍቅር ለምን በፈጠነ መልኩ መነሳሳት እንደሌለበት ሲገልጽ፣ «ፍቅር እንደ ሞት የበረታች፣ ቅናቷም እንደ መቃብር ጨካኝ ናትና፤» ይላል (8፥6ለ)። ፍቅር በዓለም ውስጥ እጅግ ብርቱ ኀይል ነው። ሞት ሰለባው ያደረገውን ሰው እንደማይምረው ሁሉ ፍቅርም እንዲሁ ብርቱ ነው።

«የውሃ ብዛት ፍቅርን ሊያጠፋ ለይችልም፣ ፈሳሾችም ለያሰጥሟትም» (8፥7ሀ)። በዓለም ውስጥ ፍቅር እጅግ ጽኑ ኀይል ነው። አንድ ሰው አንዲትን ሴት ሊወድ ፍቅሩን ለመግለጽና እርሱም በበኩሉ እንዲወደድ ለማድረግ ብዙ ርቀት ይጓዛል። አንድ ሰው ወንዝን ለመገደብ ሙከራ ሊያደርግ ይችላል። ይሁን እንጂ ከጊዜ በኋላ ውሃው እስከ ጫፍ ድረስ ከፍ እያለ ይሄዳል፤ ወይም በጉን ይፈላል። የተቃራኒ ጾታ ፍቅርም እንደዚሁ ነው፤ ራሱን የሚገልጽበት መንገድ እስከሚያገኝ ድረስ በሰውየው ውስጥ ቀስ በቀስ ያድጋል።

«ሰው የቤቱን ሀብት ሁሉ ስለ ፍቅር ቢሰጥ፣ ፈጽም ይናቃል (8፥7ለ)። ይህ ሐሳብ ፍቅር በዓለም ውስጥ እጅግ ውድ የሆነ ነገር መሆኑን ይነግረናል። አንድ ወንድ አንዲትን ሴት ከልቡ ሲወድ፣ እርሷን ለማስደሰት ሊል የማይሰጠው ወይም የማያደርገው ነገር የለም። አንዲት ሴት በእውነት አንድን ወንድ ከወደደች ፍቅሯን ለመግለጽ የሚያስችላት ከሆነ ቤተ መንግሥትን ትታ በጎጆ ውስጥ መኖር ትመርጣለች።

ገጀራ በጣም ድንቅ መሣሪያ ነው፤ በእርሻ ላይ ያለውን ቍጥቋጦ ለመቍረጥ ወይም የማገዶ ዕንጨት ለመቍረጥ ያገለግላል።

ሰውየው ራሱን ከአጥቂ ጠላት ለመከላከልም ያገለግለዋል። አንድ ሰው በሕይወት ዘመኑ በብዛት የሚጠቀምበት መሣሪያ ነው። ይሁን እንጂ አስተዋይ የሆነ አባት ለሦስት ዓመት ልጁ ይጫወትበት ዘንድ ገጀራ አይሰጠውም። ሕፃኑ ልጅ የመሣሪያውን አደገኛነት ወይም በጥንቃቄ እንዴት መጠቀም እንዳለበት አያውቅም። ገጀራውን የሚያገኝበት ሁኔታ ካጋጠመው፣ ጉዳት ሊያደርስበትና ወደፊትም በመሣሪያው እንዳይጠቀምበት ፍርሃት ሊያሳድርበት ይችላል።

የተቃራኒ ጾታ ፍቅር ከእግዚአብሔር የተገኘ ውድ ስጦታ ነው። የተጋቡ ሰዎች በአብዛኛው የሕይወት ዘመናቸው ሐሤት የሚያገኙበት ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ ፍቅር ገና ከጧቱ የሚቀሰቀስና በወሲባዊ ግንኙነት የሚገለጽ ከሆነ አደገኛ ሆኖ ሊገኝ ይችላል። ፍቅርን ገና ከጧቱ ማነሳሳት በትዳር ሕይወት ሁሉ የማይጠፋ አደገኛ የጎሊና ጠባሳን ያስከትላል፤ በሕይወትህም የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዳትፈጽም የሚያደርጉህን ጎላፊነቶች ገና ከጅምሩ ሊያስከትልብህ ይችላል።

ፍቅር፣ እግዚአብሔር ከፈጠራቸው እጅግ አስደናቂ ከሆኑት ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው፤ በተገቢው ሁኔታ ሲዘጋጅ፣ በተገቢ መንገድና በተገቢ ጊዜም ተግባራዊ ሲደረግ፣ ከሕይወት ታላላቅና አስደሳች ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው። ጊዜው ሳይደርስ ሙከራ ላይ የሚውል ከሆነ ግን፣ በሕይወት ውስጥ ከሚገጥሙ ከባድ ርግማኖች መካከል አንዱ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ጥበበኛው ሰው እንዲህ ብሎ በማወጁ መደነቅ የለብንም፤ «ራሱ እስኪፈልግ ድረስ፣ ፍቅርን እንዳታስነሡት ወይም እንዳትቀሰቅሱት።»

[Used by Permission of the author"]

ማሕልየ መሓልይ፣ ፍቅር ከመጽሐፍ ቅዱስ እይታ አንጻር፣ Lawrence O. Richords, The Teacher's Commentary, 1987, Scripture Press, pp. 356-357

ማሕልየ መሓልይ የጋብቻ ፍቅርን በማሞገስ የተጻፈ ግጥም ነው የሚለውን እይታ የምንቀበል ከሆነ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ መሠረት ወሲብ ምን እንደ ሆነ ይበልጥ በትኩረት እናይ ዘንድ ያስፈልጋል። በመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ወሲብን ተራ ነገር አድርጎ እንደማይቈጥረው መገንዘቡ ተገቢ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመንና መጽሐፍ ቅዱስ በተሠራጨባቸው በሌሎች አጎራባች ባሕሎች ውስጥ አነስተኛ ወሲባዊ ተዐቅቦ ታይቶ ነበር። በአካባቢ የሚገኙት የባዕድ አምልኮ ተከታዮች ሃይማኖታዊና ዓለማዊ ግጥሞች ጎፍረተ ሥጋንና (አካለ ወሲብንና) ወሲባዊ ግንኙነትን በሚገልፁ ሥዕላዊ ቋንቋዎችና የተሰዩ ቃሎች የተሞሉ ነበሩ። በአንጻሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ወሲብ ጉዳይ የሚናገረው በጥንቃቄ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጎፍረተ ሥጋን በትክክል የሚያመለክት ቃል አይገኝም። ወሲባዊ ግንኙነትን ለመግለጽ፣ «ማወቅ» እና «መተኛት» የተባሉት ቀጥተኛ ያልሆኑ (በማለዘብ የተነገሩ) አገላለጾች ጥቅም ላይ ውለው ይገኛሉ። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተዐቅቦ በጉልሕ የሚታይ ቢሆንም እንኳ፣ ከወሲብ አንጻር ጥብቅ የሆነ ሥነ ሥርዓት እንዲኖር አይገፋፋም። ይልቁንስ ሰው በወሲባዊ ስሜት የመሳብ ተፈጥሮ ያለው መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተረጋግጦአል። ወሲባዊ ጉዳዮች በጥንቃቄ መነገራቸውም የወሲባዊ ግንኙነትን ምስጢራዊነትና ልዩ ባሕርይ ያረጋግጣል። ቅዱሳት መጻሕፍት በተዐቅቦ አማካይነት ክልብ የሆነውን ተመክሮ ይሸውም እውነተኛ

ፍቅር ያለበትን ወሲባዊ ግንኙነት ምስጢር ነትና ንጽሕና ይጠብቃሉ። ይህም ተመክሮ ቅዱስ በመሆኑ በጥንቱ ባዕድ አምላኪ ሕዝቦች ዘንድ እንደ ነበረው ወይም በዘመናችን ለጎልማሶች ተብለው በሚዘጋጁ እትሞች ላይ እንደሚታየው ዐይነት፣ እንስሳዊ ተግባር ተደርጎ መታየት የለበትም። መጽሐፍ ቅዱስ ከጋብቻ ውጭ የሚፈጸመውን ወሲባዊ ግንኙነት ይከለክላል፤ ይህም ከጋብቻ በፊት የሚፈጸመውን ወሲባዊ ግንኙነትንና በጋብቻ ላይ ተደርቦ የሚፈጸመውን ምንዝርናን ይመለከታል፤ በተጨማሪም ሴተኛ አዳሪነትን ያወግዛል። የብሉይ ኪዳን የሕግ መጻሕፍት በተለይ ደግሞ ዘሌዋውያን ምዕራፍ 18 ወሲባዊ ዕግዶችን ወስኖ ያስቀምጣል። ይሁን እንጂ ጋብቻን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው መልእክት ከእግድ ይልቅ ነጻነት ጎልቶ ይታይበታል። በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ላይ በጋብቻ ውስጥ የሚደረገውን ወሲባዊ ግንኙነት የሚቈጣጠር ክፍል አይገኝም። ይልቁንስ መጽሐፍ ቅዱስ ሰው፣ ወንድ እና ሴት ሆኖ በመፈጠሩ ያለውን ደስታና ፋይዳ ያጸናል። በጋብቻ ውስጥ የሚፈጸመውን ወሲብ ጥያቄ ውስጥ ማስገባት ማለት፣ «የአጋንንትን ትምህርት» መከተል እንደ ሆነ ጳውሎስ ያስተምራል (1ጢሞ 4÷1)። ከፍጥረት ታሪክ እንደሚታየው ሰው የወሲብ ፍላጎት ያለው ሆኖ መገኘቱን እግዚአብሔር እንደሚወድ ግልጽ ነው፤ ምክንያቱም «ወንድና ሴት» አድርጎ የፈጠራቸው እርሱ ራሱ ነው (ዘፍ 1÷27)።

ዐልፎ ዐልፎ እንደሚታየው ክርስቲያኖች ስለ ወሲብ ባሕታዊና አሉታዊ አመለካከት ገንዘብ አድርገው ይገኛሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን እንኳ፣ አንዳንዶች ጋብቻ፣ «መንፈሳዊ» መሆን አለበት በማለት በክርስቲያን ባልና ሚስት መካከል ያለው ተገቢ ወሲባዊ ግንኙነት መቅረት አለበት የሚል ስሜት አድሮባቸው ነበር። ጳውሎስ ይህን በተመለከተ በ1ቆሮንቶስ 7÷3-5 ባለው ክፍል ትክክል የሆነውን ሐሳብ ሰጥቶአል።

በመጀመሪያው የፍጥረት ታሪክ ውስጥ እንደሚታየው እግዚአብሔር ሔዋንን ልክ እንደ አዳም፣ በራሱ በእግዚአብሔር አምሳል አድርጎ፣ ለአዳም የምትመች አጋር ትሆነው ዘንድ ከአዳም ጐድን ዐጥንት ፈጠራት። ሁለቱ ማለትም ወንድና ሴት የእያንዳንዳቸውን ውስጣዊ ፍላጎት ለማሟላት ልዩ የሆነ አንድ መሆንን ተመክሮ የማግኘት ችሎታ ነበራቸው፤ ይህም አንድነት በበኩሉ የታተመውና በትእምርትነት የተገለጸው በወሲባዊ ግንኙነት ነው። በዚህም ምክንያት ባልና ሚስት ይህን የአንድነት ክብር መገለጫ የሆነውንና በጋብቻ ውስጥ የሚፈጸመውን ወሲብ እርስ በርስ ይከላከሉ ዘንድ ጳውሎስ ፈቃደኛ አልነበረም።

ከጳውሎስ የአዲስ ኪዳን መልእክቶች ግልጽ ሆኖ እንደሚታየው፣ ወንዶችና ሴቶች ሳያገቡ የሚቀሩባቸው ምክንያቶች ያሉ መሆናቸውን ጳውሎስ አምኖአል። እርሱ ራሱ አለማግባትን መርጦ ነበር። ይሁን እንጂ ጳውሎስ ወሲባዊ ግንኙነትን የሚቃወም ሰው አልነበረም። በእግዚአብሔር ፈቃድ አንድ እንዲሆኑ ለሚጣመሩ ሰዎች፣ ወሲብ በእግዚአብሔር የታቀደው ለዕርካታ ብቻ ሳይሆን፣ በባልና ሚስት መካከል ያለውን የጠበቀ ትስስር የሚገልጽ ቅዱስ ድርጊት በመሆንም ነው።

ስለ ወሲባዊ ግንኙነት መጽሐፍ ቅዱስ ትክክል ነው ብሎ በሚያጸናው ዐውድ ውስጥ ማሕልየ መሓልይ ልዩ ሚና አለው። በፍቅር ቅኔነቱ በዚህ ግንኙነት ውስጥ

ያለውን ደስታ ልብ እንድንልና በመሠረቱ ውብ የሆነውን ጉዳይ በማድነቁ ተካፋዮች እንድንሆን ያግዘናል። በማሕልየ መሓልይ ላይ የንፁሕ ወሲባዊ ደስታ ባሕርይ ምን እንደሚመስል በጥንቃቄና በማስተዋል እንድንረዳ ተጋብዘናል። ይህም ስሜት አማኙን በጋብቻ ቃል ኪዳን ዐውድ ውስጥ ደስታ እንዲያገኝበት ነጻ የሚያደርገው ነው።

[Used by Permission of Cook Communication Ministries]

1ቆሮንቶስ 7÷1-8
Lawrence O. Richords
The Teacher's Commentary, 1987,
Scripture Press, pp. 864-865

በማንኛውም ዘመን ሰዎች ከመለኮት ጋር የጠለቀ ግንኙነት ለማድረግ መፈለጋቸውን የሚያጣ ምሙ መንትያ ዝንባሌዎች አሉ። ከእነዚህም አንዱ ሰው የሥጋ አምሮትንና ፍላጎትን በጥብቅ በመከልከል፣ ልዩ ቅድስናን ያገኛል የሚል የብሕትውና ሐሳብ ነው። ሌላው ዝንባሌ ደግሞ ልቅ የሆነ የወሲብ ስሜት ነው፤ ይህም ሥጋዊ የሆነው ነገር መፈጸም ምንም አይደለም፤ ስለዚህ ማንኛውም ዐይነት ስሜት ሙሉ በሙሉ እንዲረካ ማድረግ ያስፈልጋል በሚል እምነት ላይ የተመሠረተ ነው።

ጳውሎስ ሁለተኛውን አመለካከት በቆሮንቶስ በነበረበት ጊዜ በጥብቅ አውግዞታል፤ ይህንኑ ኢግብረገባዊነትም በዚህ መልእክት ላይ በድጋሚ ተቃውሞታል (1ቆሮ 1÷5)። አንዳንድ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች፣ የቆሮንቶስን ደልቃቃ የወጣት ፍልስፍና ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዘው መግባታቸውና ሴቶችንም እንደ መጫወቻ ነገር (እንደ አሻንጉሊት) መቍጠራቸው ግልጽ ሆኖ ይታያል።

ሴሎች ግን የተዓቅቦን መንገድ መርጠው ተጉዘዋል፤ ሴቶች በአማኞች አካል ውስጥ ሙሉ መብት ያላቸው በክርስቶስ እኅቶቻችን ናቸው ብለው መቀበላቸው ይህንኑ አመለካከት የሚያበረታታ ሆኖ ተገኝቶአል። ሴቶች አሁን ሴትነታቸው ግምት ውስጥ ሳይገባ ሙሉ በሙሉ እንደ ሰው የሚቈጠሩ ከሆነ ጋብቻና ያታዊው የሥጋ ዕርካታ የመቅረት ሁኔታን እያስከትልምን? ይህ ሐሳብ የቆሮንቶስ ሰዎች ላነሷቸው አንዳንድ ጥያቄዎች መንሥኤ ነበር፤ ይህም ጳውሎስ በተለይ፣ «ሰው ወደ ሴት ባይደርስ መልካም ነው» (7÷1) ብሎ ባስተማረው ትምህርት ላይ ተንጸባርቆ እንደ ታየው ነው።

ሴቶች ሙሉ በሙሉ እኩል መሆናቸው ጋብቻን ያስቀራልን? ጳውሎስ ሁልጊዜ እንደሚ ያደርገው ነገሩን በማሞገስ ይጀምራል፤ ይህም፣ «ሰው ወደ ሴት ባይደርስ መልካም ነው» የሚል ነው። ነገር ግን እርሱ ከእነርሱ ጋር በነበረበት ጊዜ ይህን ሐሳብ (ቍ 7) ሳያስተምራቸው እንዳልቀረ በመገንዘብ በተሳሳተ መንገድ እንዳይተረጉም አባባሉን ወዲያውኑ ያርማል። ከዚህ ላይ፣ «መልካም ነው» ሲባል «በግብረገብ ረገድ አስፈላጊ ነው» ወይም ደግሞ «የላቀ ነው» ማለት አይደለም። እንዲያውም ጤነኛው አካሄድ ጋብቻ እንደ ሆነ በአጽንዖት ተናግሯል። ጋብቻ ሲባል ደግሞ ጋብቻ ነው፤ ሩካቤ ሥጋንም ሙሉ በሙሉ ያካትታል። በቆሮንቶስ አንዳንዶች ያራምዱት የነበረው፣ ግብረ ሥጋ የማይፈጸምበት «ቅዱስ ጋብቻ» ፈጽሞ ጋብቻ አይደለም።

ጳውሎስ በዚህ ዓለም መኖር ማለት በአካል መኖር መሆኑን፣ ሰዎችም አካላዊ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን በሚገባ ግልፅ አድርጎ ተናግሯል። ከጋብቻ ዐላማዎች ውስጥ አንዱ እነዚህን ፍላጎቶች ቅዱስ በሆነ

መንገድ ማርካት ነው። ክርስቲያን ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው ይከላከሉ ዘንድ አልተፈቀደላቸውም (ቊ 5)። ከዚያም ጳውሎስ የሚያስደንቅ ሐሳብ ሰንዝሯል። በክርስቲያን ጋብቻ ውስጥ የጋብቻ መብት፣ ፍላጎትና መሻት ያለው ወንዱ ብቻ አይደለም፤ ሴቷም አሏት። ሴቲቱ የራሷ አካል ባለቤት እንደ ሆነች ሁሉ የባለቤቷ አካል ባለቤትም ናት። ይህ በጊዜው ከነበረው ባሕል ጋር ሥር ነቀል መፋታት ነው! የጸታ እኩልነትና የአጋርነት ትምህርት ዛሬ አንዳንዶችን እንደሚያስገርም ሁሉ፣ የጳውሎስንም አንባቢዎች በጣም ሳያስገርም አልቀረም *[Used by Permission of Cook Communication Ministries]*

ተጨማሪ ግንዛቤ ለማግኘት የሚረዱ የትኩረት ጽሑፎች

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ወሲብ ምን ይላል?
K.C. Hinckley, *A Compact Guide to the Christian Life.*
1989 Naupress, pp. 163-164

መልካም ነው፤ እግዚአብሔር የሰውን ዘር ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠረ (ዘፍ 1÷27)። አንዱ ለሌላው ማራኪና ደስ የሚል አድርጎ አበጀው። በባልና በሚስት መካከል ያለው አንድ አካል የመሆን ግንኙነት ዕቅዱ ምንጊዜም ሥጋዊና መንፈሳዊ ይሆን ዘንድ ነው። ወሲብ አካላዊ ውጥረትን ነጻ ያደርጋል፤ በሌላው ሰው ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘትንና በፈቃድ ላይ የተመሠረተን የእርስ በርስ መደጋገፍን ያንጸባርቃል። በጋብቻ ውስጥ የሚፈጸም ወሲብ የሚያስደስት ሊሆን ይገባል፤ «ምንጭህ ቡሩክ ይሁን፤ በልጅነት ሚስትህም ደስ ይበልህ። እርሷ እንደ ተወደደች ዋላ፣ እንደ ተዋበች ሚዳቋ ናት፤ ጡቶቿ ዘወትር ያርኩህ፤ ፍቅሯም ሁል ጊዜ ይማርክህ።» (ምሳ 5÷18-19)።

የአዳምና የሔዋን በኀጢአት መውደቅ ወሲብን በክሎታል። አንዳንድ የኀጢአት ገጽታ የሰውን የወሲብ ፍላጎት በእጅጉ አበላሽቶታል። ትዕቢትና እርስ በርስ መፈራራት በወንዶችና በሴቶች መካከል ደንቃራ ነገርን አምጥቶአል። እግዚአብሔር ፍላጎታቸውን ያሟላላቸው ዘንድ በእርሱ ላይ ባለመታመናቸው፣ አንዱ ሌላውን ሰው ፍላጎቱን ያሟላ ዘንድ በመጠምዘዝ ፍቅርንና አክብሮትን ለማግኘት ሲሉ ወሲብን እንደ መሣሪያ ይጠቀሙበታል። ጤነኛ የሆነው የሩካቤ ሥጋ ፍላጎት ከግል ብርቱ ፍላጎት ጋር በመዛመዱ፣ ስለዚህ ወሲብ የግል ፍላጎት ማርኪያ መሣሪያ፣ ማጥቂያ መሣሪያና አስጨናቂ ጥንውት ሆኖአል።

ወሲብ ጋብቻ ለፈጸሙ ባልና ሚስት ብቻ ነው፤ (1ቆሮ 6÷9-20 እና ሌሎች ምንባቦች) ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም ወሲብ የትዳር ጓደኛን የማታለልን ያህል ጉዳት የሚያስከትል ነው። ወሲብ እስከ ሕይወት ዘመን ድረስ የሚዘልቅ ቃል ኪዳን መገለጫ ነው።

ፍትወት ዝሙት የመፈጸምን ያህል ስለሆነ ኀጢአት ነው። በልብ የሚፈጸም ኀጢአት ራስን የሚጉዳና በግብር እንደሚፈጸመው ኀጢአት ያህል እግዚአብሔርን መበደል ነው (ማቴ 5÷28)። ይሁን እንጂ በፍትወትና የሌላውን ውበት በማድነቅ መካከል ልዩነት ያለ መሆኑን ልብ በል። የሌሎችን ሰዎች አካላትና አቋም ወይም ተክለ ሰውነት ልብ ማለት ያለ ነገር ነው፤ አንድ ሰው በአጠገብ ሲታይ የሆነ ስሜት ማሳየት እንኳ የሚያስነቅፍ አይደለም። በፍትወት መፈተንም ያለ ነገር ነው። ፈተና ኀጢአት የሚሆነው በፍላጎቱ ላይ ተደላድለህ ስትተኛበት ወይም በፈተናው ሳቢያ ህልም ዓለም ውስጥ ስትሰምጥ ነው።

የትዳር ጓደኛህን መመኘቱ ፍትወት ለይደለም፤ ፍትወት ውጉዝ ፍላጎት ነው። እግዚአብሔር የትዳር ጓደኛህን እንድትሻ አድርጎ ስለ ፈጠረህ፤ ይህ ፍላጎት በየምሽቱ ለመተኛት፤ በየቀኑም ለመብላት የመፈለግ ያህል መልካም ነው። እንዲያውም ባልና ሚስት አንዱ የሌላውን ፍላጎት እንዲያረካ እግዚአብሔር ያዛል (1ቆሮ 7÷3-5)።

ይሁን እንጂ የትዳር ጓደኛህን በአጉል መልክ ልትመኝ ችላለህ። እግዚአብሔር ቅድስናና ክብር በጋብቻ ውስጥ ለሚፈጸመው ወሲብ መሠረት መሆን እንዳለባቸው ይናገራል (1ተሰ 4÷3-5)፤ እርሱ ወይም እርሷ ውርደት ነው የሚሉትን ወሲባዊ ግንኙነት የምትጠይቅ ከሆነ፤ አሊያም እርሱ ወይም እርሷ ያለመፈለግ ወይም ያለመቻል ስሜት ሲሰማው(ት) ወሲብ የምትጠይቅ(ቂ) ከሆነ፤ የትዳር ጓደኛን ክብር የሚነካ ነው። አስጨንቆ መጠየቅና አይሆንም መባልን ቂም አድርጎ መያዝም ሁለቱም ኀጢአት ናቸው። የትዳር ጓደኛህ በተደጋጋሚ ፈቃደኛ ካልሆነች፤ የችግሩ መንሥኤ ምን እንደ ሆነ እንድትወያዩበት (ምናልባትም አማካሪ በተገኘ በት) የሚያመለክት ነው። *[UseD with Permission of Naupress]*

ወሲብን በተመለከተ የግዚአብሔር ዕቅድ ምንድን ነው?
Wilbur O'Donovan, Biblical Christianity in African Per Spective, 1992, Paternoster Press, pp. 283-287

እግዚአብሔር ሰዎችን በፈጠረ ጊዜ እንዲበዙና እንዲባዙ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው (ዘፍ 1÷26-27)። ለሰው ዘር በጎ እንዲሆንና ደስታ እንዲያስገኝ ወሲብ ከእግዚአብ ሔር የመጣ ሐሳብ መሆኑን ክርስቲያኖች ይረዱ ዘንድ አስፈላጊ ነው። በጋብቻ ውስጥ እስከሆነ ድረስ ወሲብ ኀጢአት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ወሲብ መልካም ነው (ዘፍ 1÷3)፤ ደግሞም ቅዱስ ነው (ዕብ 13÷4)። ሰው በዔደን የአትክልት ስፍራ በኀጢአት ከመውደቁ በፊት ለእርሱ ተሰጥቶ ነበር (ዘፍ 1÷27-28፤ 2÷21-25)። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤ «በልጅነት ሚስትህም ደስ ይበልህ እርሷ እንደ ተወደደች ዋላ፤ እንደ ተዋበች ሚዳቋ ናት፤ ጡቶቿ ዘወትር ያርኩህ፤ ፍቅሯም ሁልጊዜ ይማርክህ» (ምሳ 5÷18-19)።

የሰው ዘር የመጀመሪያው ኀጢአት የተከሠተው አዳም ከሚስቱ ጋር ወሲብ በመፈጸሙ ነው የሚል በሰፊው ተሠራጭቶ የሚገኝ እምነት አለ (ዘፍ 4÷1)። ይህ ስሕተት ነው። የመጀመሪያው ኀጢአት መልካምና ክፉን ከሚያሳውቀው የዛፍ ፍሬ እግዚአብሔር እንዳይበሉ ያዘዘውን ትእዛዝ መተላለፍ ነበር (ዘፍ 2÷17፤ 3÷6)። ሰው ከኀጢአት የተነሣ እግዚአብሔር ወሲብን በሚመለከት ያቀደውን ዕቅድ አጣመመው በከለውም። እግዚአብሔር ባቀደው መሠረት ከሆነ፤ ወሲባዊ ግንኙነት በጋብቻ ቃል ኪዳን ውስጥ ለባልና ለሚስት ብቻ በጥብቅ ተለይቶ የተሰጠ ነው (1ቆሮ 7÷2-5፤ ዕብ 13÷4)። ከጋብቻ ውጭ ወሲብ መፈጸም ከባድ ኀጢአት ነው። በአሁኑ ጊዜ በዐለም ላይ የሚታዩ አያሌ ችግሮች የዝሙት መዘዞች ናቸው። ዝሙት (ለትዳር ጓደኛ ታማኝ አለመሆን)፤ ወሲባዊ ኢግብረገባዊነት (ከጋብቻ በፊት ወሲብ መፈጸም)፤ ግብረሰዶማዊነት (ተመሳሳይ ጾታ ባላቸው ሰዎች መካከል የሚፈጸም ወሲብ)፤ ከእንስሳ ጋር የሚፈጸም ወሲብ (ከእንስሳ ጋር ወሲብ መፈጸም) የመሳሰሉትንና ሌሎች ርኩስ ድርጊቶችን መፈጸም፤ በእግዚአብሔር ፊት እጅግ አስጸያፊ ነው። በዘሌዋውያን 18 እና 20÷10-20

እግዚአብሔር ርኵስ የሆኑትና ክፋድ ቅጣት የተጣለባቸው ልምዶችን ዝርዝር ይሰጠናል።

ወሲብ ብርቱ የሆነ ኀይል ነው፤ እንደ እሳት ያለ ነው። እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው እንዲያ አድርጎ በመሆኑ እሳት እውን ሊሆን የሚችል ነው። እሳት በጣም ጠቃሚ ነው። ምግባችንን ለማብሰል፣ ቤታችንንም ለማሞቅ እሳትን እንጠቀማለን። ነገር ግን ቤት በእሳት ከተያያዘ፣ ቤቱን እንዳልነበረ ሊያደርገው፣ ሰዎችንም አቃጥሎ ሊገድል ይችላል። ስለዚህ ወሲብም እንደዚሁ ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን ወንድና ሴት አድርጎ የፈጠራቸው በመሆኑ ወሲብ ሊፈጽሙ ይችላሉ። በእግዚአብሔር መመሪያ ሥር እስከ ሆነ ድረስ ወሲብ ለተጋቡ ሰዎች ከእግዚአብሔር በረከቶች ውስጥ አንዱ ነው። ከፍተኛ ዕርካታና ደስታ የሚገኝበትና ልጆች ወደ ዓለም የሚመጡበት መንገድ ነው። የእግዚአብሔርን መመሪያ ችላ በማለት የሚደረግ ከሆነ፣ ወሲብ ቤትን ያፈርሳል፤ የሰዎችንም ሕይወት ያጠፋል።

ሰዎች ከጋብቻ ውጭ ወሲባዊ ፍላጎታቸውን ለማርካት ጥረት ሲያደርጉ፣ ጋብቻዎች ይፈርሳሉ፤ ቤተ ሰቦች ይበተናሉ፤ የግለሰቦችም ሕይወት በእግዚአብሔር የፍርድ ርግማን ሥር ይወድቃል። እግዚአብሔር ኀጢአትን ይቅር ማለቱ፣ በዚህ ምድር ላይ ምንም ዐይነት የኀጢአት መዘዝ አይኖርም ማለት አይደለም። እንዲያውም የሚያስከትለው መዘዝ አስፈሪ ሊሆን ይችላል። አንድ ሰው በቀጣዓ ገንፍሎ ሌላውን ሰው ቢገድልና በኋላም ንስሓ ቢገባ እግዚአብሔር ኀጢአቱን ይቅር ሊለው ይችላል፤ ይሁን እንጂ ንስሓ መግባትና ይቅርታ ማግኘት የሞተውን ሰው ወደዚህ ዓለም ተመልሶ በሕይወት እንዲኖር አያደርጉትም። የወሲባዊ ኀጢአት ጕዳይም እንደዚሁ ነው። የንጉሥ ዳዊትን ታሪክ ስንመለከት፣ ንጉሡ ከኦሪዮ ሚስት ጋር የፈጸመውን የዝሙት ኀጢአቱን እግዚአብሔር ይቅር ቢለውም እንኳ፣ የዳዊት የቤተ ሰብ ሕይወት ከዚያን ዕለት ጀምሮ መናጋቱን ቀጠለ (2ሳሙ 12፥11-13)።

አንዳንድ ባሕሎች እንደ ወሲባዊ ኢግብረገባዊነት ያሉትን አንዳንድ የዝሙት ኀጢአቶችን አይኰንኑም። አንድ ሰው በእንዲህ ዐይነቱ ባህል ያደገ ከሆነ፣ ወሲባዊ ኢግብረገባዊነትንና ይህን የመሳሰሉትን በደሎች ያወገዘ እግዚአብሔር መሆኑን ልብ ማለት አለበት። ክርስቲያን ባሕርይውን በተመለከተ ታማኝ መሆን ያለበት ለባህሉ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ነው። የእግዚአብሔር ሕጎች ፍጹማን ናቸው፤ ጌታ ከባህል ጋር እንዲስማሙ ለማድረግ አይለውጣቸውም።

አጓጉል ስለሆነው ወሲባዊ ግንኙነት አንድ ነገር መባል አለበት። በዛሬው ጊዜ በአንዳንድ የዓለም ክፍል ብዙ ሰዎች ወደ ግብረ ሰዶም ፊታቸውን አዙረዋል። ይህ ሁኔታ እግዚአብሔር ዓለምን፣ የፈጠረበትን መንገድ ፈጽሞ ማጣመም ነው። የእንስሳት ወገን የተፈጠሩት እንኳ ወንድና ሴት ተደርገው ነው። የግብረ ሰዶም ሰዎች የእነርሱ ልምድ አማራጭ የሕይወት አካሄድ ነው በማለት ሊከራከሩ ይሞክራሉ። እውነቱ ግን እነዚህ ልምዶች በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊዎች ናቸው (ዘሌ 20፥13)። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች አጉል የሆነውን ወሲባዊ ግንኙነት የሚፈጽሙ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ለኀጢአታቸው አሳልፎ እንደሚሰጣቸውና፣ የእግዚአብሔርንም ፍርድ በራሳቸው ላይ እንደሚያመጡ ይናገራል (ሮሜ 1፥24፡26)። እግዚአብሔር በአጉል የወሲብ ኀጢአታቸው የተነሣ የሰዶምንና የገሞራን የጥንት ከተሞች ፈጽሞ ያጠፋቸው መሆኑን ማስታወስ ይኖርብናል (ዘፍ 19፥1-25)። እግዚአብሔር ዛሬም አልተሰወጠም።

ግብረ ሰዶምን የሙጥኝ ብሎ በያዘ ሰው ላይ ተገቢ የሆነው ክርስቲያናዊ አመለካከት ምን መሆን አለበት? የእግዚአብሔር ሰዎች በግብረ ሰዶምና በሌሎች ርኩስ ተግባሮች ስተጠመዱት ሰዎች ምንጊዜም ፍቅር፣ ትዕግሥትና ርኅራኄ ማሳየት አለባቸው። ክርስቲያኖች እነዚህን ሰዎች መርዳትና በክርስቶስ ነፃ እንዲወጡ ማድረግ ይገባቸዋል። ይህ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ግን ክርስቲያኖች ይህ አጉል ድርጊት ስሕተት የለበትም የሚለውንና በመስፋፋትም ላይ የሚገኝ ውን ሐሳብ ወይም በዚህ ጎራ የተሰለፉት አጓጉል ሰዎች የተለየ መብት ሊሰጣቸው ይገባል የሚለውን ሐሳብ በቸልታ ማለፍ የለባቸውም። ይህ ጎጢአትና እንደ ሌሎቹ ወሲባዊ ጎጢአቶች የእግዚአብሔር ፍርድና ቊጣ የሚያርፍባቸው ናቸው (1ተሰ 4÷3-6)።

ፍትወትና የሚያስከትለው መዘዝ፤ ፍትወት የሚከሠተው የሰዎች ትክክለኛ ባሕርይ በጎጢአት ሲበከል ነው። ፍላጎቶች በራሳቸው መጥፎ አይደሉም። ፍላጎታችን የመጣው እግዚአብሔር እንዲያ አድርጎ ስለ ሠራን ነው። ለምሳሌ ሰዎች በሕይወት ይኖሩ ዘንድ እግዚአብሔር ምግብ እንዲበሉ አድርጎ ፈጠራቸው። ሰው በተራበ ጊዜ ምግብ ለመብላት መፈለጉ ጎጢአት አይደለም። በስግብግብነት ምግብን መፈለግ ግን፣ ከጤነኛ ምግብ ፍላጎት ያለፈ አስነዋሪ ባሕርይ ነው። ይህም የፍትወት አንድ ገጽታ ነው።

እግዚአብሔር ወንዶችንና ሴቶችን ጤነኛ በሆነ መልኩ በአካልና በስሜት ረገድ እርስ በርስ እንዲሳሳቡ አድርጎ ፈጠራቸው። ይህ መማረክ ጎጢአት አይደለም። በተቃራኒ ጾታ መማረክ እግዚአብሔር ሰውን በመጀመሪያ ሲፈጥር እንዲኖር አድርጎ ያቀደው ነው፤ እግዚአብሔርም የፈጠረውን ሁሉ መልካም ነው ብሎታል (ዘፍ 1÷31)። ችግሩ ከእግዚአብሔር የተሰጠን የወሲብ ፍላጎት በጎጢአት ተበክሎአል። በዔደን የአትክልት ስፍራ ከተከሠተው ውድቀት ጀምሮ ሰዎች ፍላጎታቸውን ጨምሮ በማንኛ ውም አቅጣጫ ያለው ተፈጥሮአቸው የተበከለ ሆኗል። ከጎጢአተኛ ተፈጥሮአቸው የተነሣ ወንዶችና ሴቶች፣ እግዚአብሔር ሆነው እንዲገኙ ባቀደላቸው መሠረት በትዳር አጋሮቻቸው ርካታ አያገኙም ከዚህ ይልቅ በፍትወት ሌሎችን ወንዶችና ሴቶች ይሻሉ።

ፍቅር ወይስ ፍትወት፤ ብዙ ወጣቶችን የሚያስችግረው አንድ ጥያቄ በፍቅርና በፍትወት መሀከል ያለው ልዩነት ነው። ፍቅርና ፍትወት ሁለቱም ብርቱ ወሲባዊ ፍላጎትን ያካትታሉ። ታዲያ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? አንድ ሰው የእርሱ ወይም የእርሷ ፍላጎት፣ ፍቅር ወይም ፍትወት መሆኑን ለማወቅ አንዱ ቀላል መለኪያ፣ ራስ ወዳድ የመሆን ወይም ያለመሆን ጕዳይ ነው። አንድ ወንድ አንዲትን ልጃገረድ በቅዱስ ፍቅር የሚወዳት ከሆነ፣ ለእርሷ ያለው ፍላጐት ራስ ወዳድነት የሌለበት ነው። ከጋብቻ በፊት ከእርሱ ጋር ወሲብ እንድትፈጽም በማድረግ፣ የሚወዳትን ልጅ ለማስነወር ወይም ለማዋረድ አይፈልግም።

ይህ መርሕ የንጉሥ ዳዊት ልጅ አምኖን ለአባቱ ልጅ ለትዕማር በነበረው የፍትወት ታሪክ ላይ ጕልሕ ሆኖ ይታያል (2ሳሙ 13÷1-12)። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ትዕማር አምኖንን ለማግባት ፈቃደኛ ነበረች፤ አምኖን ግን ፍላጎቱን ለማርካት ትዕማርን እስከ ጋብቻ ድረስ ለመታገሥ ፈቃደኛ አልነበረም (2ሳሙ 13÷13-14)። አምኖን ለትዕማር የነበረው ስግብግብነት የሞላበት ፍላጎት ፍቅር ሳይሆን ፍትወት ነበር። በፍቅርና በፍትወት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

- ፍትወት ለማግኘት ሲፈልግ ፍቅር ግን ለመስጠት ይፈልጋል።
- ፍትወት ራስ ወዳድ ሲሆን፣ ፍቅር ግን ራስን የሚክድ ነው።

ፍትወት ለመቆየት ፈቃደኛ አይደለም፤ ፍቅር ግን የእግዚአብሔር ጊዜ እስኪደርስ ድረስ በትዕግሥት ለመጠበቅ ፈቃደኛ ነው።

ፍቅር ለተወደደችው ሴትና ለልጆቹ እስከ ዕድሜ ልክ ድረስ ጎላፊነትን ለመሸከም ፈቃደኛ ሲሆን፣ ፍትወት ከወሲብ ጋር አብሮ የሚመጣውን ጎላፊነት ለመሸከም አይፈልግም።

ፍቅር ለተወደደችው ሴት ደስታና በጎ ነገር ሊመኝ፣ ፍትወት ግን ዕርካታን ብቻ ይሻል።

ፍቅር በተወደደው ሰው ላይ ጎፍረትን ለማምጣት ኩቶ የማይፈልግ ሲሆን፣ ፍትወት ግን በሌላው ሰው ላይ ጎፍረት ቢመጣበት ግድ የለውም።

ፍትወት ዘለቂታ የለውም፤ ፍቅር ግን እስከ ዕድሜ ልክ ይዘልቃል።

ፍትወት ከጎጢአተኛ ተፈጥሮ የመጣ ትልቅ ዕርግማን ነው ፍቅር ግን ከእግዚአብሔር የተሰጠ ትልቅ በረከት ነው።

ከፍትወት እንድንሸሽ ታዘናል (2ጢሞ 2÷22)፤ ይሁን እንጂ ባሎች ሚስቶቻቸውን እንዲወዱ ታዘዋል (ኤፌ 5÷25)።

ፍትወት ማንኛውንም ሰው ይጐዳል፤ ፍቅር ግን ሰውን ይፈውሳል፤ ያግዛልም።

ፍትወት ሐዘንን፣ መራራነትንና ጎፍረትን ያመጣል፤ ፍቅር ግን ደስታን፣ ሐሤትንና እርካታን ያስገኛል።

የፍትወት ምንጭ የሰው ጎጢአተኛ ተፈጥሮ ነው፤ የፍቅር ምንጭ ግን የእግዚአብሔር ቅዱስ ባሕርይ ነው።

የፍትወት ችግር ባላገቡ ወንዶችና ሴቶች ብቻ የተወሰነ አይደለም።የተጋቡ ሰዎችም በፍትወት ብዙ ጊዜ እየተቸገሩ ይገኛሉ። ያገቡ ሰዎች ከፍትወት የሚያመልጡበት አንዱ መንገድ ዘወትር ወሲብ በመፈጸም ነው (1ቆሮ 7÷3-5)። በአንዳንድ የአፍሪካ ጋብቻዎች፤ ልጅ ተወልዶ ሁለት ዓመት እስኪሞላው ድረስ ወይም ከዚያ በላይ እናቶች ከባሎቻቸው ጋር ወሲብ ለመፈጸም አይፈልጉም። ይህ ጥሩ አይደለም። ብዙ ባሎችን ወደ ፍትወትና ወደ ኢግብረገባዊነት ይመራቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤ 'በጸሎት ለመትጋት ተስማም ታችሁ ለተወሰነ ጊዜ ከልሆነ በስተቀር፤ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ፤ ራሳችሁን ባለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ እንደገና አብራችሁ ሁኑ' (1ቆሮ 7÷5)።

ሚስት አረግዛለሁ ብላ በመሥጋት፣ ከባሏ ጋር ወሲብ ለመፈጸም ፈቃደኛ ካልሆነች እርሷና ባሏ ስለ ቤተ ሰብ ዕቅድ ጠቃሚ ምክር ሊሰጥ የሚችለውን ክርስቲያን ዶክተርን ወይም የመድኀኒት ባለሙያን ወይም የጤና ባለሙያን ማማከር አለባቸው። በዕቅድ መሠረት የሆነ ዕርግዝና በብዙ መንገድ ቤተ ሰብንና ጋብቻን ሊጠቅም ይችላል።

አንዳንድ ባሎች የሚስቶቻቸውን ስሜት ይጐዳሉ፤ ምክንያቱም እነርሱን ከመውደድ ይልቅ የፍትወት ፍላጎታቸውን ለማርካት ይጠቀ ሙባቸዋል። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ባሎችም ሚስቶቻቸውን እንዲወዱ እግዚአብሔር ያዛል (ኤፌ 5÷25)፤ ወንዶችን ግን ከፍትወት (ከዝሙት) እንዲሸሹ ያስጠነቅቃል (2ጢሞ 2÷22)። ይህም ማለት ባሎች በተለይ በወሲባዊ ግንኙነታቸው ሂደት ውስጥ ለሚስቶቻቸው ከፍተኛ ትዕግሥትና ጨዋነት ማሳየት አለባቸው። በሚጠናኑበት ጊዜ ያሳየውን ርኅራኄ፣ ፍቅርና ትዕግሥት ከጋብቻም በኋላ የሚያደርግ ሰው ደስተኛ ሚስት ትኖረዋለች። ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሁሉ፣ ከራስ ወዳድነት ተላቆ ሚስቱን በእውነት ለመውደድ ጥረት የሚያደርግ ባል፣ ሚስቱ ደግሞ ለእርሱ እሺ ባይና እርሱንም የምትወድ ሆና ያገኛታል።

ላላገቡ ሰዎች የፍትወት ችግር በጣም የጐላ ሊሆን ይችላል። ይህን ፈተና ቀላል ለማድረግ የሚረዱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁለት መርሖች አሉ። የመጀመሪያው መርሕ ክርስቲያኖች በሚያዩት ነገር ራሳቸውን መግዛት (መቈጣጠር) መቻል አለባቸው። በተለይ ወንዶች በሚያዩት ነገር በቀላሉ ይማረካሉ። ንጉሥ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ዝሙት ወደ መፈጸም ደረጃ የደረሰው ስትታጠብ ሳለ ወደ እርሷ በመመልከቱ ነው። ኢዮብ፣ «ወደ ኰረዳዪቱ ላለመመልከት ከዐይኔ ጋር ቃል ኪዳን ገብቻለሁ» አለ (ኢዮብ 31÷1)። ኢየሱስም፣ «ሴትን በምኞት ዓይን የተመለከተ ሁሉ በልቡ ከርሷ ጋር አመንዝሮአል» ብሎአል (ማቴ 5÷28)። ክርስቲያኖች ስለሚያነቧቸው መጻሕፍት፣ ስለሚያዩአቸውም ፎቶግራፎችና ፊልሞች በጣም መጠንቀቅ አለባቸው።

ሁለተኛው መርሕ በአካል ከመነካካት ጋር የተያያዘ ነው። በወሲባዊ ስሜት እርስ በርስ መነካካት ወንዶችንና ሴቶችን በመቀስቀስ ለአጉል ፈተና ሊዳርግ ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ፣ «ሰው ወደ ሴት ባይደርስ መልካም ነው» ይላል (1ቆሮ 7÷1)። ወንዶች ከወጣት ሴቶች ጋር በሚሆኑበት ጊዜ ራሳቸውን መግዛት አለባቸው። መጽሐፍ ቅዱስ እኅቶቻቸው እንደ ሆኑ በመቊጠር በፍፁም ንጽሕና ሊያስተናግዷቸው ይገባል ይላል (1ጢሞ 5÷1-2)። ወንድ ሚስቱ ካልሆነች ሴት ጋር ብቻውን መሆኑ ጥሩ አይደለም። *[Used with permission of the author]*

ለብቻ መቆም
How to Stand Alone, 1983, Institute in Basic Youth Conflicts

ዳንኤል ገና በዐሥራዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ እያለ፣ ፈሪሀ እግዚአብሔር ካለበት ከወላጆቹና ከቤተ ሰቡ ፍቅር ተለይቶ ወደ ክፉዋ የባቢሎን ከተማ በምርኮ ተወሰደ ነበር። በአረማዊ አምላኪ ስም እንዲጠራ ስሙ ተቀይሮ ነበር። ሥጋዊ የሆነና እግዚአብሔር የለሽ ሥርዐተ ትምህርት እንዲከተልም ትምህርት ቤት ገብቶ ነበር። ከእርሱ ጋር ተማርከው የነበሩትና የዕድሜ እኩያዎቹ የሆኑት ብዙዎቹ ያደጉበትን እምነትና ባህል ትተው የአረማዊ ሕዝብን ልማድ ተከተሉ። ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ በጨካኞችና ምሕረት በሌላቸው ሰዎች እጅ በተዘጋጀ ዕረፍት በሚነሣ ሥቃይ ውስጥ ሊያስገባ በሚችል ሁኔታ ውስጥ ወድቆ ነበር።

አንድ ሰው በእግዚአብሔር ላይ የሚማረርበት ምክንያት አለው ከተባለና ያደገበትንም ግብረገባዊ መመሪያ መተው ካለበት ያ ሰው ዳንኤል ነበር። ነገር ግን ዳንኤል ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ብቻውን ጸንቶ በመቆም ረገድ ድንቅ ምሳሌነት ካላቸው ሰዎች መካከል አንዱ ሆነ። ዳንኤል በእያንዳንዱ ፈታኝ ሁኔታ ብቻውን በቆመበት ጊዜ ሁሉ የተነሣበትን ዐላማ የሚጥል ይመስል ነበር፤ እግዚአብሔር ግን ዳንኤል ያለፈባቸውን ፈተናዎች ሁሉ የላቀ ሞገስንና መንፈሳዊ አስተዋይነትን ለእርሱ ለመስጠት ተጠቀመባቸው።

እግዚአብሔር በማንኛውም ዘመን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሖችን የተገነዘቡና የቱንም ዐይነት ዋጋ የሚያስከፍል ፈተና ቢደርስባቸው፣ ለመርሖቹ ጸንተው ለመቆም ዐላማ ያደረጉ እንደ ዳንኤል ያሉ ወንዶችንና ሴቶችን ይፈልጋል። ዳንኤልን ለመሆን በመረጥን ጊዜ በዙሪያችን ያሉትን ሰዎች በእጅጉ ለመማረክና ለምናገለግለውም አምላክ የላቀ ሞገስና ክብር ለማምጣት ብቁ ለሆነ አካሄድ ሕይወታችንን አመች አድርገናል ማለት ነው።

ሰው ብቻውን ፀንቶ ለመቆም መሠረት የሚሰጡ ሦስት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፅንሰ ሐሳቦች፤

እነዚህ ፅንሰ ሐሳቦች በብቸኝነት ጊዜ ለእውነት ፀንቶ ለመቆም የሚሰጠው ትምህርት መሠረቶች ናቸው። እያንዳንዳቸውን በሚገባ

መረዳትና ከአያንዳንዱ ትግበራም ጋር ተዛምደው እንዲታዩ ያስፈልጋል።

ሀ. እግዚአብሔር የፈጠረን የአንዲት ሴት ባል ወይም የአንድ ወንድ ሚስት እንድንሆን አድርጎ ነው፤ ይህ የመጀመሪያ ፅንሰ ሐሳብ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮ በጋብቻ አንድ ባደረጋቸው ጊዜ በራሱ በእግዚአብሔር ትምህርት ሆኖ ተሰጠ። ጋብቻቸው የዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን እንዲሆን ነበር (ዘፍ 2÷24)። የአንዲት ሴት ባል ወይም የአንድ ወንድ ሚስት መሆን ማለት አንድ ጊዜ ካገባን በኋላ፣ ከሌሎች ጋር ለመጋባትም ሆነ ለመቀራረብ ከቶ አናስብም ማለት ነው። ይህም ማለት በጋብቻችን አንድነት ላይ ምንም ነገር ጉዳት ማድረስ እንዳይችል ለማድረግ ከትዳር ጓደኞችን ጋር አብረን እንሠራለን ማለት ነው።

የአንዲት ሴት ባል ወይም የአንድ ወንድ ሚስት ማለት ወደፊት ለምናገባው ሰው በግብረገብ ረገድ ንጹሕ መሆን ነው፤ ሌላዋ ሴት ወይም ሌላው ወንድ ግን የቱንም ያህል ማራኪ ትሁን (ይሁን)፣ «ባዕድ ሴት» ወይም «ባዕድ ወንድ» ነው ማለት ነው (ምሳሌ 7÷4-5፤ 21÷8 ይመልከቱ)። የአንዲት ሴት ባል ወይም የአንድ ወንድ ሚስት መሆን ማለት፣ የትዳር ጓደኞችን ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ቀዳሚ ስፍራን እንዲይዝ እናደርጋለን ማለት ነው (1ቆሮ 7÷33)። ለዚህ ፅንሰ ሐሳብ ታማኝ ሆኖ መገኘት፣ መንፈሳዊ መሪ መሆን ለሚፈልግ ወንድ ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልጋይ መሆን ለምትፈልግ ሴት መሠረታዊ ግዴታ ነው (1ጢሞ 3÷2፤ 5÷9)።

ትግበራዎች

I. ከሥርዓት ውጭ የሆነ ልብስ መለበስ የለበትም፤ አንድ የተስተካከለ ልብስ ከሥርዓት ውጭ ነው የሚባለው፣ በሞዱ፣ በቅዱ፣ በቀለሙና በልክነቱ ተመልካቾችን ወደ ፊታችን እንዳያዩ የሚያደርግ ሆኖ ሲገኝ ነው። አንዳንዶች ሌሎች ሰዎች የእነርሱን መልክ እንዲያደንቁ አድርገው ቢለብሱ፣ ተቀባይነትን እናገኛለን ብለው በተሳሳተ ሁኔታ ያምናሉ። እንዲህ ሲያደርጉም በመሰሪ ተግባራቸው በዙሪያቸው ያሉትን «እያታለሉ» ነው። ማታለል ደግሞ ማጭበርበር ነው። በቀረበልን በዚህ ማስረጃ መሠረትም ማታለል ማለት በጽድቅ እካሄድ ማርካት የማንችለውን የሌሎችን ሥጋዊ ስሜት መቀስቀስ ማለት ነው። እግዚአብሔር ለተታለሉት የሚበቀል መሆኑን ያስጠነቅቃል (1ተሰ 4÷6)።

2. የፍትወት ዐይን መኖር የለበትም፤ እግዚአብሔር ወደ ሕይወታችን ላመጣት የትዳር ጓደኛችን ያለንን የደስታ ስሜት ለመጠበቅ እንዲቻል፣ በፍትወት ዐይን ወደ ሌሎቹ መመልከት የለብንም። በፍትወት ዐይን ሌሎችን መመልከት፣ የአንድ ሴት ባል ወይም የአንድ ወንድ ሚስት የሚለውን የእግዚአብሔርን ሐሳብ መተላለፍ ስለሆነ በፍትወት ዐይን ወደ ሌላ ሰው መመልከትን ከማመንዝር ጋር አንድ እንደ ሆነ ኢየሱስ ሲናገር፣ «እኔ ግን እላችኋለሁ፤ ሴትን በምኞት ዓይን የተመለከተ ሁሉ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሮአል።» ብሏል (ማቴ 5÷28)። ይህም ማለት አንድ ሰው ስሜት ቀስቃሽ ሥዕሎችን፣ ግብረ ሰዶማዊ መጽሔቶችን፣ የብልግና ፊልሞችን ወይም ከሥርዓት ውጭ የለበሱ ሰዎችን እንድንመለከት ቢጠይቀን፣ «ሕይወቴን ለኢየሱስ ሰጥቻለሁ፤ ያን ማድረግ አልችልም» ማለት አለብን።

አንድ ክርስቲያን ከሚያጋጥሙት ዐበይት ጦርነቶች አንዱ ፍትወታዊ ሐሳብን ማሸነፍ ነው፤ ምክንያቱም ድብቅ ዐላማን፣ በገሐድ የሚታዩ ድርጊቶችንና የሕይወትን አቅጣጫ የሚወስነው የልባችን ሐሳብ ነው። በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር፣ «አእምሮንም ሁሉ

እየማረክን ለክርስቶስ እንዲታዘዝ» እናደርግ ዘንድ ይፈልግብናል (2ቆሮ 10÷5)። ኢዮብ የሚከተለውን ውሳኔ በመወሰን አስፈላጊ ከሆነ ርምጃ ላይ ደረሰ፤ «ወደ ኮረዳዪቱ ላለመመልከት ከዐይኔ ጋር ቃል ኪዳን ገብቻለሁ» (ኢዮብ 31÷1)።

3. ከጋብቻ በፊት እንኳ ቢሆን በዝሙት ርኵሰት መጠመድ አይገባም፤ እግዚአብሔር ከተቃራኒ ጾታ ጋር የሚፈጸመው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለጋብቻ ሕይወት መቆጠብ ያለበት መሆኑን በማሳሰብ ግልጽ ትምህርት ሰጥቶአል። ይህ ትምህርት ሲከበር ታላላቅ ሽልማቶች ይመጣሉ፤ ሲጣስ ደግሞ ከባድ መዘዞች ይከተላሉ። ከጋብቻ በፊት ተገቢ ያልሆነ መተሻሸት ለማድረግ ወይም በሩካቤ ሥጋ ለመጠመድ ሲባል፣ ግብረገባዊ ደንብ ዝቅ ከተደረገ፣ የራስ ክብር ይዋረዳል፤ ግንኙነት ይበላሻል፤ በጋብቻ የተገኘው አንድ አካልነት ይረክሳል፤ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረት ዝቅ ይላል፤ የጤናም መጓደል ይገጥመናል።

ኢግብረገባዊነት ጊዜያዊ ደስታን እንደሚሰጥ ጥርጥር የለውም፤ በመጽሐፈ ምሳሌ እንዲህ ይላል፤ «የስርቆት ውሃ ይጣፍጣል፤ ተሸሽገው የበሉት ምግብ ይጥማል» (ምሳ 9÷17)፤ በኋላ ግን ያ ደስታ ወደ መራር ሐዘን ይለወጣል። በዚህ ምክንያት ጳውሎስ፣ «ከወጣትነት ክፉ ምኞት» እንሸሽ ዘንድ ያስጠነቅቀናል (2ጢሞ 2÷22)።

ብዙ ጥንዶች ለመጋባት ዐቅደናልና ወሲብ መፈጸም ይቻላል ከሚል መደምደሚያ ላይ በመድረስ ንጽሕናቸውን አጥተዋል። ይሁን እንጂ ከጋብቻ በፊት ግንኙነት ከተፈጸመ በኋላ፣ የሰዎችን ማንነት እንዲሁም የነበራቸው ሐሳብና ዕቅድ ብዙ ጊዜ ይለወጣል።

አሁን ባለንበት የሴሰኝነት ዓለም (ዘመን) የአባለ ዘር በሽታ ከወረርሽኝ ደረጃ ላይ ደርሶአል፤ አዲስ «መድኀኒት» በተሠራ ቍጥር መድኀኒቱ የማያሸንፋቸው የባሰ አጥፊ የሆኑ በሽታዎች ስለሚከሠቱ የአባለ ዘር በሽታዎች ከቶ አይጠፉም በማለት የሕክምና ተመራማሪዎች በማስጠንቀቅ ላይ ናቸው። ወጣቶች ከአመንዝራ ሴት እንዲሸሹ እግዚአብሔር ማስጠንቀቁ በጣም ተገቢ ነው፤ «መንገድህን ከእርሷ አርቅ ... ይኸውም ... በዕድሜህ መጨረሻ ታቃሥታለህ፤ ሥጋህና ሰውነትህ ሲከዳህ» (ምሳ 5÷8-11)።

በአሁኑ ጊዜ ሄርጴስ አንድኀና ሄርጴስ ሁለትን እንዲሁም ኤድስን ጨምሮ እስከ አሁን ፈዋሽ የሆነ መድኀኒት ያልተገኘላቸው ዐሥራ አምስት ዐይነት የአባለ ዘር በሽታ ዝርያዎች አሉ። እነዚህም እግዚአብሔር ግብረገባዊ ሕጎቹን የሚያስከብርባቸውና ቅዱሳት መጻሕፍትንም የሚያስፈጽምባቸው የእርሱ መሣሪያዎች ናቸው፤ «አትታለሉ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ያንኑ ያጭዳል። ሥጋዊ ምኞቱን ለማርካት የሚዘራ፣ ከሥጋ ጥፋትን ያጭዳል (ገላ 6÷7-8)።

4. ተገቢ ካልሆነ ሰው ጋር ፍቅር መገለጽ የለበትም፤ የአንዲት ሴት ባልና የአንድ ወንድ ሚስት መሆን የሚለውን ፅንሰ ሐሳብ ሊያጠፋ የሚችል እንደ ግብረ ሰዶም ያለ ነገር የለም። ይህ ከማንኛውም ከእግዚአብሔር ዕቅድ ጋር የሚጣረስ ነው። ይህ ክፉ ልምድ ከተፈጥሮ ከራሱ ጋር እንኳ የሚቃረን ሲሆን ይህን በሚያደርጉት ላይ እግዚአብሔር ልዩ ፍርድ እንደሚፈርድባቸው ያስጠነቅቃል (ሮሜ 1÷26-27)። ግብረሰዶማዊነት የሰዎች መደብ አይደለም፤ ነገር ግን የኀጢአት ዐይነት ነው። እያንዳንዱ ሰው ኀጢአተኛ ተፈጥሮን ይዞ የተወለደ ስለሆነ ለማንኛውም ወራዳ የፍቅር ስሜት የተጋለጠ ነው። ሆኖም ግን በዚህ ክፉ ልምምድ ውስጥ ለመግባት፣ አንድ ሰው በመጀመሪያ በልቡ ላይ የተጻፉትን የእግዚአብሔር ግብረገባዊ ሕጎች መተው ይኖርበታል (ሮሜ 2÷15 ይመ)፤ ከዚያም

በሥጋዊ «ደስታ» ውስጥ ይጠመዳል (ሮሜ 1÷24 ይመ።

ሰ. እግዚአብሔር ሥልጣንን መከለያ ጥላችን እንዲሆን አድርጎ ሠራው፤ የሰይጣን ዐላማ እግዚአብሔር ለሕይወታችን የሰጠንን ክሂል እንዳልነበረ ማድረግ ነው። ሰይጣን ማጥቃት የጀመረው በዔደን የአትክልት ስፍራ ሲሆን፣ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ይህን ድርጊቱን አቋርጦ አያውቅም። ለእርሱ ውጤታማ የሆነው ዕቅዱም እግዚአብሔር በእኛ ላይ ሥልጣን እንዲኖራቸው ባደረጋቸው በወላጆች፣ በመምህራኖች፣ በቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ በመንግሥት ሹሞችና አሠሪዎች ላይ አናምፅ ዘንድ እኛን ማነሳሳት ነው።

የሚያምፁት ሁሉ እነዚህ የበላይ ጎላፊዎች እግዚአብሔር ለራሳችን ጥቅም ሲል ጥላ አድርጎ ይጠብቁን ዘንድ ያስቀመጣቸው መሆኑን መገንዘብ አይችሉም። እኛ በእነርሱ ጥላ ሥር እስካለን ድረስ ሰይጣን በመንፈሳዊ ሕይወታችን ላይ የሚሰነዝረው አጥፊ ጥቃት አይሳካም። ይሁን እንጂ ከጎላፊዎች ጥበቃ ሥር እንድንወጣ ሊያታልለን ከቻለ፣ ራሳችንን ለግዛቱና ለሥልጣኑ እናጋልጣለን። እግዚአብሔር እንዲህ በማለት የሚያስጠነቅቀን በዚህ ምክንያት ነው፤ «ዐመፅ እንደ ጥንቁላ ያለ ኀጢአት ነው!» (1ሳሙ 15÷23)። አንዳንዶች በእግዚአብሔር ሥልጣን ላይ ሊያምፁና ከሥልጣኑም እናመልጣለን ብለው ሊያስቡ ይችላሉ። ብዙ ጊዜ ዐመፅ እኛ ባልጠበቅነው መንገድ የከፋ መዘዝ እንደሚያመጣ ሳይገነዘቡ ይቀራሉ፤ «ኀጢአታችሁ እንደሚያገኛችሁም ዕወቁ» (ዘኍ 32÷23)።

እግዚአብሔር ከሰይጣን ግዛት ጋር አንዳችም ግንኙነት እንዳይኖረን ያስጠነቅቀናል። ይህም በመተት ውስጥ መሳተፍ አይገባንም ማለት ነው። በመተት ኀይል ውስጥ ለገቡት አስደንጋጭ የሆነ የመንፈሳዊ ባርነት ገጠመኝ ነው። በመተት ተግባር ተሳታፊ የሆኑት በአ እምሮ ዅከት ማለትም ምክንያት የለሽ በሆነ ፍርሃትና ሊገለጽ በማይችል የአእምሮ ጭንቀት ውስጥ ያልፋሉ። በማንኛቸውም የመተት ተግባር ውስጥ የተጠመድህ ከሆንህ ለእግዚአ ብሔር ተናዘዘው፤ ይቅር እንዲልህ፣ እንዲያ ነጻህ፣ ከሰይጣን ኀይልም ነጻ እንዲያወጣህ ለምነው። በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስምና በእርሱ ደም ተሸፍነህ ጸልይ (1ዮሐ 1÷9 ይመ)።

ሐ. እግዚአብሔር ሰውነታችንን የእርሱ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን አድርጎ ሠራው፤

ሰውነታችን የራሳችን አለመሆኑን እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በተደጋጋሚ ያሳስበናል። ይኸው ሰውነት በእግዚአብሔር ተፈጠረ፤ በድነትም ውስጥ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደም ተቤዠ። እግዚአብሔር ሰውነታችንን የሚያረክሰውን ወይም ሰውነታችን እርሱን ለማክበር ባለው ክሂል ላይ አንዳች ጉጂ ነገር እንድናደርግ ወይም እንድንፈጽም አይፈ ልግም፤ «እናንተ ራሳችሁ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውስጣችሁ እንደሚኖር አታውቁምን? ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአ ብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፤ ያም ቤተ መቅደስ እናንተ ናችሁ» (1ቆሮ 3÷16-17)።

ሰይጣን የእኛን ሰውነት የሚጠላበትና እንድናረክሰው የሚፈልግበት ቢያንስ ቢያንስ ሦስት ምክንያቶች አሉ፡- (1) የእኛ ሰውነት በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ነው፤ ስለዚህ አንድ ቀን ሰይጣንን ሙሉ በሙሉ ድል ስለሚነሣው ጌታ፣ የማያቋርጥ ማሳሰቢያ ነው። (2) የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነው። የዚህ ቤተ መቅደስ ተግባርም አምልኮና ጸሎት

ለሰይጣን ላይሆን ለፈጣሪ አምላክ የሚቀርብበት ነው። (3) እያንዳንዱ ብልትም በሰይጣን ላይ ጠላት ሆኖ የሚነሣ መሣሪያ ነው። እጆቻችን፣ ዐይኖቻችን፣ አፋችን፣ ጆሮዎቻችንና እግሮቻችን ለእግዚአብሔር ሊሰጡ፣ በሰይጣን ዕቅድና መርሐ ተግባር ላይ ብርቱ የጽድቅ መሣሪያዎች ይሆናሉ።

ብቻህን ለመቆም ቍርጥ ውሳኔ ማድረግ

የሚያስገኘው በጎ ነገር፣ እግዚአብሔር ብርቱ መሆኑን በአንተ በኩል ራሱን ይገልጻል። ከፍተኛ ነፃነት ይሰጥሃል፤ ከዓለም ጋር ተስማምቶ ከመኖር ይልቅ ከዓለም ትርቃለህ። ሕይወትህ ለሌሎች አርአያ ይሆናል። ዘላለማዊ ሽልማትን ታተርፋለህ። *[Used with permission of Institute in Basic Youth Conflicts]*

እስከ ጋብቻ ድረስ መቆየት ለምን ያስፈልጋል? የአንድ ሰው ብቻ የትዳር ጓደኛ መሆን ለምን ያስፈልጋል? አሁን በደረስኩበት የዕድሜ ዘመን ወሲብ ለምን አልፈጽምም?
Jim Burgen, What's the Big Deal Abut Sex: Loving God's Way, 1999, Standard Publishing Co., pp. 39-53

ከሞላ ጐደል ሁሉም ወጣቶች እንዲህ ይላሉ፤ «አይሆንም ማለት እንችል ዘንድ እንፈልጋለን፣ አይሆንም እንዴት ማለት እንደምንችል አግዙን፤ ከመሸነፍ ይልቅ እንድንታገሥ ሊያሳምነን የሚችል የላቀ ምክንያት ስጡን።»

ይህ መመለስ ያለበት ትልቅ ጥያቄ ነው! ይኸውም ለምን? እስከ ጋብቻ መቆየት ለምን ያስፈልጋል? እስከ ዕድሜ ልክ ከአንድ ሰው ጋር በመኖር የአንድ ሰው የትዳር ጓደኛ መሆንስ ለምን ያስፈልጋል? አሁን ወሲብ ለምን አይፈጸምም? መልስ ሊሆኑ የሚችሉትን አንዳንዶቹ ሐሳቦች እስቲ እንመልከት!

ልትሞት ስለምትችል ነዋ! ብታምንም ባታምንም ይህ አጥጋቢ መልስ አይደለም። ፍርሃት ውጤታማ የሆነ ማገጃ አይደለም። እስቲ እውነታዎችን እንመልከት፦ በመጀመሪያ ደረጃ ኮንዶሞች ከስድስቱ ውስጥ በአንዱ እጅ አይከላከሉም፤ ይህም በጣም የሚያስደንቅ አይደለም፤ የኮንዶሙ መጠቅለያ እንኳ ኮንዶም በሽታን ሙሉ በሙሉ መከላቶ ለማስቀረት ዋስትና አይሰጥም ይላል። «ሥጋት የሌለበት ወሲብ» ወይም «በብልጠት የሚፈጸም ወሲብ» የሚለው ቀልድ ነው! ልብ የምትሉ ከሆነ መገናኛ ብዙኀን በአሁኑ ጊዜ፣ «አደጋ የሌለበት ወሲብ» እያለ በማስተዋወቅ ላይ ይገኛል።

በሁለተኛ ደረጃ ብዙ ወንዶች አዘውትረው በኮንዶም አይጠቀሙም፤ ያነጋገርኳቸው ብዙ ወንዶች፣ «ለማስታወስ እሞክራለሁ» በማለት ቃል ገብተዋል። ሁለት ሰዎች ወሲብ ለመፈጸም ተዘጋጅተው ሳለ፣ ከሁለት አንዳቸው፣ «አዝናለሁ፤ ኮንዶም አላመጣሁም» ቢል፣ ወሲብ ላለመፈጸም ሁለቱም የሚስማሙበት ጊዜ ከስንት አንድ ነው።

በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ከ100 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎች በኤች አይ ቪ ይያዛሉ፤ ወይም ይህንኑ ያህል ይሞታሉ። ወይም በየ54 ሰከንዱ ጤነኛ የነበረው ሰው በኤች አይ ቪ ይያዛል፤ በየ9 ደቂቃው ከኤድስ የተነሣ አንድሰው ይሞታል። በአሁኑ ጊዜ በኤድስ ከተያዝህ የሚያድንህ መድኀኒት የለም። የባለው ጉድ ደግሞ ለዐሥር ዓመትና ወይም ከዚያ በላይ ቫይረሱ ያለብህ ሰው መሆንህን ልብ ላትል ትችላለህ። በዚህ ጊዜ ብዙዎች ያገቡ ሰዎች ይሆናሉ፤ ምናልባትም ልጆች ሊወልዱ ይችላሉ፤ ከቫይረሱ ጋር የምትኖር ሰው ከሆንህ፣ የቤተ ሰብህ አባሎች ሁሉ በበሽታው ሊያዙ ይችላሉ።

በቅርቡ የዛሬ ዐሥር ዓመት ክርስቲያን የሆነን ሰው አገኘሁ። በክርስቶስ ካመነበት ጊዜ ጀምሮ ከወሲብ ፊጽሞ የታቀበ ጥሩ ተሰጥኦ ያለው የመዝሙር ግጥም ጸሓፊና የሙዚቃ ባለሙያ ነው። በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ እርሱ የጻፋቸውን የአምልኮ አዝማቾች ዘወትር እንዘምራለን። ከጥቂት ሳምንታት በፊት

ሲመረመር ከኤድስ ደረጃ የደረሰ ሕመምተኛ ሆኖ ተገኘ። ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት የፈጸመው የወሲብ ድርጊት ይህን መዘዝ አስከትሎበታል። እግዚአብሔር ምንጊዜም ጎጢአትን ይቅር ይላል፤ ነገር ግን ከዓመታት በፊት ያደረግነው ምርጫ መዘዝ እስከ ሕይወት ዘመናችን ድረስ ሊከተለን ይችላል፤ ምናልባት ሕይወታችን እንዲያከትም ሊያደርግ ይችላል።

ምን እንደ ሆነ ታውቃላችሁ? የሞት ፍርሃት እንድትታቀቡ ለማድረግ በቂ ጎይል ላይኖረው ይችላል።

ሴላው ይቅር ልታረግዢ የምትችይ መሆኑ ለመታቀብ በቂ ምክንያት አይደለምን? አሁንም ለአንዳንዶች ይህ በቂ ምክንያት አይደለም። አንዳንድ ሰዎች የወሊድ መቈጣጠሪያ ክኒን እየወሰድሁ ስለሆነ ምንም አይደለም» ይሉ ይሆናል። መደበኛ ወቅትን ጠብቆ ለሚመጣ የወር አበባ ገና ላልደረሰች፣ በዐሥራዎቹ የዕድሜ ክልል ለምትገኝ ልጃገረድ ይቅርና አካለ መጠን ለደረሱ ሴቶች እንኳ ክኒኑ መቶ በመቶ አስተማማኝ አይደለም።

ከዚህ ላይ የምታነቡት ማንኛውም ነገር ወይም ከስብከት የሰማችሁት ነገር ለረጅም ጊዜ ከወሲብ እንድትታቀቡ «ፍርሃት» የሚያሳድርባችሁ አይመስለኝም። ለአንድ ሳምንት ወይም ለሁለት ሳምንት ሊሠራ ይችላል። በኤድስ የተበላሸ አሳዛኝ የሕይወት ታሪክ ልነግራችሁ እችላለሁ፤ ወይም የውርጃ ፎቶግራፍ ላሳያችሁ እችላለሁ፤ ያ ዐይነቱ ሕይወት ለእናንተ የማይገባ መሆኑንም ውሳኔ ላይ ትደርሳላችሁ። ይሁን እንጂ በፍርሃት የተቀሰቀሰው ምላሽ ውሎ አድሮ ይደበዝዛል፤ በምን ምክንያት?

ምክንያቱም በጣም ጥቂት ሰዎች በተለይም በዐሥራዎቹ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ወጣቶች በማንኛውም ሰዓት በቅርቡ ልንሞት እንችላለን ብለው ስለሚያስቡ ነው።

በጣም ጥቂት ልጃገረዶች ልናረግዝ እንችላለን ብለው ያስባሉ። ዕርግዝና እውን የሚሆነው «በሌሎች ሰዎች» ላይ ነው ተብሎ ይታሰባል። ራሳቸው በዚህ ዐይነት አጋጣሚ የተጠመዱ በዐሥራዎቹ የዕድሜ ክልል የሚገኙ ጥንዶች ሁሉ ያንኑ ተመሳሳይ ነገር በመድገም እንዲህ ብለዋል፤ «ይህ በእኛ ላይ ይደርሳል ብለን ከቶ አላሰብንም ነበር።»

የወሲብ ግፊት በጣም ብርቱ ነው። የወሲብ ፈተና ሲገጥምህ፣ ለፍርሃትህ ምክንያት መደርደር ትችላለህ። የማሰቢያ ሚዛንህንም ልትጥስ ትችላለህ። ማንም ሰው አስፈራርቶ ወሲብ እንዳትፈጽም ሊያደርግህ እንደማይችል ከማመን ደረጃ ላይ ደርሻለሁ።

ይህ ከሆነ ታዲያ መፍትሄው ምንድን ነው? ከጋብቻ በፊት ወሲብ ለምን አትፈጽምም? ይህ ከባድ ጥያቄ እንደ ሆነና ይህንም ጥያቄ ለመመለስ ከፍ ወዳለው ደረጃ መሄድ እንዳለብን አምናለሁ። እስቲ እግዚአብሔርን እንጠይቀው፤ ወንድና ሴት በማድረግ ወሲብን የፈጠረ እርሱ ነው፤ ስለዚህ ጕዳይ ምን አስቦ ይሆን?

ሰውነትህ የተፈጠረው ለትዳር ጓደኛህ ነው። እግዚአብሔር በጌደን የአትክልት ስፍራ እንዴት አድርጎ ሰውነትህን እንዳበጀው አስታውስ፤ አንድ ወንድና እንዲት ሴት አንድ አካል መሆን ነበረባቸው፤ ይህም በአካል፣ በሥነ ልቦናና በመንፈሳዊ ረገድ አንድ መሆንን ያካትታል። ይህ ትታገሥ ዘንድ በቂ ምክንያት ካልሆነ ዋና፣ የመጨረሻና የላቀ ምክንያት ስለሆነው እግዚአብሔር ላቀደው ሩካቤ *ሥጋ* መታገሥ ያስፈልጋል።

ሰውነትህ የተፈጠረው ለጌታ ነው። ሰውነትህ የተፈጠረው ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት እንዲኖረው ሆኖ እርሱ ለአሰበው ዐላማ እንዲጠቀምበት ነው። እንዲያውም ሰውነትህ የእግዚአብሔር እንጂ የአንተ አይደለም፤ እርሱ

ፈጠረው፤ እርሱ ዋጋ ከፈለለት፤ በእርሱም ውስጥ ያድራል፤ «ለመሆኑ ሰውነታችሁ በውስጣችሁ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? ይህም መንፈስ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት ነው። እናንተም የራሳችሁ አይደላችሁም፤ በዋጋ ተገዝታችኋልና፤ ስለዚህ በሰውነታችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ» (1ቆሮ 6÷19-20)።

ጥያቄ፡- ስለዚህ ከትዳር ጓደኛህ ውጪ ከሌላ ሰው ጋር በመጣመር፤ «አንድ አካል» ብትሆን ምን ይፈጠራል? መልስ፡- የወደፊት የትዳር ጓደኛህን ወደዚሁ ማጥ ጕትተህ ታስገባለህ! በአካል ደረጃ ሲታይ የኤድስ ወረርሽኝ ይህ መርሕ ትኵረት እንዲደረግበት አድርጎአል። ከአንዲት ሴት ጋር ወሲብ ስትፈጽም፤ ይህችው ሴት ከዚህ ቀደም አብራ ከፈጸመችው ከማንኛውም ሰው ጋር ወሲብ እየፈጸምክ ነው። ሽክርክሮሹ በዚህ መልኩ ይቀጥላል። ይህ እንግዲህ አካላዊ እውነታ ነው።

ነገር ግን ከዚህ በላቀ ደረጃ ላይ በሚገኘው በመንፈሳዊ አቅጣጫም ስለ ተከሠተው ሕግ መተላለፍ ልነግርህ እፈልጋለሁ። እግዚአብሔር ለአንተ ካሰበልህ ውጪ ከሌላ ሰው ጋር ወሲብ ስትፈጽም፤ ያችን ሴት ከወደፊት የትዳር ጓደኛህ ጋር ወደሚኖርህ ኀብረት ጕትተህ እያስገባሃት ነው። ይህን እንደሚከተለው ላብራራ፡-

ከጥቂት ዓመታት በፊት 'ዘ ላስት ቴም ፕቴሽን ኦፍ ክራይስት' (The Last Temptation of Christ) የሚል ርእስ ያለው ፊልም ጌታ ኢየሱስን ከአንዲት ሴት ጋር ወሲብ እንደሚፈጽም አድርጎ ቀረጸው። ብዙ ክርስቲያኖች በቊጣ ገነፈሱ። አንድ ሰው እንዲህ ያለውን ኢግብረገባዊ ነገር ጌታ ኢየሱስ ይፈጽማል ብሎ በማሰብ እንዴት በድፍረት ሊቀርጸው ቻለ! አስቲ አስቡበት፤ ግብረ ሰዶማዊ የሆነውን መጽሔት በመውሰድ፤ ጌታ በግብረ ሰዶም ሥራ ውስጥ እንደሚሳተፍ አድርጌ የክርስቶስን ፊት የሚያሳየውን ሥዕል ከአንዳንድ ገጸ ባሕርያት ላይ በማጣበቂያ ባጣብቀው ምን ይሰማችኋል? በጣም ትቈጣ ላችሁ፤ ይህ ድፍረት ነው፤ እግዚአብሔርን መሳደብ ነው፤ ዘግናኝ ነው ትሉኛላችሁ። በተሰይ እኛ ክርስቶስን እንከተላለን የምንል፤ የእርሱም ማደሪያ የሆንን ክርስቲያኖች ጓደኞችን ካልሆነች ሴት ጋር ወሲብ የምንፈጽም ከሆነ፤ ከዚያ በምን ይለያል? የፈጸምነው ነገር በቀጥታ ያንኑ ነው።

ይህ ጕዳይ እንዲሁ ሥጋዊ ተግባር ነውን? ሁለት አካሎች በወሲብ ድርጊት አንድ ላይ ከሚሆኑበት በላይ ነው። እግዚአብሔር በጋብቻ ውስጥ እንዲፈፀም ያቀደውን ከፍተኛ ግንኙነት በሌላ መንገድ ወደዚህ ደረጃ እንዲመጣና እንዲደመደም ማድረግ ነው። እግዚአብሔር ወሲብን የፈጠረው ለጋብቻ ነው፤ የባረከውም በዚያ ውስጥ ሲሆን ነው። ከዚያ ሌላ የሆነው ስሕተት ነው፤ ልክን የተላለፈ ነው ብሎታል፤ አጠንክሮም ሲናገር፤ ኀጢአት ነው ይለዋል! ከጋብቻ በፊት ወሲብ ስትፈጽም፤ የወደፊት የትዳር ጓደኛህን እያታለልክ ነው፤ የእግዚአብሔርን ሕግ በመቃረንም ዝሙት እየፈጸምክ ነው።

እስኪጋቡ ድረስ ወሲብ ከመፈጸም መታቀብ ለምን አስፈለገ? ምክንያቱም የላቀ ዐላማ አለህ፤ በዚህ ምድር ላይ እንድትኖር የተበጀኸው ሙሉ በሙሉ ለአንድ ሰው ነው። ለውነትህ የተሠራው እግዚአብሔር እንዲጠቀ ምበት ነው። እርሱ ፈጠረው፤ በደሙ ገዛው በእርሱ ውስጥ ይኖራል፤ ጠባቂውም እርሱ ነው፤እርሱም «ታገሥ!» ይላል። *[Used with Permission of Standard Publishing].*

ወሲብን የፈጠረ እግዚአብሔር ነው
Lerry Richards, How Far Can I Go? 1979
Zondervan Corp., pp. 53-61

በዐሥራዎቹ የዕድሜ ክልል የሚገኝ አንድ ክርስቲያን ስለ ወሲብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው አመለካከት ምን እንደ ሆነ በተጠየቀ ጊዜ እንዲህ በማለት ተቃውሞውን ገልጿል፤ «መጽሐፍ ቅዱስ የወሲብ መጽሐፍ አይደለም።» በአንድ በኩል ሊታይ ትክክል ነው። እንዴት ማድረግ እንደሚገባ ከመግለጽ አንፃር ከሆነ የዚህ ዐይነት መጽሐፍ አይደለም። እያንዳንዱ ዐይነት ጠባይ እንዴት መጓዝ እንዳለበት ሕግ በመስጠት ረገድም ቢሆን የዚህ ዐይነት መጽሐፍ አይደለም። ይሁን እንጂ፣ «እኔ በተለይ ምን ማድረግ እችላለሁ?» እና «ማድረግ የማይገባኝ ነገሮችስ በትክክል ምን ምን ናቸው?» በሚሉት በዐሥራዎቹ የዕድሜ ክልል ያሉትንና በሃያዎቹ የዕድሜ ክልል የሚገኙትን ወጥረው በሚይዙ ጥያቄዎች ሥር በጣም መሠረታውያን የሆኑ ጥያቄዎች ይገኛሉ።

አንዲት የዐሥራ ስድስት ዓመት ልጃገረድ እንዲህ በማለት ጻፈች፤ «ብዙ ወጣቶች ወሲብን በትክክል እንደማይረዱ፣ ምን እንደሚያመለክትና በሕይወት ውስጥ ምን ሚና እንዳለው እንደማይገነዘቡ ይሰማኛል።» ይህም ባደረግነው ጥናት እንደ ተገነዘብነው በጣም ግልጽ ጕዳይ ነው። አንዳንድ ወጣት ወንዶች ወሲብን አንድን ነገር መግዣ ንብረት አድርገው ይመለከቱታል፤ ተቀባይነትን የሚገበዩበት መንገድ አድርገውም ይቈጥሩታል። አንዳንዶች ደግሞ እንዲሁ ለደስታ ሲባል ማድረግ የሚለው ፍልስፍና ማራኪ ሆኖ ያገኙታል፤ ከዚህም የተነሣ ከወሲባዊ ግንኙነት፣ ከእንስላዊ ዕርካታ ደረጃ ያለፈ ነገር ሊያገኙ አይችሉም። ወሲብን ከፍቅር ግንኙነት ጋር ለማያያዝ የሚፈልጉት እንኳ፣ ሙሉውን ሥዕል አያዩም።

እግዚአብሔር ለምን እንደ ፈጠረው ከተረዳችሁ በኋላ እንኳ ወሲብ ግራ የሚያጋባ ነገር ነው። ሕይወታችሁን በተጣመመ አመለካከት ላይ በምትመሠርቱበት ጊዜ በርግጥ ጕጂ ነው። አንዲት ልጃገረድ፣ «በጋብቻ ውስጥ እንኳ ቢሆን ጎጢአት መስሎ ይታየኝ ነበር» በማለት ተናገረች። ይህ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ወሲብ ከሚናገረው ሐሳብ ጋር አይጣጣምም። ይህ አመለካከት ለእርሷና ለወደፊት ባሏ ጋብቻን በርግጥ አስቸጋሪ ያደርገዋል! ነገር ግን ከስሜት ዐልፎ ድርጊት ደረጃ ላይ ስለ መድረስ የጻፈች የዐሥራ ሰባት ዓመት ልጃገረድ እንዲህ አለች፤ «መዳራት ጥሩ ይመስለኛል፤ ሰዎች እርስ በርስ ቢዋደዱ መልካም ነው፤ ምክንያቱም የሰው ተፈጥሮ ነው፤ እግዚአብሔርም በጎ ነው ይሰዋል፤» ይህም በበኩሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ የራቀ ነው።

እንዲህ ያለው አጕል ግንዛቤ እንዴት ሊከሠት ይችላል? መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆኑ አጥጋቢ ምክንያቶች የተደገፈ ጥርት ያለ ደንብ ለማውጣት ለምን አስቸጋሪ ሆኖ ይታያል? ወጣቶች የሚጠይቋቸው ብዙ ጥያቄዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቀጥታ አልተመለሱም።

እግዚአብሔር ወሲብን ለምን ፈጠረ? ወሲባዊ ጠባይን የሚመለከቱት ደንቦች የማይለወጡ ናቸውን? ጋብቻን ጋብቻ የሚያደርገው ነገር ምንድን ነው? ሩካቤ ሥጋ ነውን? ሥነ ሥርዐት ነውን? ወይስ ሌላ ምንድን ነው? የጋብቻ ዐላማውና ትርጕሙ ምንድን ነው? አንዳንድ ሰዎች ከጋብቻ ውጭ ፍቅርን መግለጽ «ራስ ወዳድነት» ነው፤ በጋብቻ ውስጥ ከሆነ ግን ያንኑ ነገር ፍቅር ነው ለምን ይላሉ? በፍቅርና በፍትወት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ወሲባዊ ፍላጎትን በጋብቻ ውስጥ ሲሆን «ፍቅር»፣ ከጋብቻ ውጭ ግን «ፍትወት»

የሚያደርገው ነገር ምንድን ነው? ጋብቻን አስመልክቶ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተገለጠውን ታሪክና የቤተ ክርስቲያን ትምህርትን እንዴት ታስታርቁታላችሁ? ፍላጎቶቻችን በራሳቸው ጎጢአት ናቸውን?

አንድ ሰው ስሕተት ሠርቶአልን?

እውነቱን በደንብ ለመረዳት ቀዳሚ ጉዳይ ይህ ሳይሆን አይቀርም። እግዚአብሔር በወንድና በሴት መካከል የወሲብ ግንኙነት እንዲኖር ሲያደርግ አልተሳሳተም ነበር። ወንዶችና ልጃገረዶች ለአካለ መጠን ሲደርሱ በውስጣቸው የሚቀሰቀሰው ስሜት፣ ከሰውነታችን ወሲብ ቀስቃሽ ከሆኑት አካሎች ጋር ግንኙነት ያላቸው አስደሳች ስሜቶች ሁሉ በዐላማ በእግዚአብሔር የተፈጠሩ ናቸው። በወንዶችና በሴቶች ላይ የስሜት አውታሮችን ጫፍ ሠራ። ለመሳሳም፣ ለመደባበስ፣ ለመዳራትና ለሩካቤ ሥጋ የሚመቹ፣ የሚያማልሉና የሚያስደስቱ አድርጎ አበጃቸው።

በዘፍጥረት 1÷27 ላይ «እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክ» የፈጠረው መሆኑን «ወንድና ሴት አድርጎ» እንደ ፈጠራቸው ያመለክታል።ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ወሲብ ያላንዳች ጎፍረት ይናገራል። «አዳምና ሚስቱ፣ ሁለቱም ዕራቍታቸውን ነበሩ፤ ይሁን እንጂ አይተፋፈሩም ነበር» (ዘፍ 2÷25)። ዛሬ ብዙዎች በሚናገሩት ዐይነት ስለ ወሲብ መናገሩ አሳፋሪ ሊሆን ቢችልም እንኳ፣ ወሲብ አሳፋሪ ወይም መንፈሳዊ ይዘት የሌለው አይደለም፤ የተቀደሰ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አስደሳች ተመክሮንና አላገባብ መጠቀምን በእውነተኝነት በመግለጽ ስለ ወሲብ ያለው አመለካከት ግልጽ ነው።

ስለ ወሲብ በእግዚአብሔር ፊት በግልጽ በመናገር «የተቀደሰ» አድርገን ማሰብ ለእኛ አስቸጋሪ ነው። ባልና ሚስት ያላንዳች ችግርና ያላንዳች የበደል ስሜት ሊያደርጉት እንደሚገባ ማሰብ ሊከብደን ይችላል። እርግጥ ነው ወሲብ የግል ጉዳይ ነው፤ በሁለት ሰዎች መካከል የሚፈጸም ጉዳይ ነው። ሁለት ሰዎችንና እግዚአብሔርን የሚመለከት ነው። ይሁን እንጂ በዚያ ዐውድ ውስጥ ማንኛውም ስሜት፣ ማንኛውም ደስታ፣ ማንኛውም ተመክሮ ለእኛና ለእርሱ አስደሳች ነው። እግዚአብሔር ሰውን ከፈጠረ በኋላ የፈጠረውን ሁሉ እንዴት አድርጎ መዘነው? እርሱ የሰጠው አስተያየት ዓለምን ወይም የእንስሳትን ዘር ከፈጠረ በኋላ እንደ ሰጠው ዐይነት ያለ አስተያየት ነበርን? «እነሆም፣ ... መልካም ነበረ» የሚል ብቻ ነበርን? እንዲህ ያለ ቃል አልተናገረም፤ እግዚአብሔር ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ በፈጠራቸው ጊዜ ከሁለንተናቸውና ከጸታቸው መለያ አንፃር ተመለከታቸው፤ «እጅግ መልካም ነበረ» (ዘፍ 1÷31)።

ወሲብ በጎፍረት የሚፈጸም ጉዳይ ነው የሚለውን ሐሳብ ከየት ነው ያገኘነው? ቈሻሻ የሆነ ጉዳይ ነው፤ በውስጣችን የተሠራ የእንስሳ ተግባር ነው፤ ዘር ማፍራት ስላለብን ብቻ መፈጸም ይኖርብናል የሚለውን ሐሳብ ከየት አመጣነው? የዚህ ምንጩ እኛና አካላችን የተለያየን ነን የሚለው ልዩ ሐሳብ ነው። ይህም ሥጋ አልባ የሆነው፣ «እውነተኛው እኛነታችን» ሕይወት እንዲኖረው በተደረገ ሽክላ ውስጥ ለጊዜው እንዲደነቀር ተደረገ የሚለው ሐሳብ ነው።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው የሰው ሥዕል በርግጥ ይህ አይደለም። እግዚአብሔር ብቻ ሊሠራው በሚችል በሆነ ታምር የተገጣጠምን፣ ስምምነት ከሌላቸውና ለየብቻ ከሆኑ (ሥጋና ነፍስ) ነገሮች የተፈጠርን አይደለንም። በርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አካላችን፣ ስለ ነፍሳችንና ስለ መንፈሳችን ይናገራል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ልዩ ቃላት የሚጠቀምበትን መንገድ ምዕራባውያን ፈላስፋዎች ከሚጠቀሙባቸው ሁኔታ ጋር አምታተነዋል።

«የወሲብ ሕይወታችን» ከጠቅላላው ሕይወታችን የተለየ አድርገን ልናስብ አንችልም። ወይም ደግሞ በሰውነታችን ላይ አንድ ነገር ስናደርግ ከእኛ ውጭ እንደሚሆን ነገር አድርገን ልንፈጽም አንችልም፤ ይኸውም እኛ አሁን ሆነን ከምንገኘውና ወደፊት ከምንሆነው የተለየ አድርገን ልንፈጽምበት አንችልም፤ መጽሐፍ ቅዱስ ሰውን በዚህ ዐይነት መንገድ አይከፋፍልም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እኛ ራሳችን ሙሉ መሆናችንን ለማሳየት ሲል፣ ከተለያየ አቅጣጫ «ሥጋ» እና «መንፈስ» የተባሉትን ቃላት ይጠቀማል። ይሁን እንጂ አንዳቸውም የሰውን ማንነት አይከፋፍሉም፤ አካላዊ የሆነውን ወይም «መንፈሳዊውን» ከሙሉው ሰው ማለትም ከሙሉው ሕይወት ለይተው አይመለከቱም።

ይህ እጅግ በጣም አስፈላጊና መሠረታዊ ነገር ነው። ለምን? ምክንያቱም «ሙሉነታችን» ወሲብን «የሥጋ ጉዳይ ነው» ብለን እናልፈው ዘንድ አይፈቅድልንም። ፍትወት ውስጥ የሚገባው አካላችን ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ እኛነታችን ነው። በጋብቻ ትስስር የሚዋሐዱት አካሎቻችን አይደሉም፤ እኛነታችን ነው። ማንኛውም የወሲብ ድርጊት ሙሉውን ማንነታችን ያሳትፋል። ወሲብ እንደ አስፖርት መኪና፣ እንደ ቴሌቪዢንና እንደ ባንክ ደብተር የሚገለገሉበት ነገር አይደለም። ወሲብን ለመረዳት በሙሉ ማንነታችን ዐውድና በድርጊቱ ተካፋይ በሆነው ሌላው ሰው ሙሉ ማንነት ላይ ወሲብ በሚኖረው አስፈላጊ ተጽዕኖ ዐውድ ውስጥ ማየት አለብን።

የግንኙነቶች ሚና፤ አዳም በመጀሪያ እንደ ተፈጠረ ብቻውን በመሆኑ ብዙ ደስተኛ እንዳልነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል። ዘፍጥረት 2÷20 ለከብት መንጋው ስም ማውጣቱን ይነግረናል፤ «ይሁን እንጂ ለአዳም ተስማሚ ረዳት አልተገኘለትም ነበር።» ይላል። በዚህ ጊዜ ነበር እግዚአብሔር አምላክ አዳምን እንቅልፍ እንዲወስደው አድርጎ ሔዋንን ከጐድን ዐጥንቱ ያበጃት። እግዚአብሔር ሴቲቱን ወደ እርሱ ባመጣት ጊዜ፣ ሰውየው ለእርሱ በጣም የምታስፈልገው መሆኗን ተገነዘበ፤ «... ይህች ዐጥንት ከዐጥንቴ፣ ሥጋም ከሥጋዬ ናት» አለ። እግዚአብሔርም ይህን ማብራሪያ አከለ፤ «ስለዚህ ሰው ከአባቱና ከእናቱ ተለይቶ ከሚስቱ ጋር ይጣመራል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።» «ስለዚህ» የተባለው ለምንድነው? ምክንያቱም ቤተ ሰብን ልጅ በማስገኘት በኩል የሚያረካ፣ ለዐቅም አዳም ደርሶ ትዳር ከመመሥረትም አንፃር በሁለቱ ጾታዎች መካከል ያለው «አንድ የመሆን» ግንኙነትን እውን የሚያደርግ፤ ከልብ የሆነ የርስ በርስ መቀራረብ ያስፈልገናል።

«አንድ ሥጋ» የሚለው የጋብቻ ውጫዊ ገጽታ ብቻ አለመሆኑን ማስተዋሉ ጠቃሚ ነው። በብሉይ ኪዳን «ሥጋ» የሚለው ሐሳብ ሰው በምድር ላይ ያለውን ሕይወቱን ማለትም ሙሉውን የሰው ሕይወት የሚመለከት መሆኑን ያስገነዝበናል። በጋብቻ ውስጥ ወንድና ሴት በማንኛውም ደረጃ ባለው ማንነት እርስ በርስ ለመረዳዳት ቃል ይገባሉ። በክርስቶስ ቃል መሠረት ሲገለጽም፤ «አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም!» በተጨማሪም «እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለየው» ይላል (ማቴ 19÷6)።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነው አገላለጽ ሲነገርም፤ ወሲብ ተገቢ የሚሆነው በዚህ አንድ ሥጋ በመሆን ዐውድ ውስጥ ብቻ ነው። እግዚአብሔር አካላችንን ከሙሉ ማንነታችን ጋር አዋሕዶታል፤ በዚህ ረገድ ራስን መስጠትም ሙሉ በሙሉ የመስጠት ማኅተም ተደርጎ ይታያል፤ ይህም ግልጽና እውነተኛ በሆነ አነጋገር «እኔ ሙሉ በሙሉ የአንተ ነኝ» ብለን መናገር የምንችልበት መንገድ ነው።

በዚህ የግንኙነት አውታር ውስጥ ወሲባዊ ግንኙነት ሙሉ በሙሉ መልካም ነው፤

ባልና ሚስት እርስ በርስ የሚያገኙት የሩካቤ ሥጋ ደስታ፣ ለእርስ በርስ ያላቸውን መስጠትና አንዱ ለሌላው የደስታ ምንጭ ሆኖ የመገኘትን ጉዳይ ያጐላዋል፤ ያፀናዋልም። ከዚህ ግንኙነት ውጭ የሆነው ወሲብ የመለኮትን ዕቅድ ማጣመም ይሆናል። ግላዊ ዕርካታን ለማግኘት አካልንና ወሲብን መገልገያ መሣሪያ ማድረግም ነው። ይሁን እንጂ ወሲብ የተፈጠረው ከሰው ግንኙነት ሁሉ የሚበልጠውና በጣም ጥብቅ የሆነው በባልና በሚስት መካከል ያለውን ግንኙነት ለማበልጸግ በሚደረገው ጥረት ለማገዝ ነው።

ስለዚህ እግዚአብሔር ወሲብን ፈጠረ፤ ስሕተትም አልሠራም። የሚያነሳሱና ደስ የሚያሰኙ ስሜቶችን ያበጀ እርሱ ነው። በእነርሱም ሐሤት ታደርጉ ዘንድ ይፈልጋል። ይሁን እንጂ ወሲብ የግብ መድረሻ መንገድ እንጂ በራሱ ግብ አይደለም። አንተ ሙሉ ሰው እንጂ ቴሌቪዥንን ለመዝናኛ እንደሚጠቀሙበት ሁሉ መጠቀሚያ አካል ያለህ አንዳች መሣሪያ አይደለህም። አካልህ አንተው ራስህ ነህ (እንዲህም ስለሆነ እግዚአብሔር ትንሣኤን ዐቅዶአል። እግዚአብሔር የአሁኑን አካላችንን የትንሣኤ አካል አድርጎ ዳግም ለማበጀት ባያቅድ ኖሮ፣ 1ቆሮንቶስ ምዕራፍ 15 እንደሚያመለክተው ዐይነት በዘላለም ሕይወት ራሳችንን ሆነን አንገኝም ነበር)።

ይህ የአንተ ማንነት የሚገለጥበት ሰውነትህ ማለትም አካልህ ከውስጣዊ ስሜትህ፣ ከሥነ ልቦናህ፣ ከመንፈሳዊ ማንነትህ ጋር በጥብቅ የተሳሰረ በመሆኑ፣ አንዱን ከሌላው መነጣጠል አይቻልም። አንዱ በሌላው ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል። ይህ የእርስ በርስ መደጋገፍ በአንድ በኩል ሲታይ እግዚአብሔር ጸታን ሲያበጅ፣ የባለቤትነት መጠበቂያ አድርጎ ያስቀመጠው መሆኑን ነው። ይህም ወሲብን ለመስጠት እንጂ ለመውሰድ ልንጠቀምበት እንደማንችል ያረጋግጣል። ማንም በጋብቻ ውስጥ ባለው የአንድ አካልነት ግንኙነት ካልሆነ በቀር፣ በወሲባዊ ግንኙነት ትርጕምና ዕርካታ ሊያገኝ እንደማይችል ያረጋግጣል።

አድን ነገር ለማግኘት ብለን ወሲብን ስንጠቀምበት ምን ይሆናል? አንዳንድ ወጣቶች እርዳታ ለማግኘት የሚያሰሙት ጩኸት እግዚአብሔር ከሠራቸው የባለቤትነት ማስከበሪያ ዎች ውስጥ ወደ አንዱ ያመላክታል። እነዚህ ወጣቶች ስለ ፈጸሙት ነገር ትክክል መሆን ወይም አለመሆን የሚያውቁት ነገር የለም፤ ይሁን እንጂ በውስጣቸው ትክክል እንዳልሆኑ ይሰማቸዋል። በደል የፈጸሙ መሆናቸው ይሰማቸዋል። ያሻችሁን በሉት ዞሮ ዙሮ ያው የጸጸት ስሜት ነው።

በአሁኑ ጊዜ አያሌ ተማሪዎች ከአሮጌው ትውልድ መታሰሪያ ገመድ ሁሉ ነጻ የሆኑ ይመስላቸዋል። የአባትና የእናታቸው ግብረገቦች ሕጎችና ደንቦች መሰናክል ከመሆን በቀር ያተረፈላቸው ነገር እንደሌለ ይሰማቸዋል፤ ስለዚህ እነርሱ ራሳቸው ከእነዚህ መቀፍደጃዎች ነጻ በመሆን፣ ደስተኞችና ጸጸት ያለሽ ሆነው መኖር እንዳለባቸው ያስባሉ።

ይሁን እንጂ በተማሪዎች ዘንድ ሰፋ ባለና ጠበቅ ባለ መልኩ የሠሩት፣ በዊስኮንሲን ዩኒቨርስቲ የሥነ አእምሮ ፕሮፌሰር የሆኑት ዶክተር ኤስ ኤል ሀሌክ (Dr. S.L. Halleck) እንደሚሉት እንዲህ ያለው ሰው «ሕይወት በተለይም ወሲባዊ የሆነው የሕይወት ገጽታ ያላንዳች ጸጸት ደስታ ይገኝበታል ብሎ ሲያስብ ቆይቶ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ጸጸት አይቀሬ መሆኑን ሲደርስበት በእጅጉ ይረበሻል።» እንግዲህ ዋናው ነገር ይኸው ነው። በተወሰነ መልኩ የጸጸት ስሜት አይቀሬ ነው።

ሴሰኛ የሆነ ሰው «ነጻ የወጣ ሰው ነው»፤ ከአንድ ሰው ጋር በጥብቅ ሳይቈራኝ፣ ብዙ ሰዎችን ለማወቅም ነጻነት አለው የሚለው

ሐሳብስ? በቅርቡ ዶክተር ቴምዶር አይዛክ ሩቢን የተባሉት ሌላ በጣም የታወቁ የሥነ አእምሮ ሊቅ፣ ሴሰኛ የሆነ ወንድ ወይም ሴሰኛ የሆነች ሴት፣ ሴሰኛ ካልሆነው ወንድ ወይም ሴሰኛ ካልሆነችው ሴት ይልቅ በጣም ሥልጡኖችና ነጻ የወጡ ሰዎች ስለ መሆናቸው ተጠይቀው የሰጡት መልስ እንደሚከተለው ነው፡-

«ሥነ አእምሮአዊ በሆነው መልኩ ሲገለጽ፣ በወሲባዊ ረገድ ነጻ የወጡ ሰዎች ቢሆኑ ኖሮ በዚህም ሆነ በሌላ መልኩ ሴሰኞች አይሆኑም ነበር። ሴሰኝነት የከፍተኛ ጭንቀት ውጤት ነው፤ አንድ ችግር እንዳለ የሚያመለክት ነው፤ ሴሰኛ የሆነ ሰው ጭንቀቱን ለመቀነስ ሲል ያለአንዳች ምርጫ ከአንድ መጋጣ ባልንጀራ ወደ ሌላ መጋጣ የወሲብ ባልንጀራ ይነዳል። ለእርሱ ወይም ለእርሷ ወሲብ መተሳሰብ ካለበት ግንኙነት ጋር ዝምድና የለውም፤ ይህኛው ከዚያኛው ይሻላል ሳይባልም ተስፋ አስቈራጭ ነው። በሕክምና ያገኘኋቸው ሴሰኛ ሰዎች ሌላ ሳይሆኑ ብዙውን ጊዜ የተራቀቁ ሥልጡኖችና ነጻ የወጡ ዐይነት የሚባሉ ነበሩ። መፍትሔ ላላገኘው የሕፃን መሻት አሳማኝ የሆነ ምክንያት ለማቅረብ የሚደረገውን ጥረት ለመግለጽ የሚቀርቡት እነዚህ ልዩ ስያሜዎች ተገቢዎች አይደሉም፤ ይኸውም በባለሥልጣን ላይ ለማመፅ ብርቱ የሆነውን ፍላጎት፣ አሸናፊና በጣም ባህላዊ የሆነውን ጎሊና፣ ብስለት የሌለው ወሲባዊ አመለካከት፣ እንዲሁም በየትኛውም ደረጃ ጠንካራ የሆነን ግንኙነት በተለይ ደግሞ ከወሲብ አንዣር ያለውን ግንኙነት ይዞ ለመዝለቅ አለመቻልን የሚገልጽ ጉልሕ ዐቅመቢስነት ነው። እንደሚመስለኝ አንድ ወንድ ወይም አንዲት ሴት በወሲባዊ ረገድ ነጻነትን ያገኙ ዘንድና በጣም ሥልጡኖች ይሆኑ ዘንድ ለብቻ በሆነ፣ ዘላቂነት ባለውና፣ ተሳታፊነት በሚታይበት (ጥልቅ ስሜትን በመለገስና ክብካቤን በማድረግ) በሁለት ተቃራኒ ፆታዎች ግንኙነት ውስጥ ለመገኘት መብቃት መቻል አለባቸው።»

ዶክተሩ የሚሉትና የሥነ አእምሮ ሕክምናው ይበልጥኑ ግልጽ የሚያደርጉት መጽሐፍ ቅዱስ ምንጊዜም ትክክል መሆኑን ነው። እግዚአብሔር ወሲብን ያበጀው ለጋብቻ፣ ለሙሉነት፣ ዘላቂነት ላለውና አንድ ለአንድ ለሆነ የወንድና የሴት ግንኙነት ነው። በዚህ ዐይነቱ ግንኙነት እንደ አንድ ግለሰብ በሳል መሆን እንችላለን፤ ሁለቱ ሰዎችም መጽሐፍ ቅዱስ፣ «አንድ ሥጋ» ናቸው ባለው መሠረት አንድ ላይ ሊያድጉ ይችላሉ። ከዚህ ግንኙነት ውጭ ወሲብ ዋጋ የለውም።

ርግጥ ነው ለጊዜው የላይ ላይ የሆነውን አካላዊ ፍንደቃ ልታገኘው ትችላለህ። ነገር ግን አንተ ከአካልህ የላቅህ ስለሆንህ ጥልቅ የሆነው ርካታ ከቶ የአንተ ሊሆን አይችልም። በዛሬው ዘመን በወሲብ ረገድ «ነጻነት ያለው» ስለ ተባለው ሰው ዶክተር ሩቢን ያደረጉትን ገለጻ የምትቀበልበት ጊዜ ይመጣል። እንዲህ ያለው ሰው ጉጉ ነው፤ መፍትሄ ያልተገኘላቸው የሕፃን ልጅ ፍላጎቶች በአያሌው የሚታዩበት፣ ብስለት ያለውን ግንኙነት በዘላቂነት ይዞ ለመጓዝ ብቃት የሌለው ሰው ነው፤ ከዚህም በላይ ይህ ዐይነቱ የወሲብ ሕይወት «ያ ከዚህኛው ይሻላል ሰይባል ተስፋ አስቈራጭ» ሆኖ ታገኘዋለህ።

በርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ የወሲብ መጽሐፍ አይደለም፤ ይሁን እንጂ ቀጥተኛ የሆነውን ግንዛቤ ይሰጠናል። እኛ ማን እንደ ሆን፣ ጾታ ምን እንደ ሆነ፣ እግዚአብሔር ለምን ወንድና ሴት አድርጎ እንደ ፈጠረን ውስጣዊ ግንዛቤ ይሰጠናል። እንደ አለሌ ለመኖር ጥረት የሚያደርጉት ሰዎች እንኳ፣ ያ የካዱት ልዑል እግዚአብሔር በማንነታቸው ውስጥ ወሲብን ያበጀው ለዐላማ መሆኑን ይረዳሉ፤ ዋጋ ሳይከፍሉበትም ያ ዐላማ እንዲጣመም የማይፈቅድ መሆኑን ይደርሱበታል፤ አሁንም የእግዚአብሔር የባለቤትነት መብት ማስከበር ሥራ ተግባራዊ

ይሆናል። *[Used with Permission of Zondervan Corporation]*

ጋብቻ እንዴት እንደሚሠራ
(How Marriage Works) Nigeria Covenant Study Guide, 1999, Covenant Keepers, Lesson 6

የትዳር ጓደኛ ምርጫ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ ቀዳሚ በሆነው የጋብቻ ታሪክ እንደ ተጠቀሰው እግዚአብሔር ከመጀመሪያው አንሥቶ በዚህ ጋብቻ ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ ተሳታፊ ነበር፤ ለወንዱ ሴቲቱን የመረጠለት እርሱ ነበር። ስለዚህ ሔዋን ብቁ ሴት መሆኗን ከማረጋገጡ በፊት አዳም ሚስቱን መቀበሉ የሚያስገርም አይደለም። ይህን ያደረገውም ወደ እርሱ ያመጣለትን እግዚአብሔርን በማመኑ ነው።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው ይህ ዐይነቱ የትዳር ጓደኛ ምርጫ ልምድ፣ ባሕላዊ ከሆነው የአፍሪካ የጋብቻ ልምድ ጋር በአንዳንድ ረገድ ተመሳሳይነት አለው። ይሁን እንጂ ይህ ውስን የሆነ ተመሳሳይነት ነው። በነባሩ የአፍሪካ ወግ መሠረት ለሙሽራው የትዳር ጓደኛ የሚመርጠው አባቱ ነው (ተመሳሳይነቱ ከእግዚአብሔር ጋር ነው)። ርግጥ ነው ውሎ ሲያድር ይህ ልምድ የሚጋቡት ጥንዶች ራሳቸው ምርጫ እንዲያደርጉ ቦታውን በመልቀቅ ላይ ነው። እግዚአብሔር ክርስቲያን የትዳር ጓደኞች የሚሆኑትን እንዲመርጥ በመፍቀድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወደ ሆነው ልምድ እንመለስ ዘንድ የሚያስፈልገን ሁኔታ አለ፤ ይህም የሚከተሉትን መርሖችን ያካትታል፦

1. እግዚአብሔር ምርጫውን ማክናወን አለበት፤ እግዚአብሔር ይመርጥ ዘንድ አንድ ሰው አዳም እንደ አደረገው መተኛት አለበት። በሌላ አነጋገር የትዳር ጓደኛን ምርጫ በተመለከተ እግዚአብሔር ከእንቅልፉ እስከሚያ ነቃው ድረስ እንዲህ ዐይነቱ ሰው በውጭ ያለውን ሁኔታ መርሳት አለበት (ማሕልየ መሓልይ 8፥4)። እግዚአብሔር ይመርጥ ዘንድ ሁሉን ነገር ለእርሱ መተው ደግሞ፣ በእውነት መጸለይን በማወቅ እና እግዚአብሔር የሚናገረውን የመስማት ልምድ በማዳበር ላይ የተደገፈ ነው። ይህ ሲሆን ብቻ ነው አንድ ሰው ከፍትወት ወይም ከራስ ወዳድነት የመነጨ ፍላጎት ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ራሱ ከእንቅልፉ የቀሰቀሰው መሆኑን የሚረዳው።

2. በትዳር ጓደኝነት የሚጣመር ሰው አማኝ መሆን አለበት፤ መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ክርስቲያን የማታምንን ሴት ማግባት እንደ ሌለበት ግልጽ ያደርጋል (2ቆሮንቶስ 6፥14-15)። በጣም በጠበቀ ጎብረት አንድ ላይ የሆኑ ሁለት ሰዎች ሃይማኖታቸውን በመሰለ ዐቢይ ጉዳይ ላይ በርግጥ መስማማት አለባቸው። ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ «በአሮጌ ልብስ ላይ አዲስ ጨርቅ የሚጥፍ ማንም የለም፤ ይህ ቢደረግ ግን፣ አዲሱ ጨርቅ አሮጌውን ይቦጭቀዋል፤ ቀዳዳውም የባሰ ይሰፋል» (ማር 2፥21)። አንድ ክርስቲያን የማታምንን ሴት ካገባ ተመሳሳይ ሁኔታ ይፈጠራል። አንዱ፣ «አዲስ ፍጥረት» በመሆኑ፣ ሌላው ደግሞ «በአሮጌው ሰው» ቍጥጥር ሥር በመሆኑ፣ በግንኙነቱ ውስጥ ወዲያውኑ መለያየት ይፈጠራል።

3. እምነት አስፈላጊ ነው፤ አንድን የትዳር ጓደኛ መቀበል የሚቻለው በእምነት ነው። እንዲያውም አንድን ሰው የትዳር ጓደኛውን ከጋብቻ በፊት በትክክል ማወቅ አይችልም። ወጥ በደንብ መሥራት የምትችል ወይም የማትችል መሆኗ፣ ስትተኛ የምታንኰራፋ ወይም የማታንኰራፋ መሆኗ ያሉ ትናንሽ የሚመስሉ ግን በጣም አስፈላጊ ነገሮች የተጋቡበትን መድረክ ለቀው እስካልወጡ ድረስ ላይታወቁ ይችላሉ። ይህ ዕንቅፋት ሆኖ ሳይቈጠር አንድ ሰው አብሮ ለማደግና እግዚአብሔርን ለማገልገል የትዳር ጓደኛውን ደስ የማይሉ ሁኔታዎችን ጨምሮ ባሕርይዋን ሁሉ የእግዚብሔር መልካም ስጦታ አድርጐ መቀበል

አለበት። በርግጥ እንደነዚህ ያሉ ባሕርያት እግዚአብሔር እኛን ፍጹም ለማድረግ የሚጠቀምባቸው መሆኑን በምስጋና ተስፋ ማድረግ አለብን። እንዲህ ያለው የእርስ በርስ መቀባበል የጋብቻን ዘላቂነት እውን ያደርጋል።

4. ዘላቂነት ያለው እንዲሆን ያስፈልጋል፤ ባህላዊ በሆነው የአፍሪካ ጋብቻ ወንድ ሚስቱን በዘላቂነት የመቀበል ግዴታ የለበትም፤ ወይም ሚስት ከባሏ ጋር በዘላቂነት የመጣመር ግዴታ የለባትም። በአሁኑ ዘመን በምዕራቡ ዓለም ይበጅ እየተባለ ያለው አካሄድም እያደር ተመሳሳይ እየሆነ በመሄድ ላይ ነው። አንድ ሰው ያገኘው ነገር ደስ የማያሰኘው ከሆነ ምንጊዜም ማስወገድና መለወጥ ይችላል። መፋታት የቤተ ሰብ ትስስር ዋና ጠላት ነው። ክርስቲያኖች፣ ሁለቱ የትዳር ጓደኛሞች በሕይወት እስካሉ ድረስ አብረው መኖር እንዳለባቸው ለሚናገረው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ደንብ መገዛት አለባቸው።

የክርስቲያን ባል ሚና

ከትዳር ጓደኛ ጋር የሚኖር ግንኙነት በመንፈሳዊ ረገድ ለማደግ መልካም ዕድል ነው። ባልና ሚስት አንዳቸው ለሌላቸው እንዲገዙ እግዚአብሔር ይፈልጋል (ኤፌሶን 5÷21)። ይህ ለአፍሪካዊ ባል ጆሮ የማይጥም ሊመስል ይችላል። ወንድ ለሚስቱ እንዴት ሊገዛ ይችላል? ከዚህ ይልቅ ሴቷ ለወንዱ የምትገዛ መሆን የለበትምን? ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ በሚያዘው መሠረት ባል በሚከተሉት መንገዶች ለሚስቱ መገዛት አለበት፤

1. ፈሪሀ እግዚአብሔር ያለበትን አመራር በመስጠት፤ ባል ለሚስቱ ተገዥ ሊሆን የሚችለው ፈሪሀ እግዚአብሔር ያለው መሪ በመሆን ነው። ኤፌሶን 5÷23 ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ባልም የሚስቱ ራስ መሆኑን ያመለክታል። አፍሪካውያን ክርስቲያን ወንዶች ከዚህ ጥቅስ አብልጠው የሚወዱትን ሌላ ጥቅስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈልጎ ማግኘት አስቸጋሪ ነው።

ምክንያቱም ልዩ እንደ ሆኑ የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን፣ ነባሩ አፍሪካዊ አመለካከት ስለሚጠነክር ነው። ይሁን እንጂ እውነቱ ይህን ጥቅስ ብዙ ጊዜ በትክክል መረዳት አለመቻሉ ነው። የዚህ ጥቅስ ዐውድ አንዱ ለሌላው መገዛት እንዳለበት የሚያመለክተው ቀደም ብሎ የተጠቀሰው ጥቅስ ገለጻ ነው። ይህም ራስን ትሑት አድርጎ በማቅረብ መገዛት የሚቻልበት መንገድ ነው። ጉዳዩን ግልጽ ለማድረግ፣ ይኸው የበላይነት ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነው ዐይነት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያመለክታል። ወንዱ የመሪነቱን ሚና የሚያሳይባቸው ፈርጆችም መንፈሳዊ፣ ማኅበራዊ፣ ቍሳዊ እንዲሁም ስሜታዊና አካላዊ የሆኑትን የሕይወት ክፍሎች ያካትታል።

2. የክርስቶስን ዐይነት ፍቅር በመግለጽ፤ ወንዶች ሚስቶቻቸውን መምራት ያለባቸው በፍቅር መንፈስ ነው። ወንድ ደካማ አፍቃሪ ነው፤ ነባሩን የአፍሪካ ወግ የሚከተለው አፍሪካዊ ወንድ ደግሞ ከሁሉም የባሰ ደካማ አፍቃሪ ነው። ጌታ ወንድን ሚስቱን እንዲወድ የሚያዘውም ከዚህ የተነሣ ነው፤ ይህን እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንችላለን? የክርስቶስን ምሳሌነት በመከተልና ሕይወታችንን ለእነርሱ አሳልፈን በመስጠት ነው። ይህ በተግባር ሲገለጽም በማንኛውም ረገድ የሚስቶቻችንን ፍላጎት ከእኛ ፍላጎት ማስቀደም አለብን ማለት ነው። ወንዶች ሚስቶቻቸውን እንደሚወዷቸው በቃላት መግለጽ አለባቸው። ዘመዶችንና ባልንጀሮችን ጨምሮ ከማንኛውም ሰው ይልቅ እነርሱን በመምረጥ ፍቅር ማሳየት ይኖር ባቸዋል። ባሎች የሚስቶቻቸውን ጥረት ማድነቅ አለባቸው። ስጦታዎችን መስጠት፣ ለእነርሱና ለልጆችም አስፈላጊውን ነገር ማድረግ አለባቸው። ባሎች በቤት ውስጥ መገኘትና ሚስቶቻቸውን በሥራ ማገዝ አለባቸው። ከሁሉም በላይ ባል ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ለሚስቱ የሚኖር መሆኑን መገንዘብ አለበት። ትኵረቱ ሚስቱ ለእርሱ ትኖር ዘንድ ማገኘውንም ጥረት ማድረግ ሳይሆን፣ ሕይወቱን ለእርሷ አሳልፎ እስከ

መስጠት ድረስ እርሷን መውደድ መሆን አለበት።

የሚስት ሚና

ይህ ትምህርት ለወንዶች ነው፤ ስለዚህ በጋብቻ ውስጥ የወንዶች ሚና ምን እንደ ሆነ ይበልጥኑ ትኩረት ተሰጥቶበታል። ይሁን እንጂ ወንድ የሚስቱ ሚና ምን እንደ ሆነ መገንዘብ አለበት። በአጭሩ ሊገለጽም የሚስት ሚና የረዳትነት ሚና ነው። ሴት ወደ ወንድ ሕይወት መጣች፤ ምክንያቱም ወንድ ብቻውን ውጤታማ ሆኖ ሊኖርና ሊሠራ እንደማይችል እግዚአብሔር አይቶአል። ስለዚህ እግዚአብሔር ለወንዱ የምትስማማውን ረዳት መረጠለት። ሚስት አስቀድማ በጌታ በመሆን ባሏን መርዳት አለባት። ኤፌ 5÷22 ሚስቶች በማንኛውም ረገድ ለባሎቻቸው በመታዘዝ ለአነርሱ መገዛት እንዳለባቸው ያመለክታል። አሁንም ቢሆን ይህን ጥቅስ ሠልጥነናል የሚሉት የዘመናችን የአፍሪካ ሴቶች አይወዱትም፤ ምክንያቱም ይህ ጥቅስ በነባሩ የአፍሪካ ወግ ውስጥ ያሉትን የጋብቻ መርሖች መጥፎ ጐን የሚያስጠብቅ ይመስላል። ይሁን እንጂ ይህ የመታዘዝ ጥያቄ ባልየው እርሷን ከመውደዱና ከመንከባከቡ መሠረታዊ ዳራ አኳያ መታየት አለበት። ባልየው ከእርሱ የሚጠበቀውን ሚና ባይፈጽም እንኳ፣ አርአያነት ያላት ሚስት ለክርስቶስ ታዛዥ ከመሆኗ የተነሣ የራሷን ግዴታ መፈጸም ይኖርባታል። [*Used with Permission of Covenant Keepers*].